# ምዕራፍ ሁለት

ወ/ሮ አባይነሽ ፀባያቸው ከድሮ እጅግ በጣም ተለወጠ ። የእውሬነት መልክ እየያዘ ሄደ ። ያገኙትን ሰው ሁሉ መቆጣት አበዙ። ሁሉም ትዕግስቱን ጨረሰ ። እንደድሮ ቁጣቸውን ዝም ብሎ የሚቀበል ጠፋ ፤ ደንበኛ ራቃቸው ። ምግብ ቤት የሚሰራው ሁሉ ማንም ሳይበላው እያደረ መደፋት ጀመረ ። ማታ ማታ በደንበኛ ጥበት ሲፈነዳ የሚደርሰው ቤታቸው በየጠረጴዛው ዝንቦች ያንዣብቡበት ጀመር ። የማይከራየው የአልጋ ብዛት ቁጥር እየጨመረ መጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለዚህ ሁሉ የገበያ መቀዝቀዝ ምስጢሩ ገብቷቸዋል ። ሕሊና . . . መጥረቢያዋ . . . በቀል . . ሟርት . . መተት . . . ይሄ ነው በቃ ።

« ይህች ሟርተኛ ፣ የዚያ የሟዋርተኛ ዘር ቂሙን ሲበቀል ነው ወደእኔ የሰደዳት » ብለው ደምድመዋል ። መፍትሄው ደግሞ ግልፅ ነው ። ድግምቱን ማስፈታት አለባቸው ። ለዚህ ደግሞ መጥረቢያው መገኘት ፣ እጃቸው መግባት ነበረበት ። እሁን እሁን ሲያስቡት ይቆጫቸዋል ። መጥረቢያው እርቋል ። ሰዶ ማሳደድ ሆኖባቸዋል ። ግን ደግሞ መገኘት አለበት ። የህይወት ጉዳይ ነው ። ለዚህ ጉዳይ ፈሩቅ አለ ። ፈሩቅ ታማኛቸው ከመሆኑ ጋር ጥሩ የመረጃ ስራም ያውቅበታል ። ሕሊና የምትኖርበትን ቦታ ሲያገኝ ቀናት አልፈጀበትም ። መጥረቢያውን በእጁ ለማስገባት ብዙ ለፋ ። ጎረቤቶቿን ለመደለል ሞከረ ። ከሕሊና እጅ ግን የፈለገውን መጥረቢያ ማግኘት አልቻለም ። ተስፋ መቁረጥ ጀመረ ።

አንድ ቀን ወ/ሮ አባይነሽ ፈሩቅን ወደ ክፍላቸው አስጠርተውት በምስጢር ዓይነት በልመና ዓይን እየተመለከቱት ፣ « ፈሩቅ የእኔ ጌታ እባክህን መላ እታጣም አንድ መላ ፍጠር » በማለት ተማፀኑት ግራ ቢገባቸው ። ፈሩቅም የተጣመሩ እጆቹን እያፋተገ ፣

« እትዬ እኔ ልሙት ! መላው ጠፋብኝ እኮ ! እትዬ ያልሞከርኩት ነገር የለም » አላቸው ።

« ለእኔ እኮ ህይወቴ ነው ይገባሃል ፈሩቅ ! የፈለገው ወጪ ይውጣ እንጂ እሱን ማግኘት አለብኝ » አሉት በእልህ ።

« ለመሆኑ እትዬ አዋቂ ቤት ሄደዋል ? እዚያው እንዳለ እኮ ማርከስ የሚችል አዋቂ አይጠፋም ። እስኪ ያጠያይቁ » ሲል ቀስ ብሎ ነገራቸው ። ከጭንቀት የተገላገለ ያህል ነበር የቆጠረው ። ወ/ሮ አባይነሽ ለፈሩቅ በሚሰማ በሹክሹክታ ድምፅ ፣ « የአዋቂውን ነገርማ ተወው ። ያች እርጉም ከሞተች ጀምሮ እስከአሁን በሸዋና በሐረርጌ አሉ የተባሉ አዋቂዎች የሚሉት በዘርሽ ተቆጥሮ በገዛ ሥጋሽ ተጠምጥሞብሻል ፤ ግማሹ ይሄን አረጂ ይሄን አድርጊ ይለኛል ። ሆኖም እውነተኛውን ያገኘሁት እዚሁ አቃቂ ነው ። የየማነብርሃን ውቃቢ ነው እውነቱን የነገረኝ ። ስሟን ከነአባትዋ ፣ የተበተበችበት ቦታ ሳይቀር ነው ቁልጭ አድርጎ የተናገረው ። ጠምጣሚው አባቷ ነው ።

« መተቱን ለማርከስ ግን መጥረቢያው ካልመጣ ከሥረ መሠረቱ መንቀል አልችልም ብለውኛል » አሉት ሁለት እጃቸውን ወደጣሪያው ከፍ አድርገው « የእሳቸውን አውሊያ የታረቀች የዚህች ግቢ አድባር እንዳለች ይህን መጥረቢያ እጄ ታስገባልኝ ፤ ጥቁር በሬ እርጄ ነው የምክሰው » እያሉ ተለማመኑ ። ለማልቀስም ዳዳቸው ። ፈሩቅ የወ/ሮ አባይነሽ ጭንቀት እጅጉን ያሳሰበው መሰለ ። እምጦ እምጦ አንድ ሀሳብ መጣለት ።

« እ - እ እትዬ ! እትዬ » ሲል ተጣራና ፀጥ አለ ። በሀሳብ እንደሚዋዥቅ ፣ ጥቂት ዘግየት አለ ። « ይሰሙ እትዬ ፤ መቼም በነብሴ ፈርጄ ነው የምገባው ። እርስዎ እንዲህ ሲሰቃዩ ማየት

አልችልም ። የእኔስ መኖር እርስዎ ኖረው በቤቱ ውስጥ የተሰራው ሲሸጥና ገበያው ሲኖር አይደል ? እንግዲህ እንዲህ እናድርግ ፣ መቼም በግዥ ከእጇ መውሰድ የማይታሰም ነገር ነው ። ሆኖም በስርቆት ለማውጣት ይሞከራል ። ግን ግን ጉልበት ሲያስፈልግ ስለሚችል በጉዳዩ ላይ ከጓደኞቼ ጋር መመካከር ይገባል ። ይህ እንግዲህ የሞትና የሽረት ሙከራ ይሆናል » አላቸው ፣ ዕቅዱ ሲሳካ እንደሚችል እራሱን ለማሳመን እየሞከረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸው በፈገግታ ተውጦ « ታዲያ ምን ወሬ ታበዛለህ ? » አሉና ጮኽብት ፤ መልሰው « ቆይ ! ቆይ ! » እያሉ ወደ መኝታ ቤታቸው ሮጠው በእጃቸው ቀያይ ብር ይዘው ተመለሱ ።

እራሱን እያሻሸ በፍንደቃ ይጠብቃቸው የነበረው ፈሩቅ ሁለት እጆቹን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘርግቶ ፣ « ገና እኮ ነው አሁን ምን ያደርግልኛል ብለው ነው ? » ሲል በማቅማማት ዓይነት ተናገረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለማንኛውም ይገዳል በሚል ዓይነት ብሩን ጠቅልለው ሲሰጡት ፣ « ይልቅስ መጠጥና ደግነት የማይደልለው ወንድ የሰም፤ ጋብዛቸው » ብለው እስከ ጓሮ በር ተከትለው ሸኙት ።

ፈሩቅ ከወ/ሮ አባይነሽ ዓይን እስኪሰወር ቀስ አያለ አዘገመ ። ከእይታቸው ከራቀ በኋላ ግን ከኋላው በጦር እንዳባረሩት አሩጫውን ተያያዘው ። ሠፈሩን አልፎ አሳቻ ቦታ ሲደርስ ኪሱ ውስጥ ተጠቅሎ የተቀመጠውን ቀያይ ብር ወጣ አድርጎ በፍጥነት ቆጠረው ። ስድሳ ብር ነበረ ። አልተከፋም ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ተስፋ በመፈንጠቁ ከሰሞኑ ያልታየባቸውን ፈገግታና ደግነት ለሠራተኞቹ ፣ ገብቶ ለሚወጣውም ደንበኛ በአዲስ መልክ በመቅረብ ያሰወትሮአቸው ቀልድና ፌዝ በማውራት መሳቅ አበቡ ። አዲስ የገቡት ሠራተኞች ይህን የተደበቀ ደግነት ሲመለከቱ እውነትም የዘላለም ደግ ሰው አድርገው ቆጠሯቸው ። ነባሮቹም ሠላም በመውረዱ እየተገረሙ



እርስ በርሳቸው ይጠቃቀሳሉ ። ቀኑ ሲመሽ የመጠጥ ቤቱ ገበያም ከወትሮው እየደራ መጣ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከአሁን አሁን ፈሩቅ የመጣ እየመሰላቸው በጓሮ በር ብቅ እያሉ ከዚያ አካባቢ የሚታዩትን የማዕድ ቤት ሠራተኞቹን ፣ « ፈሩቅ መጣ ? » ሲሉ ይጠይቃሉ ። ፈሩቅ ግን ድምፁም በአካባቢው አልተሰማም ። አዝማሚያው አልጥማቸው እያለ መሄድ ጀመረ ። መነጫነጭ ጀመሩ ።

ፈሩቅ በአለባበሳቸው እስከዚህም ደስ ከማይሉ ሰዎች ጋር በፊት ለፊት በር ሲገባ አዩት ። ደስታቸው ልኩን አጣ ። የሚያደርጉትን አሳጣቸው ። ፈሩቅና አብረውት ያሉት ሰዎች የፈለጉትን መጠጥ የፈለጉትን ያህል እንዲጠጡ ለሠራተኞቻቸው ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፉ ።

« አበዱ እንዴ ሴትየዋ ? ዛሬ ደግሞ ማን ይሆን ተረኛ ? » አለች ቆየት ካሰችው ሠራተኞች መካከል አንዷ ። የወ/ሮ አባይነሽ ድርጊት ሳይገርማቸው አልቀረም ። ለሁሉም የዛሬ ደግነት ምስጢር ሊከሰትላቸው አልቻለም ። አንዳንድ ጊዜ የታደሰ ሰው የሚሞትበትን ቀን ቀደም ብሎ ስለሚያውቅ የቁም ተዝካሩን ያወጣል አሉ ።

ወ/ሮ አባይነሽ እስከዛሬ የናፈቃቸውን የጤና ዕንቅልፍ በዛሬው ቀን መልሰው እንደሚያገኙት ፍንድቅድቅ ያለው ፊታቸው ይናገራል። የመኝታ ሰዓቱን የሚወስነው ግን የፈሩቅ ተልዕኮ ነው ። መላ ህይወታቸውን በፈሩቅ እጅ ጥሰውታል ።

« ፈሩቅ እንግዲህ አደራ ፤ መጥረቢያው እጄ እንደገባ ወዲያውኑ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር ቆጥሬ አስረክባለሁ » አሉት። ፈሩቅ ቃል ሳይተነፍስ ከሦስቱ ሰዎች ጋር ተልዕኮውን ለመፈፀም ወጣ ። የመንደር ውሾች ጩኸት አልፎ አልፎ እየተሰማ ጨለማውን እየሰነጠቁ ወደ ተልዕኮዋቸው በጥንቃቄ ተጓዙ ።

* * *

ያሬድና ሕሊና ኑሮአቸውን በመተጋገዝ መምራት ጀምረዋል:: ሕሊና ተደብቆ የነበረ ባልትናዋን በተግባር መተርጎም ጀመረች ። የቤት አያያዙን ፣ የምግብ ሥራውን፣ ቤት ውስጥ መሰራት የሚገባውን ሁሉ እጠቃላ በራስዋ ቁጥጥር ሥር አደረገች ። ያሬድ ፣ ሕሊና እቤት ውስጥ ከገባች ዕለት ጀምሮ ቤት ውስጥ መመገብ ጀመረ:: እንደ ወንድምና እህት በመግባባት ሁለተኛ ወራቸውን ጨርሰው ሦስተኛውን አገባደዋል ። መጀመሪያ ያሬድ ሕሊና ቄስ ትምህርት ቤት ገብታ መስከረም እስከሚደርስ እንድትማር ፈልጎ ነበር:: ነገር ግን ሕሊና ከቄስ ትምህርት በላይ ችሎታ እንዳላት በተጨባጭ አሳየችው ። ያሬድ ባሰው ትርፍ ጊዜ ሕሊናን ሰማስተማር ቆርጦ ተነሳ ። እሷም ትምህርቷን ሳታሰልስ በመከታተል ትጉህ ተማሪ መሆንዋን አስመሰከረች ። ያሬድ መደበኛ ፕሮግራም በማውጣት ጊዜውን በየትምህርቱ ዓይነት በመከፋፈል ማስተማር ጀመረ ። እልፎ አልፎም ጠዋት ጠዋት ስፖርት በማሰራት ያስተምራታል ። እሷም ሳቅ እያፈናት በደስታ እየፈነደቀች ነበር የምትሰራው ።

ከትምህርት ውጪ ሥራ ስትፈታ ያሬድ በመደበኛ ሥራው ላይ ስለሚያጋጥመው ችግርና ስላሰት ሠራተኞች ክፋውንም ደጉንም ያወራላታል ። አምኖ ግን ብቻዋን ከቤት ውጭ እንድትወጣ አያደርግም ። ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ያጫወተችው ፣ እሱም የደረሰባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ሕሊናን ብቻዋን ወደ ውጪ እንድትወጣ የሚያደፋፍሯት አልነበሩም ። የምትፈልገው ቦታ ለማድረስም አይሰስችም ነበር ።



አንድ ቀን ያሬድ እራሱን አሞት በሥራ ሰዓት ወደ ቤት ይመጣል ። በቀጥታ ወደ ሕሊና መኝታ ቤት ሲያመራ ሕሊና አልጋዋ ላይ ተቀምጣ በእጅዋ መጥረቢያ ታቅፋ የሆነ ነገር ስታደርግ ይደርሳል ። ሳያንኳኳ በመግባቱ ይቅርታ ጠየቃት ። የፈፀመችው ግን አዲስ ነገር ስለሆነበት ግር አለው ። በሳሎኑ መሀል የቆመውን ጠረጴዛ በሁለት እጁ ተደግፎ ፊቱን ወደ እሷ መልሶ አትኩሮ አያት:: በድንጋጤ የተቀመጠችው ሕሊና ያቀፈችውን መጥረቢያ እንደያዘች ቀና ብላ አስተዋለችው ። ሁለቱም ከመናገር ተቆጠቡ ። በዝምታ ተያዩ ። መጥረቢያውን አልጋዋ ላይ አሳረፈች ።

« ምነው እንደዚህ ታየኛለህ ? » ስትል የምንተዕፍረቷን ጠየቀችው ።

« ለምን አላይሽ ፤ ይህ ደግሞ ምን ዓይነት ስፖርት ነው ? » በማለት ጠየቃት ።

« ስፖርት አይደለም አለች ቆዘም ብላ ። ብቻ አንድ ቀን ስለዚህ መጥረቢያ ታሪክ አጫውትሃለሁ ። » ብላ ወደኩሽናዋ አመራች ።

ወደ አልጋው ሄዶ መጥረቢያውን አንስቶ እጀታውን ይዞ ወዲያና ወዲህ እያገላበጠ አስተዋለው ። ሕሊናን በሀዘን እየቃኘ ፣ ግራ ቢገባው መጥረቢያውን እያወዛወዘ የሳሎኑን በር አልፎ ሕሊና ወዳለችበት ኩሽና በመሄድ ከበሩ እንደደረሰ ፤ ሕሊና « ውይ ! » ብላ ጮኸች ።

« የመጥረቢያውን ታሪክ እነግርሃለሁ ብለሽኛል ፣ አሁኑኑ ንገሪኝ ! ከዚህ በፊት የምሰራው ሥራ የለም እላት ፍርጥም ብሎ »።

« መጥረቢያውን የነበረበት ቦታ አስቀምጥና እነግርሃለሁ ። » በማለት ወደ በሩ ስታመራ ያሬድ « ግድ የለም እዚሁ ንገሪኝ » ፊት ለፊት መንገዷን ዘግቶ ቆመ ። እሷም ያላሰበችው ነገር ስለተፈጠረባት እና በቀላሱ እንደማይለቃት ስታውቅ ፣

« በል መጥረቢያውን ስጠኝና ልገርህ » ስትል ሁለት እጆችዋን ዘረጋች ፤ ሰጣት ::

« ስለአባቴ ሞት ነግሬሃለሁ :: አባቴ ሲሞት ትቶልኝ የሄደው ይሄንንና አንድ የራሱን ሱሪና ኮት ብቻ ነው :: አባቴ ከእንጨት ፈለጣ ሥራው ሲመለስ ይህን መጥረቢያ አጠገቡ አስቀምጦ የአባትነት ሙቀቱንና ምክሩን ይለግሰኝ ነበር :: ይህ መጥረቢያ እኔን ለማሳደግ ከአባቴ ጋራ አብሮ ተንከራቷል :: አባቴና ቤተሰቦቼ በስደት ከሀገራቸው ሲወጡ አለኝታቸው ሆኖ ከእነሱ ጋር አብሮ የተሰደደው ይህ መጥረቢያ ነበር :: ከአክስቴም ጋር እንድጣላ ያደረገኝ ይህን መጥረቢያ ለመውሰድ በመሞከራቸው ነበር :: አሁንም በዚህ መጥረቢያ ላይ የአባቴ ወዝ ይገኝበታል :: ሲከፋኝ ይህ መጠረቢያ ነው የሚያጽናናኝ :: ስለዚህ ማንም እንዲነካው ፤ ካጠገቤም እንዲርቅ አልፈልግም » በማለት በፍቅር ዓይን አየችው ::

« አሁንስ ተረዳህ ታሪኩን ? በል እንግዲህ ፍቀድልኝና ልሂድ» አለችው ::

በራሱ ንቅናቄ መፍቀዱን ገለፀላት :: ሁኔታዋ ስሜቱን ተጭኖት ነበር :: ወደ መኝታ ክፍሏ እንደገባች ከረጢቱ ውስጥ የቀረውን የአባቷን ቁምጣ ሱሪና ካኪ ኮት አስቀምጣ አልጋዋ ላይ አረፍ አለች :: እፍታም አልቆየች :: ብድግ ብላ ወደበሩ ተጠግታ ፤

« ጋሼ ያሬድ » ስትል ተጣራች ::

« ምነው ጠራሽኝ ? » ሲል ጠየቃት :: ምንም ሳትናገር አንገቷን ቀና አድርጋ ወደ አልጋዋ ጠቆመችው :: ከመጥረቢያው ሌላ ሱሪና ኮት አስተዋለ ::

« ለመሆኑ አባትሽ ዕድሜያቸው ስንት ነበር ? » ሲል ጠየቃት ::

« የት አውቀዋለሁ » አለችው ፤ ከሀዘንዋ ሳትወጣ ::



ያሬድ ሒሲናን ብዙ ጥያቄ ለመጠየቅ ፍላጎት ቢኖረውም እነኝህ ጥያቄዎች ሀዘኗን የሚቀሰቅስባት ፤ ክፉ ነገሮችን የሚያስታውሳት ስለመሰለው ከመጠየቅ ተገታ ::

ይህን መጥረቢያ እንደአባቷ ማስታወሻ አድርጋ ማየቷ አይከፋም :: ግን እንደ አምልኮት ማመን እንዳትጀምርና የሰብእናዋን ጥያቄ እንዳይፈታተናት ፈራ :: በተለይም የእምነት ህይወቷን እንዳያበላሽባት የተለየ ትምህርት እንደሚያስፈልጋት አሰበ ::

« ሒሲና ፤ አባትሽ ከመሞታቸው ቀደም ብሎ የተነሱት ፎቶግራፍ የለም ? » ሲል ያላሰበችውን ጥያቄ ጠየቃት ::

« እይ ጋሼ ያሬድ አባቴ እንኳን ስለፎቶግራፍ ሲያስብ ቀርቶ የዕለት ጉሮሮአችንን በመከራ ነበር :: አሸንፈን የምንኖረው :: በነገርህ ላይ ስለአባቴ እንድታስብ አልፈልግም :: ከኔ አልፎ አንተን ማስጨነቅ አልፈልግም » አለችው ፤ ከራሷ ይበልጥ የያሬድ ሁኔታ አሳሰባት::

« ስለሞተ ሰው ማሰብ በህይወት ያሉትን አለመዘንጋት መሆኑን ተገንዘቢ :: እኛ በሙታን ሀውልት የምንኖር ሰዎች ነን :: የእኛ አባቶች ለፍተው ግረው ጥረው ይህን ህይወት ባያቆዩን ኖሮ እኛ ከመጀመሪያ ሀ . . ሁ . . ብለን ይህችን ዓለም መገንባት በተገደድንም ነበር :: ሆኖም እነሰም በዛ ኑሮአችን በአባቶቻችን መሠረት ላይ የተጣለ ነው :: የእንቺም አባት እንቺን ተከተው ሲያልፉ ከእሳቸው የተሻለ ኑሮ ፤ ዕውቀትና ዝንባሌ እንዲኖርሽ መመኘታቸው አይቀርም:: መቼም ሰው ሆኖ ከወለደ ለልጁ ጥሩውን ብቻ ነውና የሚመኘው » ሲል ምክሩን ለገሳት ::

« ጋሼ ያሬድ አባቴም ሁልጊዜ እንዲህ ይል ነበር :: አብረን በኖርንበት ወቅት እኔ በምሰራው ሥራ ደስተኛ አልነበረም :: በመጨረሻ የህይወቱ ሰዓትም የተመኘልኝ ተምሬ እራሴን እንድችል ነበር :: ይህ ቃሉ እስከመጨረሻው ህይወቴ ድረስ አብሮኝ ተቆራኝቶ የሚኖር ቀሪ ሀብቴ ነው :: » አለችው ሳግ እየተናነቃት ::

« ከመ/ቤት ያስለዓቱ የመጣሁት እራሴን ስላመመኝ ነበር :: ህመሙንም አስረሳሽኝ » ሲል ወደመኝታ ክፍሉ አመራ :: ሁኔታውን መቀየር ነበረበት ::

« ምሳህን በልተህ አንደኛህን ብትተኛ አይሻልም ? » አለችው::

አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ የጫማውን ክር እያላላ ፣ « ትንሽ ልረፍና ትቀሰቅሽኛለሽ » እያለ ወደላይ ወጣ :: እንዳሰበው ግን ሊያሸልብ አልቻለም :: « ሕሊና . . . ሕሊና በጣም አዋቂ ልጅ ናት :: በመጥረቢያ ማመንን አሁን ምን አመጣው ? የአባቷ ፎቶግራፍ አብሮአት ቢኖር ኖሮ ትተወው ነበር :: ማን ያውቃል ? ስለመጥረቢያው ስትናገር ከአባቷ እኩል ለፍቶ ግሮ ጥሮ ማሳደጉን ታወሳለች ፤ ይህን ሥራ ታዲያ ሌሎች መጥረቢያዎች ሊፈፅሙት አይችሉም ነበር ? . . . »

ሕሊና ሥራዋን ጨርሳ የያሬድን መነሳት ስትጠባበቅ ፀሐይዋ አሽቆለቆለች :: እንዲተኛ ስለፈለገች ልትቀሰቅሰው አልሞከረችም :: ያሬድ በራሱ ጊዜ ሲነቃ በጣም መሽቷል :: እራት ቀርቦ እየተጫወቱ በልተው ወደየመኝታቸው ሄዱ :: ያሬድ ግን እንቅልፉን ጨርሶ ነበር:: ዝናቡ መጣል ሲጀምር ፣ « በሩ በደንብ ተዘጋ ? » ስትል ጠየቀችው ::



* * *

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሠዓት ሆኗል :: ጭለማው ድቅድቅ ያለ ነበር:: ዝናቡ በመጠኑ ያካፋል ፤ አልፎ አልፎ የሠማይ ብልጭታ ይፈነጥቃል :: ፈሩቅ ያልተዘጋውን የግቢ በር ቀስ ብሎ ከፈተ :: ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መዝጊያ አመራ :: መኝታ ቤታቸው ከሳሎኑ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ወደዚሁ መግባት የሚቻለው ሳሎኑን አልፎ በኮሪደሩ በኩል ነው :: ከውጪ ከበረንዳው በስተቀኝ በኩል የሚገኘው የመኝታ ቤት መስኮት ለፈሩቅ ማንም ሳያየው ለማንኳኳት አመቺ ነበር :: የግቢው መብራት በአጠቃላይ ጠፍቷል :: ፈሩቅ የመኝታ ቤቱን መስኮት ቀስ ብሎ አንኳኳ ::ወ/ሮ አባይነሽ እንቅልፍ ስላልወሰዳቸው፣

« ማነው ? » አሉ ፤ ዝግ ባለ ድምፅ ::

« እኔ ነኝ » ሲል ደጋግሞ አንኳኳ ::

ወ/ሮ አባይነሽ መስኮቱን ለመክፈት እጀታውን ከያዙ በኋላ አመንትተው ፣ « በጓሮ ዙርና ና » ሲሉ አዘዙት :: ፈሩቅም በመጣደፍ በጓሮ በኩል ዞሮ የውጭውን በር ቀስ ብሎ በመክፈት በዳበሳ ሁለተኛውን በር አልፎ ወደሳሎኑን በር ገብቶ ግራ ቀኙን ሲቃኝ የወ/ሮ አባይነሽ ምልክት ስላልታየው በኮሪደሩ በኩል ወደመኝታ ቤት በር ሲጠጋ እሳቸውም የመኝታ ቤት በራቸውን ገርበብ አድርገው ከፍተው አንገታቸውን ብቅ አደረጉ ::

« ቀናችሁ ? » ሲሉ ጠየቁት ለመልሱ ጓጉተው :: ልብሱ ርሶ ውሃ ውስጥ ገብታ የወጣች አይጥ የሚመስለው ፈሩቅ በጨለማው ውስጥ ፈገግ አለና በእጁ የያዘውን መጥረቢያ ለወ/ሮ አባይነሽ እያሳየ ፣ « የሰይድ ኑርዬ አምላክ ቀናን እትዬ ፤ እንኳን ደስ ያለዎት » ሲል ፣ ወ/ሮ አባይነሽ የመኝታ ቤቱን በር ወገግ አድርገው ከፈቱለት ::

« የኔ ፈሩቅ ዝናቡ አበስብሶህል ና ግባ አሁን እሞቅሃለሁ » አሉት ፤ በደስታ ተውጠው ::

ፈሩቅ ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ እንደቆመ ወ/ሮ አባይነሽ ወደቁምሳጥናቸው ሮጠው ነጣ ያለ ጨርቅ አምጥተው ሰጡት ::

« አውልቅ ይህን ልብስህን እና ቢጃማውን ልበስ » አሉት :: ፈሩቅ በማመንታት ልብሱን ከላዩ ላይ ወደእሳቸው በሀፍረት እየተመለከተ አወለቀ :: ከአልጋቸው ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን ፎጣ እየወረወሩ ፣

« ሰውነትህን አድርቅ » አሉት :: ያሉትን አደረገ :: አጠገባቸው ጋደም ብሎ መጥረቢያውን እንዴት አድርገው ከሕሊና ኩሽና ሰብረው እንደሰረቁ እንዲያወራላቸው ጠየቁት ::

« ማንም ሰው ነቅቶ ለመከራከር አልሞከረም ? » አሉት ::

« ሰዎቹኮ እኛ ነን :: መጀመሪያውኑ ማን ቢሰማ » አላቸው:: ጥንካሬውንና ወንድነቱን በኩራት እያሳየ ::

« ቱፍ ! ቱፍ ! . . . ቱፍ ! ምኖቹ ናቸው የሞቱ . . ሆ . ሆ አይጣል ነው ወይ ፈርተው ይሆናል ? » አሉ የፈለጉትን በማግኘ ታቸው እየተደሰቱ ::

« ከጓደኞችህ ጋር ለመቼ ነው የተቃጠራችሁት ? »

« ነገ በጠዋት ሰው ሳይነሳ :: ድንገት ያያቸው ሰው እንኳን ቢኖር ከዚህ አካባቢ መሰወር አለባቸው » እያመነታ መለሰላቸው ::

« ታዲያ አሁን እውነት በአንድ ጊዜ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር ሊወስዱ ነው ? » ብለው ፈሩቅን ክንዳቸውን እያንተራሱ ጠየቁት :: ገንዘባቸው እያሳዘናቸው ነበር የተናገሩት ::

« እንዳታስገድሉኝ ፤ እነሱ እንደሆነ በደም የታጠቡ የሰው ነፍስ ምንም የማይመስላቸው ነፍሰ ገዳዬች ናቸው :: እኔን ለማጥፋት ደግሞ ቀደም ሲል ከገደሏቸው ሰዎች ጋር ሲያወዳድሩት ምናቸውም አይደል:: ቃሌን መጠበቅ አለብኝ ! :: » አላቸው በማስተዛዘን ::



« አታዝንልኝም ? እኔ ላንተ የፈለከውን አደርጋለሁ :: ከስሞኑ እንደምታየው ምንም ገበያ የለኝም :: ይህን ያህል ገንዘብ ደግሞ ከየት ታመጣለች ብለህ ነው ? እባክህ ለምናቸው » አሉት እንደማባበል ጠጋ እያደረጉ ::

« አሆሆ ! የምን ልመና ነው ያስገድሉኛል ነው የምልዎት :: ይልቁንስ ለነፍሰችን እንፍራ ፣ እነሱ በእኔ አያቆሙም ይቀጥላሉ :: ጉዳዩን ከእርስዎ እንደበት ሰምተውታል :: ባያይዎት እንኳን ደህና ነበር :: »

« የዚያን ቀን ለምን አመጣሃቸው ? » እኔ እኮ ሲመጡ አልወደድኩም እህ . . ድንገት ቢያዙ እንኳን . . . « ይምጡ ልያቸው» አላሉኝም ፤ ምን ላድርግ ? »

« አሁን ይልቁንም አንድ ሺህ አምስት መቶውን አሁኑኑ እሰጣቸዋለሁ :: ትንሽ ቆየት ብዬ ደግሞ አንዱን ሺህ ብር እጨምራለሁ :: አለበለዚያ ገንዘብ ከዬት አመጣለሁ ? በዚህ ቢስማሙ ተስማሙ ካልሆነም መጥረቢያውን ወስዶ ፖሊስ ጣቢያ ማስመዝገብ ነው ብለህ ንገራቸው :: እንዲህ ስትል አንተንም ይፈሩሃል ወንድ አይደለህም እንዴ ? » ሲሉ በክርናቸው ፈሩቅን ጎሸም አደረጉት ::

ወ/ሮ አባይነሽ ክንዳቸውን አንተርሰውት በሌላው ነፃ እጃቸው ሰውነቱ ላይ እንዳሻቸው ተራወጡ ፣ ደባበሱት . . . ፈሩቅ የወንድነት ፈተና በአንድ ላይ ተደራርቦበት መደራደር አልቻለም :: እቅሉን ሳተ፣ አእምሮውን ተው ሊለው ሊያዘው ቢሞክርም አሻፈረኝ አለው :: ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ ከእጃቸው ለመውጣት በወጥመድ እንደተያዘች አይጥ ተፍጨረጨረ :: ሆኖም ሁሉም ነገር ሀሳብ ሆኖ ቀረ :: ሻካራ እጆቹን ትርፍስፍስ ሰውነታቸው ላይ ላካቸው ፣ መጋለብ ጀመሩ :: እሳቸውም እጃቸውን ላላ አድርገው የሰጡት ህክምና ምን ያህል

እንደሰራ ፈሩቅን ሰረቅ አድርገው አዩት ። እውነትም ሠርቷል ። ከንፈሩ ከንፈራቸውን ዳሰሰ ።

« ወንድማ ወንድ ነኝ ። ነገ ሄጄ እንደነገሩኝ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብሩን ወርውሬላቸው አይ የሚሉ ከሆነ አፋቸውን ለማስያዝ እሞክራለሁ » አለ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ጀመረ።

ወ/ሮ አባይነሽ በመስጠትና ባለመስጠት በሀሳብ ባህር ሲወጡና ሲወርዱ ቆዩ ። « ይህን ሁሉ ለፍተው አልሰጥም ብል በቀላሉ አይለቁኝም ነገሩ ከተባባሰ መቼም ውርደት ነው ። እንኳን መጥረቢያው መጣልኝ እንጂ ከእንግዲህ ገበያውም እንደሚያንሰራራ ተስፋ አለኝ ። ሺህ አምስት መቶ ብር ምን አለው ? የሁለት ቀን ሥራ ነው ። ሰጥቼ ከሁሉም ጭንቀት ብገላገል ይሻላል ። እኔማ እንዳሰብኩት አምስት ሽህ ብር አምጪ ማለትስ ይችሉ አልነበር ? ታዲያ በቀላሉ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ሰጥቶ መገላገሉ በጣም ቀላል ነው ። ሆኖም ምስጢሩን ሁሉ ፈሩቅ ወደውጪ ያወጣው ይሆን ? ከነገሮች ሁሉ ከባዱ እሱ ነው ። ከአሁን በኋላ በጥንቃቄ መያዝ አለብኝ ። . . . አጠገቤ አርጌ ብቆጣጠረው ማን ይጠይቀኛል። ባይሆን . . . ልብሱን መለወጥ አለበት ። ሥራውም በዚያ አካባቢ ሲሆን አይችልም ሲቀየር ይገባዋል ፣ » የወፎች ጩኸት ተሰማ ። ንጋት ሆነ ።

ወ/ሮ አባይነሽ በድንጋጤ ተነስተው « ፈሩቅ . . . ፈሩቅ . . . ፈሩ . . ተነስ ነግቷል » ሲሉ ቀሰቀሱት ። ፈሩቅ የቀኝ እጁን አንገቱ ላይ ጠምጥሞ በዕንቅልፍ ልቡ ፣

« ምነው ቦጌ . . . ገና . . . ገናኮ ነው » ሲል አጉረመረመ ። ወ/ሮ አባይነሽ ከትከት ብለው ከልባቸው ሳቁና « ተበላሽቻለሁ እኔ አባይነሽ » ሲሉ ስሜታቸውን ወደንዴት ለወጡት ።

« ወራዳ ! ደሞ የማነች ቦጌ ? ቦጌ አባክ ይጥፋና ! በል አሁን ልብስህን ለብሰህ . . . የጀመርነውን ሌላ ጊዜ እናወራለን ።



ወደተላከበት ሂድ ፣ » አሉ ስሜታቸውን ለመግታት እየተጣጣሩ ። ነገር ላለማበላሸት ጥንቃቄ እያደርጉ አጠገባቸው ከነበረ ኮመዲኖ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር ቆጥረው ሰጡት ።

ከመኝታ ቤት ሲወጣ ሲል አስቁመው « አትፍራ ፣ ቀሪውን በቅርብ ቀን እሰጣለሁ ። ይህቺ ቦጌ ያልካት ደግሞ ዋ ነግሬሃለሁ ። እንግዲህ ይቅናህ . . . » አሉና ሸኙት ። እንደወጣ የመኝታ ቤቱን በር ዘግተው ትራስጌያቸው ሥር ያስቀመጡትን መጥረቢያ አውጥተው ከእጀታው እስከብረቱ አጠኑት ። የሚፈልጉት መጥረቢያ ላይ አንዳች የተለየ ፅሁፍ ወይም ምልክት ይኖራል ብለው ገምተው ነበር ። ግን እጀታውም ሆነ ጫፉ እንደማንኛውም ተራ መጥረቢያ ሲሆንባቸው ፣ « ታዲያ ምኑ ይሆን ድግምቱ ? » ሲሉ አሰቡና ፣

« ምን አስጨነቀኝ ? የሚቀጥለው ዓርብ አዋቂው ራሱ ይፈታው የለ ? » ሲሉ ሀሳባቸውን ደመደሙ ። የእሳቸው ግዴታ ዕቃውን ጠብቆ እስከ ዓርብ ማቆየትና ማቅረብ ነው ። ከመቀመጫቸው ተነስተው ከቁምሳጥናቸው አዲስ ነጠላ አውጥተው መጥረቢያውን ጠቀለሉት ። ቀስ ብለው ልብሳቸው መሀል አስቀምጠው ቁምሳጥኑን መልሰው ቆለፉት ። ከዚያም እጃቸውን ጨብጠው ሽቅብ ወደሠማይ እያነሱ « የትአባቷ በዚህ ያከትምላታል» እያሉ ወደ መኝታቸው ተመለሱ ።

ሕሊና በጥዋት ተነስታ ፀጉሯን አበጣጥራ ፣ አልጋዋን አንጥፋ ፣ ቁርስ አዘጋጅታ እንደጨረሰች ያሬድን ለመቀስቀስ የመኝታ ክፍሉን በር አንኳኳች ።

« ተነስ ሰዓት ደርሷል » አለችውና የፊት ለፊቱን መግቢያ በር ከፍታ ወደ ኩሽና ተመለሰች ። ኩሽናው አጠገብ ስትደርስ ክው ብላ ቀረች ። እራስዋን በእጆችዋ ይዛ ለመጮህ ቃጣት ። ዓይኖቿን ከኩሽናው በር ሳትነቅል የዋናውን ቤት የጓሮ በር እያንኳኳች ፣

« ጋሼ ያሬድ ! ጋሼ ያሬድ ! » እያለች እንደገና ተጣራች ።

ያሬድ በሩን እየከፈተ ፣ « ምን ሆነሻል ? ምን ሆነሻል ? » አላት በተቻኮለ አነጋገር ፤ በሩን ከፍቶ ከመኝታ ክፍሉ እየወጣ ::

« ሠረቁን . . . ተዘርፈናል ! ትናንትና በቁልፍ ዘግቼው ነበር:: » ስትል በመማፀን ስሜት ነገረችው የኩሽናውን በር እያመለከተች ያሬድ የበሩ ጓንንቸር ተፈልቅቆ መሬት ላይ መጣሉን አስተዋለ ::

« እውነትም ሰብረውታል » አለ ያሬድ የተፈለቀቀውን ጓንንቸር ከመሬት አንስቶ አገላብጦ እያየ ::

ሒሊና ያሬድን ካየች በሁዋላ እየተጣደፈች ወደክፍሉ ዘልቃ ገብታ ነበር :: በምትችለው ፍጥነት ዕቃውን ሁሉ ለማየት ሞከረች :: ቁምሣጥኑም ፣ ቡሀቃውም በቦታቸው አሉ ::

« ምንም አልወሰዱም ፣ ለምን ታዲያ ሰበሩት ? » አለች ያሬድ ወደ ኩሽናው ክፍል ሲገባ አይታው ::

« እነኚህ ፈሪ ሌቦች ሳይሆኑ አይቀሩም :: ሰው ሲገላበጥ ሰምተው ወይም መብራት ሲበራ አይተው ፈርጥጠዋል ማለት ነው:: ግን እኔን ምን ነካኝ ? ቁልፍን ያህል ነገር ሲሰብሩ መስማት ነበረብኝ» አለ በሁኔታው በመገረም ::

« ለዛሬ ተርፈናል ይመስገነው ፤ ለወደፊቱ ግን ጥሩ ማስጠንቀቂያ ይሆናል :: ነቅተን እንጠብቃለን :: . . . በል አሁን ሰዓት ደርሶብሀል ፊትህን ታጠብ ፤ እኔም ቁርስህን ላቅርብልህ » አለችው :: ያሬድ የታዘዘውን ፈፅሞ ቁርስ ስታቀርብለት ፣

« እስኪ አምጪ እንብላው የሌቦቹን ትራፊ » አላት ሠረቅ አድርጎ እየተመለከታት ::

« መቼ ተነካና ነው ትራፊ የምትለው ? » አለች በቅሬታ ዓይነት ::

« ሁሉም ነገር በቦታው አለ አልሽ እንጂ ይጨምር ይቀነስ በምን ታውቂያለሽ ? »



« እኔ ዕቃ ስከድን ምልክት የማድረግ ልምድ አለኝ » አለችው የጠፋ ዕቃ አለመኖሩን እንዲያምንላት ::

« በነገራችን ላይ ዛሬ ሀሰን ይመጣ ይሆናል ፤ ጥሩ ምሳ አዘጋጅተሽ ጠብቂን ሲል የጀመሩትን ርዕስ አስቀየራት ::

« ለመምጣት ያብቃችሁ እንጂ ምሳውስ አይቸግርም » አለችው ::

*          *          *

ጭጋጋማው የክረምት ወራት አለቀ :: ደመናው ሸሽቶ ለንፁህ ሠማይ ቦታውን ሰጠ ፣ አደይ አበባዎች ፈነዱ :: « ዕንቁጣጣሽ በየዓመቱ ያምጣሽ » እያሉ ህፃናት ቦረቁ :: « እዮሃ አበባዬ » በማለት አዲሱን ዓመት በደስታ አበሰሩ :: የተዘጉ ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ ::

የአቃቂ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ግቢ በልጆች ተወራሰች :: ሁሉም ለዘመን መለወጫ የተገዛላቸውን ልብስ ለብሰው አበባ ይመስላሉ :: ወንዶቹ በጨርቅ ኳስ የእግር ኳስ ይጫወታሉ ፤ ሴቶቹ ሰኞ ማክሰኞ ይዘላሉ :: የተወሰኑት ሁለት በሁለት ተጓድነው አረንጓዴ ምንጣፍ በሚመስለው ለምለም ሣር ላይ ተቀምጠው የጠጠር ቅልልቦሽ ይጫወታሉ ፤ ሌሎች ደግሞ « ከም . . . አሞ . . . ሴላ . . . ሪካ . . . » እያሉ የገመድ ዝላይ ይጫወታሉ ::

ቀደም ሲል ት/ቤት ከመከፈቱ በፊት ዳይሬክተሩ ለያሬድ በገቡለት ቃል መሠረት ሒሊና የሦስተኛ ክፍል ፈተና እንድትወስድ ተደርጋ መልካም ውጤት ብታመጣም ለማንኛውም ተብሎ ከሁለተኛ ክፍል እንድትጀምር ተደረገ :: 2ኛ ሀ እንደተመደበች ከበራፉ ላይ ከሌሎች ተማሪዎች ስም ዝርዝር ጋር አብሮ ስሟ ተፅፎ ወጥቷል :: ሒሊና የትምህርት ቤቱ ሁኔታ እንደጓጓችለት አልሆነላትም ::

ከት/ቤቱ ተማሪዎች መካከል እኩያዋን ማየት ባለመቻሉዋ ወይም የልጆቹ የልጅነት ድርጊት አደናግሯት ወይም በሁሉም ምክንያት ግቢው አልመቻት አለ ። እራሷን እንደምንም ስትቆጣጠር፣ ግቢውን ስታጠና ውላ ሲመሽ ወደቤቷ እስክትመለስ ድረስ የሆነ ነገር ሆድዋን ይጎረብጠው ነበር ።

ያሬድ ቤት የገባው አምሽቶ ነበር ። በጥድፍያ ልብሱን አውልቆ ፒጃማውን ለብሶ ሕሊና ጎን ሲቀመጥ በጉጉት ነበር ።

« ውሎሽ እንዴት ነበር ? » ሲል ጠየቃት ።

« ጥሩ ነበር . . . ግን ምንም ትምህርት አልተማርንም ። ዝም ብለን ሜዳ ላይ ስንጫወት ውለን መጣን »

« ታዲያ ትምህርት ቤት መዋሉ ጥሩ አይደለም ? »

« አይ እሱማ ጥሩ ነበር ። ነገር ግን እነኛ ውጫጮች ሲበጠብጡ በጣም ያስጠላሉ . . . . አቤት . . . ጨኸታቸውስ አያድርስ ነው ። የሁሉም በየፊናው መጯጯህ ይሰለቻል ። »

« አይዞሽ አትፍሪ እየቆየሽ ትለምጂዋለሽ ። የት/ቤት ህይወት እውስጡ ካልገቡ በስተቀር ከጅምሩ መረዳት አይቻልም » ሲል ሲያበረታታት ሞከረ ።

በማግስቱ ሕሊና ወደ ትምህርት ቤት አመራች ። ከግቢው ስትደርስ ከሠንደቅ ዓላማው በስተኋላ ተማሪዎች ሲተራመሱ ተመለከተች ። ተማሪዎቹ በየክፍል በየክፍላቸው በመሠለፍ ሠንደቅ ዓላማ ለመስቀል እየተጣደፉ ነበር ። ሕሊና የክፍሏን ልጆች እንደምልክት ተጠቅማ ወደክፍሏ መስመር ገባች ። ለትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ የሠልፍ ቀን ስለነበር ሥነ-ሥርዓቱ የጠበቀ አይደለም ። ሠልፍ መስለፋቸውን መምህራኑ አረጋግጠው አስፈላጊውን የሠንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት ከፈፀሙ በኋላ አንድ ወፈር ያለ ጠይም ደልዳላ ሰው ከተማሪዎቹ ፊት ለፊት ቆመው የሥነ ሥርዓት ሁኔታውን ለተማሪዎች ካስረዱ በኋላ ተማሪዎቹ



ወደየክፍሎቻቸው አመሩ ። ሕሊናም ከ2ኛ ሀ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅላ ወደ ክፍሏ ሄደች ።

በክፍሉ ውስጥ 57 ተማሪዎች ይገኛሉ ። አብዛኞዎቹ ከስምንት ዓመት በታች ናቸው ። በቁመትም ቢሆን ከሕሊና ጋር ሲመጣጠኑ በጣም ትልቅ ልዩነት እንዳለ ይታይ ነበር ። ተማሪዎቹ ክፍላቸው ከገቡ በኋላ የሚፈልጉትን ቦታ ለመያዝ ከፍተኛ ትርምስ ተቀሰቀሰ ። ግማሹ ያለበትን ወንበር ላለመልቀቅ ፣ ሌላው ለማስለቀቅ ሲጋፉ ፣ ሌሎች ደግሞ ላልመጡት ጓደኞቻቸው ቦታ በመያዝ ጭቅጭቅ ሲፈጥሩ ሕሊና ግራ ተጋብታ መሀል ሜዳ ላይ ቆማ በመገረም ስታይ ቆይታ ባገኘችው ባዶ ቦታ ላይ ሄዳ ተቀመጠች ። በመካከል የሥም ጠሪው መምህር ፋይላቸውን ይዘው ወደ ክፍሉ ገቡ። መምህሩ ፂማቸውን ያሳደጉ ፣ ቲትሮን ኮትና ሱሪ የለበሱ ፣ ከቁመታቸው አጠር ብለው መሀከለኛ ውፍረት ያላቸው ፣ በሉጫ ፀጉራቸውና ፂማቸው ላይ አልፎ አልፎ ሽበት ወጋ ወጋ ያደረጋቸው ሲሆኑ ገና ወደ ክፍል ሲገቡ ተማሪዎቹ በአንድ ድምጽ ፣

« ውይ ! » በማለት ከተቀመጡበት ተነሱ ። እዚያው እንደቆሙ ግማሾቹ እጃቸውን በአፋቸው ጋርደው አጠገባቸው ለቆመው ጓደኛቸው በሹክሹክታ ማውራት ጀመሩ ። መምህሩ በጠረጴዛው ላይ ፋይላቸውን ወርውረው ወደ ተማሪዎቹ ፊታቸውን መልሰው ፣

« እንደምን አደራችሁ ተማሪዎች ? እንኳን ለአዲሱ ዓመት የትምህርት ዘመን አደረሳችሁ» ሲሉ ሠላምታ አቀረቡ ። ተማሪዎቹ አፀፋውን እንደመለሱላቸው ሕሊና ወደ ተቀመጠችበት ቦታ እየተራመዱ « ተነሽ ! » ሲሉ ቁጣ ብለው አዘዟት ። ሕሊና ከመቀመጫዋ ለመነሳት ብትሞክርም አነስተኛ የሆነው የመቀመጫው ድጋፍና በውስጥ ያለው ተደራቢ የደብተር ማስቀመጫ አንድ ላይ ተባብረው ጉልበቷን አጣብቀው ስለያዟት መነሳት አልቻለችም ።

ከአጣብቂኙ በግድ ተላቃ ወደ ዳር በመውጣት ቆመች ፡፡ የስም ጠሪው ትዕዛዙን ሰጥተው ወደ መደበኛ ቦታቸው በመመለስ ፣ « ተማሪዎች ተቀመጡ» ሲሉ አዘዙ ፡፡ ሕሊና ግን ሳትቀመጥ እንደቆመች ቀረች ፡፡ በክፍሉ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በሙሉ ፊታቸውን ወደ ሕሊና መልሰው ተመለከቷት ፡፡ ሳቅ አፍኗቸው ነበር ፡፡ የክፍል ኃላፊው ተማሪዎቹን እያዩ ፣ « ትምህርት ቤት እንደ ቡና ቤት ሁሉንም ሰው ቁጭ ብሎ መቀበል አይቻልም ፤ አይደለም እንዴ ተማሪዎች ? » ሲሉ በሽሙጥ ጠየቁ ፡፡ « አይቻልም » በማለት በህብረት ጮሁ ተማሪዎቹ ፡፡

« ስመሆኑ እንዴት ትምህርት ቤት ገባሽ ? » ወደ ሕሊና እየተጠጉ ጠየቋት ፡፡

ሕሊና ለዚህ ላልጠበቀችው ስድብና ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አልቻለችም ፡፡ መምህሩን እያየች ዕንባ ተናነቃት ፡፡ በልመና መልክ ዓይኖችዋ ከብስል ከብለል ይሉ ጀመር ፡፡ ግን ሊገባቸው አልቻለም፡፡ እንዲያውም የመምህሩ ድርጊት የተንኮልና ሰው የላከው ዓይነት መስሎ ታያት ፡፡ በዚህ ላይ በት/ቤት ውስጥ የዚህ ዓይነቱ ዘለፋ ቀመስ ፌዝ እንደሚካሄድና ሁሉም ተማሪዎች በየተራ እንደሚደርስባቸው አላወቀችም ፡፡

በወ/ሮ አባይነሽ ቡና ቤት በፈገግታ የሚቀበሏት እቶ ጌታቸው አድማሱ ፣ የእሁኑ መምህሯ በእነኚህ ትንንሽ ልጆች ፊት እሷን ማዋረዳቸው ሊዋጥላት አልቻለም ፡፡ ገፍትራቸው ልትወጣ አሰበችና የያሬድ ጭንቀት እየታያት ከድርጊቷ ተገታች ፡፡ መምህሩም ፣

« ሁስተኛ እንዳይሰምድሽ እሺ ወይዘሪት . . . ወይስ ወ/ሮ » ሲሉ መምህሩ በማፌዝ ጠየቋት ፡፡ ታፍኖ የነበረ የተማሪዎች ሳቅ ፈነዳ ፡፡ ሕሊና ድርጊቱን መቋቋም አልቻለችም ፡፡ በማታውቀው ኃይል ተገፋፍታ ከመምህሩ ፈቃድ ሳትጠይቅ እያለቀሰች ወጥታ በረረች ፡፡ መምህሩ በሕሊና ድርጊት ተደናግጠው ተከተሏት ፡፡



« ሕሊና ! ሕሊና » ሲሉ ጠሯት ፡፡ ሆኖም ምንም መልስ አላገኙም ፡፡ መልሰው ወደ ክፍላቸው ገብተው ተማሪዎችን በመቆጣት በችኮላ ከክፍል ወጥተው እየተምዘገዘጉ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ አመሩ ፡፡ ተማሪዎቹ በድንጋጤ ፀጥ ብለው ቀሩ ፡፡

ሕሊና እንባዋን እያዘራች ወደቤትዋ ነበር የሄደችው ፡፡ ቤት እንደደረሰች ከረጢቷን አውጥታ አልጋዋ ላይ ተጋደመች ፡፡

« እንግዲህ አባቴ አትቀየመኝ ፡፡ ትምህርት ለመጀመር የመጨረሻ ሙከራዬን በዛሬው ቀን አድርጌ ነበር ፡፡ ነገር ግን የተፈታተኑኝን ሁኔታዎች ሁሉ ለመቋቋም ባለመቻሌ መተው ግዴታ ሆኖብኛል ፡፡ ቀደም ብዬ ቃል በገባሁልህ መሠረት እንተን በመርሳት ወይንም በፍላጎቴ ሳይሆን በመገደዴ ብቻ ነው » አለችና መጥረቢያው ላይ ዓይኖችዋን ተከለች ፡፡ እንደድንገተኛ ውሃ ሙላት ፍርሃት ዋጣት፡፡ መንፈስዋ ባዶ ሆነ ፡፡ በዓይኗ የሆነ ምስል የሚታያት መሰላት ፡፡ ማመን አልቻለችም ፡፡

« አባዬ ! አባዬ! » እያለች ቤቱ ውስጥ ስትጮህ ለእርሷ አልታወቃትም ነበር ፡፡ ከብዙ ቆይታ በኋዋላ ጎረቤቷ የሆኑት የኩቻ እናት ተደናግጠው ወደነያሬድ ቤት ገቡ ፡፡ ሕሊና በትምህርት ቤት ውሎዋ የገጠማትን ዝርዝር ሁኔታ ስትነግራቸው በጣም አዘኑ ፡፡ በማጽናናት መልክ እራስዋን እየደባበሱ ሊያስተኟት ሞከሩ ፡፡

ያሬድ ከሥራ ሲመለስ ቤቱ በጎረቤት ሰዎች ተሞልቶ አገኘው ፡፡ ክፉኛ ተደናገጠ ፡፡ «ምን ሆናችኋል ? ሕሊና ምን ሆነች?» ሲል ዓይኑን አፍጥጦ ጠየቀ ፡፡ የኩቻ እናት « ዝም በል » በሚል ምልክት ተማፀኑት ፡፡ ያሬድ ግራ ተጋባ ፡፡

« አውቄዋለሁ ! ይህን መጥረቢያ አውጥቶ መጣል ነው ! እሱ ካልጠፋ ምንም ጤና አታገኝም ፡፡ ግን በምን ዓይነት ሁኔታ ማስረዳት ይቻላል ? እሷ በጀ አትል ! » እያለ በንዴት እየጮኸ ወደ

ቤት ገባ ። ተቀምጠው ስነበሩት ሴቶች የረሳውን ሠላምታ ሰጥቶ ወደ ሕሊና በመቅረብ ፣

« ሕሊና ደህና ነሽ ? ተሻለሽ ? » ሲል እራ ሷዋን አሻሻት ። እራስዋን በማንቀሳቀስ የአዎንታ ምልክት ፈገግ ብላ አሳየችው ። ሠዓቱ እየቆየ ሲሄድ ሊጠይቋት የመጡ ሰዎች « እግዜር ይማርሽ » እያልዋት ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

ያሬድና ሕሊና ስለሁኔታው ለመወያየት ጊዜ ያገኙ መሰሉ ። ሕሊና ከንዷን ተንተርሳ የያሬድን ዓይን እየተመለከተች ፣

« ጋሼ ያሬድ አትቆጣኝ ከአሁን በኋላ ትምህርት ቤት አልሄድም ። . . . አውቃለሁ ። አሁን ልክ አይደለሽም ብለህ ልትመክረኝ ትሞክር ይሆናል ። የዛሬው ቀን የትምህርት ገበታዬ እንዳሰብኩት ሊሆን አልቻለም ። በዚህ ምክንያት ነው እራሴን ያመመኝ » አለችው ትንፋሿን በረጅሙ ለቃ ። በቀን ውሎዋ ያጋጠማትን የአስተማሪዋን ዘለፋ ፣ ስለልጆቹ ሳቅ አንድም ሳታስቀር ነገረችው ። እና አለች ለስለስ ባለ የድምጽ ቃና በዚህ ሁኔታዬ የአባቴን ምኞት ለማሳካት እንደማልችል ስለተረዳሁ ነው አለችው በሰጨት ብላ ።

« መጀመሪያ ህመምሽ ይሻልሽና ስለ ትምህርቱ በኋላ እንነጋገራለን » አላትና ሌላ መልስ ላለመስማት ወደሳሎን ሲመለስ ከአልጋው ሥር ግማሽ አካሉ የወጣውን መጥረቢያ አስተዋለ ።



*   *   *

ወ/ሮ አባይነሽ መጥረቢያውን በፈሩቅ አስይዘው ከምሽቱ 1 : 30 ሲሆን ከአቃቂ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው ገጠር መሳይ አካባቢ ሄዱ ። ጊዜው ጨረቃ በመሆኑና ዝናብም ባለመኖሩ ለጉዞው አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላቸው ነበር ። እኩል ለዓት ያህል ከተጓዙ በኋላ እጅብ ያሉ የጎጆ ቤቶች ወደሚገኙበት አካባቢ ሲደርሱ ለፈሩቅ ስለሚሄዱበት ቤት ሥነ ሥርዓት ነገሩት ። እሱም የሚነገረውን ሁሉ እራሉን በማነቃነቅ በእሺታ አዳመጠ ። « ፈሩቅ ስትገባ ጫማህን አውልቀህ መግባት እንደአለብህ እንዳትረሳ » አሉት ወ/ሮ አባይነሽ ።

« ኸረ የጫት ቃሚ ዘር እኮ ነኝ ቀን ጎሎብኝ የሰው ጓሮ ጠባቂ ሆንኩ እንጂ ። ግድየለም የሚያስፈራ ነገር የለም » ሲል እንደድሮው ሳይሽቆጠቆጥ መለሰላቸው ።

« አይ ፈሩቅ አንተ ደግሞ ደግ ደጉን ሲነግሩህ ግራ ነው የምትመልሰው »

« እሱን እንኳ ግራ ተናጋሪው ማን እንደሆነ እሱ ነው የሚያውቀው ። ግን ሰውን ትንሽ አድርጎ ሁልጊዜ መገመት ተገቢ አይደለም » አላቸው ። ቤቱ አካባቢ ሲደርሱ ፣ « ለማንኛውም ያ ትልቁ እልፍኝ ነው ። ብዙ አታውራ ። ቀስ ብለን ነው የምንገባው ። እዚያ የተሰበሰበው ሁሉ የከተማው መኳንንትና ወይዛዝርት ናቸው ። የእኔ ተራ ሲደርስ አንተ ልብ ብለህ አዳምጥ » አሉት ።

አንድ የሣር ክዳን ያለው ክብ የጭቃ ቤት አጥር በር አጠገብ ደርሰው እንደቆሙ መልኩን ለመለየት ያዳገተው ጋቢ የለበሰ ሰው ከቤቱ ወጥቶ « ወ/ሮ አባይነሽ ደግ ዋላችሁ ፣ በር ላይ አትቁሙ »

በማለት ወደ ቤት አስገባቸው ። ጫማቸውን አውልቀው ወደ እልፍኙ ገቡ ።

የሚበራው ሻማ ከማሾ ጋር ተደባልቆ ቤቱን የብርሃን ፀዳል ሞልቶታል ። የፊት ለፊት እግራቸውን አጠላልፈው የተቀመጡ ወፋፍራም ሰዎች ነፋስ እንደሚያወዛውዘው ዛፍ አንገታቸውን እየነቀነቁ እጃቸውን ወደ ፊት ለፊታቸው ዘርግተው እራሳቸውን ወደ ለማይ አንጋጠው « አሜን . . . አሜን » ይላሉ ። ከፊት ለፊታቸው በመጋረጃ ውስጥ የማይታይ ሰው ቅኝት ባለው ዜማ እየዘመረ « ሰለላ . . ያ መሀመዴ . . ና ታረቀን ቤትህ ነው አንተ አዳልሞቴ ደፋሩ ግባ በበሩ . . . » በማለት ያዜማል ።

በቤቱ ውስጥ የተሰበሰበው ሴትና ወንድ ከንፈሩን በመምጠጥ፣ « አይ ጌታዬ ባንተው መጀን . . » በማለት እየተቀበለ አመኔታውን ይገልፃል ። ወ/ሮ አባይነሽ ከመጋረጃው ፊት ለፊት እንዲቀመጡ ካዳሚው እያጋፈራቸው በተሰጣቸው ቦታ ላይ ተቀመጡ። ፈሩቅም ከኋላ ከነበሩት ሰዎች ጋር ተደባለቀ ።

ከወ/ሮ አባይነሽ አጠገብ የተቀመጡት አብዬ ጋሻዬ ቢሆኑም አልተያዩም ። አብዬ ጋሻዬ ነጠላቸውን እስከ አፍንጫቸው ድረስ ተከናንበው ሕዝቡ የሚያደርገውን ሁሉ ይፈፅማሉ ። ከፊት ለፊት የቆመው ካዳሚ በመጋረጃው ውስጥ እጁን ሰዶ በእጁ ሙሉ እቃራ ጫት ከማይታየው ሰው በሁለት እጁ ጎንበስ ብሎ ይቀበልና እጅ ነስቶ መለስ ብሎ ከወገቡ ቀና ሳይል ለወ/ሮ አባይነሽ ሲሰጣቸው ከካዳሚው ተቀብለው ስመው በቀሚሳቸው ላይ በማስቀመጥ አንዱን ዘለላ አንስተው እየቀነጠሱ ወደ አፋቸው መክተት ጀመሩ ። አብዬ ጋሻዬ ወ/ሮ አባይነሽን ቀረብ ብለው ከተመለከቱ በኋላ ፣

« ምን እግር ጣለሽ ወ/ሮ አባይነሽ » ሲሉ በሹክሹክታ ጠየቋቸው ። እሳቸውም የተሰጣቸውን የጫት ቅጠል እያመነዠጉ ፣



« አንተን ያመጣህ እኔንም ጎተተኝ » በማለት ፈገግ አሉ ።

« መቼም ሰው ወዶ አይደለም ከሠይጣን የሚዛመደው ፣ የሚያደርገው ሲጠፋው ነው እንጂ » አሉና አብዬ ጋሻዬ በመቀጠል « እውሊያው አልገባም ብሎ ሰው ሁሉ እየቃመ ነውኮ » አሏቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽም « እውሊያው የሚገባው እኮ ሀጢአት የሰራው ሁሉ ለውቃቢው ሲሳል ነው ድንገት መናፍስት ገብተው ከሆነ ያረክስብናል » እያሉ ሲወያዩ ከመጋረጃው ውስጥ የማይታየው ሰው በተለየ ድምጽ ምርቃቱንና እርግማኑን ጀመረ ።

« ጫት ሺዲድ ፣ ሽቶ ሺዲድ ፣ እውዛ ሺዲድ ፣ የሚጠላን ሁሉ ይወገድ ፣ ድንበራችንን ጥሶ የመጣ ፣ እኛን በሰው ፊት ያሳጣ፣ ጠዋራውን ያላነጣ ፣ ሽንኩርትና ቁጦ አላምጦ ውጦ የመጣ ፣ ከንፈሩን መጦ በሰው አሻጥር ለመስራት የሚጠራጠር ፣ ወጊድ በለው እባክህ ፤ እንፈራፍሮ እንዳይረግጠው . . . አዳልሞቴ ፍርዱ የማያወላዳ መጥቻለሁ እንደ እሳት የሚፈጀው ፊቴ ኤሎሂ ! ኤሎሂ ! . . . » በማለት እጓራ ። በአካባቢው የተኮለኮሉ ሰዎችም አንገታቸውን ደፍተው « እግዚዮ ማረን ጌታዬ ይቅር በለን » በማለት እራሳቸውን መሬት ላይ ደፍተው እጃቸውን ወደ መጋረጃው ዘርግተው ይማፀናሉ ። ከባለጉዳዮቹ መካከል አንድ በመሀከለኛ ዕድሜ የሚገኝ ሰው ብድግ ፣ ብሎ

« ጌታዬ በደል ደርሶብኝ ነው የመጣሁት ። ፍርድህን ስጠኝ፣ ስለትህን አገባልሃለሁ » በማለት ሰገደና ቀና ብሎ ተንበረከከ ።

« እህ. . . ህ. . . ህ. . . ህ የመጣኸው ከሩቅ ሀገር ነው ። ቤትህንና ትዳርህን ለማፍረስ ጎረቤቶችህ አድመውብሃል . . . . እህ. . . ህ. . . ህ. . . ህ ከዚህ ቀደም መጥተህ ፈርደንልህ ነበር ። አንተ ችላ አልከው እንጂ አሁን ጊዜም የለኝ እየመሸብኝ ነው » ሲል ከመጋረጃ ውስጥ ያለው ድምፅ አስተጋባ ። የተንበረከከው ሰው ሰገደና ፣

« ኧረ ጌታዬ ያሰብኸን እፈጽማለሁ አትጨክንብኝ » ሲል ተማፀነ ::

« በቤትህ በራፍ ጥቁር በግ እረድና በጣትህ ደሙን ነክተህ በእራስህ ዙሪያ ሶስት ጊዜ አዙር :: የበጉን ጭንቅላት ጓሮ ወስደህ ቅበረው :: የተረፈውን ላሞራ ስጥ ፤ ጠላትህ እንደ አሞራ ይብረር ፤ ሃጃህ ሲሞላ እኛን እንዳትረሳን ፤ ሰማህ ወይ ? » አለው የመጋረጃው ሰው ድምፅ ::

« ስምቻለሁ ጌታዬ :: ስለቴን ጉዳዬ በተፈፀመ በማግስቱ አስገባለሁ » አለና እጅ ነስቶ ተቀመጠ :: ባለተራው አብዬ ጋሼዬ ነጠላቸውን አጣፍተው ሲቆሙ ፤

« አትምጣብኝ ብዬ አልነበረም አንተ ወላዋይ ? » አለ የማይታየው የመጋረጃ ድምጽ ::

« ጌታዬ ማረኝ በጥፋቴ ልትቀጣኝ ይገባሃል አትጨክንብኝ » በማለት መሬት ላይ ተደፉ ::

« የልጆችህን እናት ለምን አስቀየምካት ? የሀብትህ መሠረት እሷም አይደለች? »

« ጌታዬ ሀቅ ነው አስቀይሜአታለሁ :: ሆኖም የወለደቻቸው ሴቶች ብቻ በመሆናቸው ወንድ ልጅ እንድትሰጠኝ ተማልጄህ ነበር :: አሁንም አልተፈፀመልኝም » በማሳዘን ተንበርክከው ተናገሩ ::

« ወንድ ልጅ ወንድ ልጅ እህ . . . ሀ . . . ሀ » በማለት አዜመና « አምናም ወንድ ልጅ ዘንድሮም ወንድ ልጅ ፤ እንደአሳት የሚፈጅ ፤ ለአውሊያችን የሚሆን አጎብዳጅ ፤ እሱማ እውነትህን ነው:: ታዲያ የልጆችህ እናት ማህፀንዋ ወንድ ልጅ አይሸከምም ፤ ከሴላ ሞክር ብዬህ አልነበረም ወይ ? » ሲል የማይታየው ሰው ፀጥ አለ ::

« ጌታዬ ሞክሬ ነበር ፤ አልሆነልኝም እንጂ » አሉ ወ/ሮ አባይነሽን የጎድን እያዩ ::



« የነጠፈች ከብት ምንም ብትጠቃ ለፍሬም አይላት እህ . . . ሀ . . . ሀ . . . ጊደር መሳይ ፈልግ ፤ ስታይህ የምትለውን ፈገግ እህ . . . ሀ . . . ሀ ሰማህ ወይ ? » አለ :: አብዬ ጋሼዬ ፈጠን አሉና፣ « አዎ ሰምቻለሁ ጌታዬ አመጣጤም ለዚሁ ነው ጌታዬ፤

ከአንድ አልባሌ ቦታ ፤
ስሟን የማልጠራው የሆነች ከርታታ ፤
ስሜቴን የነካችው በጥርሷ ፈገግታ ፤
አለች አንዲት ውብ ልጅ ያየኋት ላንዳፍታ ፤
መርቅልኝና ልድፈራት አቤት የኔ ጌታ :: » በማለት

ዓይናቸው ከወ/ሮ አባይነሽ ወደ መጋረጃው በደስተኛነት ስሜት እስተዋለ ::

« እህ . . . ሀ . . . ሀ . ሀሀ
እሷን ለመድፈር ከሆነ ፈቃድህ ፤
ለማግኘት ወንድ ልጅ እንደምንም ብለህ ፤
አውልያው ይከተልህ አቦ እንደልማድህ ::
እህ . . . ሀ . . . ሀ የምድሩ ባለቤት የሰማዩ ጌታ ፤
እንግዲህ ይስማልህ ይህን አቤቱታ » በማለት

የማይታየው ሰው ድምፅ ፍርዱን ሰጠ :: አብዬ ጋሼዬ እየፈነደቁ አጠገባቸው የነበሩትን ወ/ሮ አባይነሽን እንኳን ሳይቀር « አሜን . . . አፎቱሉላሂ » በማለት ስመው ዘየሩ :: በዚህ ዓይነት የብዙ ሰዎች ጥያቄ ፍርድ ከተሰማ በኋላ የወ/ሮ አባይነሽ ተራ ደረሰና ተነስተው ተንበረከኩ ::

« አቤት ! አቤት ! የኔ ጌታ ! » በማለት መማፀን ጀመሩ ::

« ሠላም የለሽ በቤትሽ ፤
የእህትሽ ባል በመጥረቢያ ያስደገመብሽ ፤
ወ/ሮ ፤ የተባልሽውን አገኘሽ ? » ሲል ጠየቃቸው ::

« አግኝቻለሁ ። ጌታዬ እም አግኝቻለሁ ካንተ ምን ይሰወራል፣ ስለትህን ይኸው ለማስገባት እምጥቻለሁ » ሲሉ ከተንበረከኩበት ሆነው በእጃቸው የጨበጡትን ለካዳሚው ሰጡ ። ካዳሚውም ተቀብሎ በመጋረጃው አሳልፎ ለማይታየው ኀው አቀበለ።

« እህ . . . ህ . . . ህ . . መጥፎ ያለበውን በላ ይውረድበት፣ አሁን ምን አደረገችህ ይህች የዋህ ሴት ፣ ለፍታ ስለበላች ! በሠራችው ቤት ፣ . . . ለንፋስ ይዳርገው ፣ እርጉም አጋንንት ፣ እናረክሰዋለን ለጥተን ትሩፋት » በማለት መጥረቢያውን ከሆነ ነገር ጋር ሲያጋጨው የብረት ጩኸት ተሰማ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሳቅና ለቅሶ በአንድ ላይ በማደባለቅ አጠገባቸው የተቀመጡትን ሰዎች አንድ በአንድ እጃቸውን ስመው ቦታቸው ተመልሰው ተቀመጡ ። ከዚያም ወደ አብዬ ጋሻዬ አቅጣጫ እየተመለከቱ ከቢጤዎቻቸው ጋር የባለወረፋውን አቤቱታ እየሰሙና ከንፈራቸውን እየመጠጡ ፣ « አሜን . . . አሜን . . . » በማለት የፈራጁን ድምፅ ተቀበሉ ። በዚህ ዓይነት ሌሊቱ በጭፈራና በዜማ አሰፈና ዶሮ አንድ ጊዜ ሲጮህ በመጅሊስ ላይ የነበሩት ሰዎች ሁሉ እየወጡ መበታተን ጀመሩ ።

ወ/ሮ አባይነሽና ፈሩቅ ተከታትለው ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ እንዳሉ ፣ « አየኸው ያ ወራዳ ሽማግሌ ፣ ቀላል ! ደግሞ ብሎ ብሎ ወንድ ልጅ አጥቻለሁ በማለት . . . ያቺን ወስላታ ገፌ እኮ ነው አግኝቻለሁ የሚለው » ሲሉ ወሬ ጀመሩ ።

« እሷ ደግሞ ማነች ? » ሲል ጠየቀ ፈሩቅ ።

« ያቺን መተተኛ ሕሊና ናታ ! በዚያ በመተቷ ዳበስ ዳበስ ሳታደርገው አልቀረችም ። አንድ ቀን እኔ ጋ መጥቶ ይህች ውብ ቆንጆ እያለ ጆሮዬን ሲያደነቁረኝ ነበር ። »



« እይ . . . ሄ እሱን እንኳ ይተውት ። መተተኛነቷ ከፋ እንጂ ሰውበቷስ ምንም እንከን አይወጣላትም » አላቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ቆም ብለው ፈሩቅን ዓይን ዓይኑን በቁጣ ከገረመሙ በኋላ ፣

« እኔስ ምን ይሻለኛል የዘንድሮ ወንዶች ፣ አንተንም አስነክታህ እንዳይሆን ፣ ዳሩ ምን ያደርጋል መጥረቢያውን በእጅህ ጨብጠህ የለ ምን ቀረህ ? » አሉ በቅናት ።

የፈሩቅ መዳፈር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ እየሆነባቸው ሄደ ። ከብዙ ማለላሰል በኋላ ፈሩቅን ከአጠገባቸው ማራቅ እንዳለባቸው እራሳቸውን አሳመኑ ። ቢሆንም ፈሩቅን ከአጠገባቸው ማራቅ ቀላል አይደለም ። ጠቅላላ ምስጢራቸውን ያውቃል ። ተንኮላቸውን አጥንቶታል ። ከሁሉም በላይ ጭናቸውና ሀብታቸው ጥሞታል ። ሀብታቸውን እሱ በመሰለው መንገድ መቆጣጠርና የእልጋ ደንበኞቻቸውን ማባረር ያዘ። እያደር የእሳቸው ባል ፣ የንብረታቸው ባለቤት እየሆነ ፣ ሰውም እየፈራው መጣ ።

በዚህ ዓይነት ከተራ ሠራተኝነት ወደ ባሰሟልነት ከዚያም እያለ ወደ ባልነት በመጨረሻም የሀብቱ ፈላጭ ቆራጭ አባወራነት እየተሸጋገረ መጣና ወ/ሮ አባይነሽን ማዘዝ ጀመረ ። የሀብታቸው ሁሉ የበላይ ሆነ ።

አንድ ጊዜ ወ/ሮ አባይነሽ በጠና ይታመማሉ ። ፈሩቅ ወደ ህኪም ቤት እንዳይሄዱ በመፈለግ ቤቱ ቂጤማ አስጎዝጉዞ ፣ ቡና አስፈልቶ ፣ ዕጣን አስጭሶ ጠያቂ በመጣ ቁጥር ፣ « ውቃቢ ነው ያልፍላቸዋል » በማለት ከሳሎን እያስቀረ ይሸኛል ። ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መኝታ ቤት እንድታልፍ የተፈቀደላት የወጥ ቤት ሠራተኛዋ ካብትሽ ብቻ ነበረች ። ወ/ሮ አባይነሽ ጣር ባዘለ ድምጽ ፣ ካብትሽ የነብሰ አባታቸውን እንድትጠራላቸው ተማጸኗት ። ወ/ሮ አባይነሽ

ሲፈሩ ሲቸሩ የነፍስ አባታቸውን ጠበል እንዲረጩ ነው በሚል ሰበብ ወደ መኝታ ቤት አስገቧቸው ።

« ምነው ልጄ ? ምን ነካሽ ? » በማለት ጠጋ ብለው የነፍስ አባታቸው ጠየቋቸው ። ከአንገታቸው ነቃ አሉና በሴባ ጣታቸው የነፍስ አባታቸው ዝም እንዲሉ አፋቸውን እየጠበጠቡ አሳዩና ፤

« ካብትሽ » ሲሉ ተጣሩ ። ካብትሽ ከተፍ አለች ።

« ፈሩቅ ሳሎን እንዳለ እይልኝ » ሲሉ አዘዟት ።

« ማንም ሰው የለም » ብላ ካብትሽ ወጣች ።

« አባቴ ይቅር ይበሉኝ ። ሀጢአቴ ከራሴ ፀጉር የበዛ ነው » በማለት መናዘዝ ጀመሩ ወ/ሮ አባይነሽ ።

« ምን ሀጢአት ሰርተሽ ነው ይቅር የምልሽ ፤ ፀበል ፀዲቁን በጊዜው እየለገስሽ ፤ የነፍስ አባትሽን በየዓመቱ በዓሉ እያስታወስሽ ፤ ፀሎትና ቤተክርስቲያን መሳም ሳይለይሽ ፤ ከይህ የበለጠ በሥጋሽ የኖርሽ ለምኑ ነው ንስሃው ? » ብለው የነፍስ አባታቸው ከያዙት መፅሀፍ አንዱን አውጥተው ማንበብ ሲጀምሩ ሲሉ ፤

« ለሱ ጊዜ የለኝም ፤ በጥሞና ያዳምጡኝ ። ይህ ሰውዬ ተጫወተብኝ ። ለእኔ የሚቆም ዘመድ አዝማድ የለኝም ። ሀብቴን ሙጥጥ አድርጎ እራቁቴን ሊያስቀረኝ ነው ። ምን ላድርግ ብዬ ላማክርዎት ነው ያስጠራሁዎት » በማለት ዕንባቸውን በአንሶላቸው ጫፍ እየጠራረጉ ወደ ነፍስ አባታቸው አስተዋሉ ።

« ይህማ ምን ንስሀ አለው ። እግዚአብሄር በመገላገያው ይገላግልሽ እንጂ ። ምን አድርግ ትይኛለሽ ? በማያገባኝ ነገር ገብቼ ነፍሴን ልሸጥ ? » በማለት ወደ መፅሀፋቸው እንደገና በማትኮር ትንሽ አመነቱ ።

« የእህትሽ ልጅ እዚህ አለች ማለትን እሰማለሁ ። እሷን ጠርተሽ ለምን አታማክሪያትም ? » አሉና መልሰው መጽሐፋቸውን



ማንበብ ጀመሩ ። ወ/ሮ አባይነሽ መኝታቸው ላይ በጭንቀት እየተገላበጡ ያስባሉ ።

« ከዚህ ሰው ነፍሴን ሳያጠፋ የሚያላቅቀኝ ቢገኝ የዘላለም ቤቱን የሠራ ነው ። ቀደም ብሎ በሞኝነቴ ያራቅኳቸው ዘመዶቼ አጠገቤ ቢኖሩ ኖሮ አሁን ለዚህ ሁሉ ውርደት ባልተዳረግኩም ነበር ። ምንም ያህል ሒሲና ብትሆን በላይዋ ላይ የፈፀምኩት በደል ኃያል ስለሆነ ይቅር የምትለኝ አትሆንም ። እፌን ከማበላሸት እራሴ ያመጣሁትን መከራ እራሴ ብወጣው ይሻለኛል » በማለት በዝምታ አሰላሰሉ ። በጭንቅ ቀን የዘመድ አስፈላጊነት ከቁሱ ምክር ጋር ልባቸው ውስጥ ገባ ። « ምህረቱን ያውርድልሽ ! » አሉ የነፍስ አባታቸው ከተቀመጡበት እየተነሱ ።

* * *

ያሬድ ከሒሲና ጋር ወደ ት/ቤት በመሄድ በመጀመሪያ የትምህርት ቀን ስለተፈጠረው ሁኔታ ለት/ቤቱ ዳይሬክተር አስረድቶ፣ የሒሲና ቡና ቤት መሥራት በሥራ እጦትና ከዕለት ጉርስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልጾ ፤ አሁንም እንደማንኛውም የት/ቤቱ ተማሪዎች ሥነ ሥርዓትን አክብራ እንደምትገኝ ቃል ገባና እርምት እንዲካሄድ አድርገው ወደ ክፍሏ እንደገና ተመልሳ እንድትገባ አደረገ። ይህን ከማድረጉ በፊት ግን ሒሲናን በት/ቤቱ ውስጥ በዕለቱ የተፈጸመው ድርጊት ለእርሷ ብቻ እንደተፈጠረ ሳይሆን አጥፊና ሥነ ሥርዓትን የማይከተሉ ተማሪዎች ሁሉ የዚህ ዓይነቱ ቅጣት እንደሚፈፀምባቸው በማስረዳት እንደገና ተመልሳ ት/ቤት እንድትገባ አሳመናት ።

ሒሲና ከሣምንት በኋላ ተመልሳ ወደጠላችው ክፍል ስትገባ እየቀፈፋት ነበር ። ሆኖም ቀደም ሲል ሒሲናን ከክፍሉ እንድትወጣ ምክኒያት የነበሩት መምህር በፈፀሙት ስህተት ተፀፅተው እና

ተለውጠው ስታገኛቸው በፊት የነበራት መጥፎ ስሜት ተለወጠ ፡፡ እኚህ መምህር ይባስ ብለው የክፍል አለቃ ሆና እንድትመረጥ አደረጉ፡፡ በመጀመሪያ ምን እንድትሆን ወይም እንድትሰራ መመረጧ አልገባትም ነበረ ፡፡ ከቀን ብዛት ግን ነገሮችን ቶሎ የመቀበል ችሎታዋን አዳበረች ፡፡ በጋራም ሆነ በግል የሚሰጣትን ኃላፊነት ለመወጣት ቻለች ፡፡

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በፌዝም ሆነ በቀልድ ከእሷ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አርመው አክብረው አሜን ብለው ተቀበሉ፡፡ የቤትና የክፍል ሥራ በመስራት ከክፍሏ ልቃ ተገኘች ፡፡

ለዚህ ሁሉ ያበቃት ወደ ቤት በምትመለስበት ወቅት በቀኑ ሥራዋ ስላጋጠማት ችግር ሁሉ ከያሬድ ጋር በመወያየት የምታገኘው ምክር ነበር ፡፡ ሕሊና ከመጀመሪያ ጊዜ አንስቶ ከያሬድ ጋር ዓይን ለዓይን ሲተያዩ የምትመኘው የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ነበር፡፡ ከትምህርቷ መልስ የቤቱ ውስጥ ሥራውን ችላ ባትለውም አጋዥ እንዲሆኗት አንድ ጠና ያሉ የቤት ሠራተኛ በቀን ሥራ ደረጃ ተቀጥረውላታል ፡፡ ኑሮዋ በተማሪ ደረጃ የተደላደለ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከትምህርት ዓለም ለማለናከል የሚመጡ ሀሳቦች አልጠፉም ፡፡ የሦስተኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቃ ወደ አራተኛ ክፍል ስትዛወር ስሜቷን ከሚጎዳ ፤ ባህሪዋን ከሚያሻክር ሁኔታ ጋር ነበር ፡፡

አንድ ቀን ሕሊና ከት/ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ አንድ ነጭ 304 ፔጆ መኪና በምትሄድበት አቅጣጫ በዝግታ ይከታተላት ኖሮ አጠገቧ እንደደረሰ ጥሩንባ ያሰማል ፡፡ እንዲህ ዓይነት መኪና ያለው ሰው ከዚህ ቀደም አነጋግሯት ስለማያውቅ ፊቷን ሳታዞር መንገዷን ቀጠለች ፡፡ የመኪናው ጥሩምባ ያለማቋረጥ ከኋላዋ ጮኸባት ፡፡ ሕሊና ግን በዝምታ አሳለፈችው ፡፡ ከመኪናው ውስጥ በስተግራ በኩል አንድ ፊቱን በውል ለመለየት ያልቻለችው ሰው በመስኮት በኩል እጁን ወጣ አድርጎ የጥሪ ምልክት አሳያት ፡፡



ባሰችበት ቆም ብላ ለጥቂት ጊዜያት አሰተዋለች ፡፡ መልስ ሳትሰጥ መንገድዋን ቀጠለች ፡፡

ነጯ መኪና ከቆመችበት ቦታ ተንቀሳቅሳ ወዲያው ተከተለቻት፡፡ አሁንም ጥሩምባ ተሰማ ፡፡ መኪናው በድጋሚ አጠገቧ እንደደረሰ በመኪናው ውስጥ የተቀመጠው ሰው « ሕሊና አንቺን እኮ ነው ! » በማለት በጎርናና ድምፅ ጠራት ፡፡ ስሟን ስትሰማ ዞር አለች፡፡ ለአንድ አፍታ የጠራትን ሰው ፊት በተከፈተው የመኪና መስኮት አስተዋለችው ፡፡ የሰውዬውን ማንነት ለመለየት አልቻለችም፡፡ ፊቷን መልሳ ወደ ፊትለፊቷ ፈረጠጠች ፡፡ ከሚከተላት ሰው መራቋንና እሱም መመለሱን እንዳወቀች ሩጫዋን አብርዳ ልቧን በቀኝ እጇ ይዛ ስለሰውየው ለማስታወስ ሞከረች ፡፡ መልኩ አዲስ አለመሆኑ ገብቷታል ፡፡ ግን ልታውቀው አልቻለችም ፡፡ ቤቷ እስክትደርስ የዚህን ሰው ማንነት ለማወቅ አዕምሮዋን በማስጨነቅ ብዙ አሰበች ፡፡ ወደቤት ስትገባ ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ምሳ በመብላት ላይ ነበር ፡፡ ቀና አለና ፤

« ደህና ዋልሽ ? » በማለት በፈገግታ ተቀበላት ፡፡ አፀፋውን መልሳ ደብተሯን አስቀመጠች ፡፡ ያሬድ ፊት ያለውን ወንበር ስባ አረፍ አለች ፡፡ ፊቷን በሁለት እጆችዋ መሀል በማድረግ ፤ « እፎይ!» ስትል በረጅሙ ተነፈሰች ፡፡

« ምነው ዛሬ ደግሞ ስፖርት በመጨረሻ ፔሬድ ያሰሯችሁ ጀመር እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ፡፡ « ሰላላበኝ ነው ፡፡ ዛሬ ደግሞ የሆንኩትን ብነግርህ ትገረማለህ » ስትል ጀመረች ፡፡ አዲስ ነገር ለመስማት በመጓጓት ያሬድ ባለበት ተቁነጠነጠ ፡፡

« ደግሞ ምን ተፈጠረ » ሲል ጠየቃት ፡፡

« ነጭ መኪና ያለው ጓደኛ አለህ እንዴ ? ማለቴ እዚህ ከተማ ነጭ መኪና ያለው ሰው ታውቃለህ ? » በማለት አትኩራ ተመለከተችው ፡፡ በዝምታ አንገቱን በአሉታ ነቀነቀ ፡፡

« እሁን ከት/ቤት ስመለስ መንገድ ላይ መኪናውን አቁሞ ወርዶ ወደ እኔ ሲመጣ አሮጩ አመለጥኩኝ »

« ሰመሆኑ ምን ዓይነት ሰው ነው ? »

« ወፍራም ፣ ቀላ ያለ ፣ ነጭ ኮፍያ ያደረገ ። እኔ እንኳን መኪና ውስጥ እንዳለ ነው ያየሁት ። ወርዶ በሩን ሲዘጋ እኔም ዞር ሳልል ሩጫዬን ተያያዝኩት ። »

« ለምን አታነጋግሪውም ነበር ? ለክፉ አይሆን ይሆናል ። »

« ከእኔ ጋር ምን አገናኘው ? ባለፈው ጊዜ ብዙ የከተማው ሊስትሮዎች ሥም ሳይጠቅሱ እዚህ ቦታ በዚህ ሰዓት ሰው ይፈልግሻል እያሉ ሲያስቸግሩኝ ነበር ። እሁን ደግሞ ባለመኪና መጣልኝ » በማለት ፈገግ ብላ ያሬድን አስተዋለችው ። « ሌላ ጊዜ ይህ ሰው ቢጠራሽ የሚፈልገውን ነገር እስከሚነግርሽ እንዳትሸሽ ። መቼም ቀን በቀን በሀገር እማን አይሰርቅሽ » አላት ያሬድ የሰውየውን ማንነት ለማወቅ በሚፈልግ አስተያየት እያስተዋላት ። ከት ብላ ሳቀችና ፣

« እኔን ሰርቆ ምን ያደርግለታል ? » በማለት የዋህ አነጋገሯን ጣል አደረገች ።

« በይ እሁን ልብስሽን እውልቂና መክሰስ በልተሽ ወደ ጥናትሽ » አለና ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። አልጋው ላይ ተጋድሞ ቴፕ ከፍቶ በስሜት ተዋጠ ።

ሕሊና « እኔን ሰርቆ ምን ያደርግለታል » ነበር ያለችው ። ቃሉን እየደጋገመ አኘከው ። ሀሳቡን እያወጣ እያወረደ አብሰለሰለው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሕሊናን በማዘን ፣ በማገዝና በመርዳት ልቡና እንጂ በሌላ መልኩ አይቷት አያውቅም ነበር ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የሕሊናን አንድ ገጽታ ባየ ቁጥር ልዩ ጭንቀት ሰውነቱን እየወረረው መምጣት ጀምሯል ። ሕሊናን በሌላ መልክ ላለማሰብ



ራሱን ደጋግሞ ለማሳመን ቢሞክርም ደመነፍሱን እስከመጨረሻ ማሳመን አልቻለም ።

« ግን ሰውየውን ሰምን አነጋግሪው አልኳት ? » ሲል እራሱን ጠየቀ ።

* * *

ሕሊና ከት/ቤት ስትወጣ ከመንገድ ላይ ቆሞ የሚጠብቃትን ነጭ ፔጆ መኪና ከሩቅ አስተዋለች ። መንገዷን አሳብራ በሌላ በኩል ለመሄድ አሰበችና ያሬድ የተናገራት ትዝ አላት ። መለስ ብላ መንገዷን አቅንታ ወደ መኪናው ተጠጋች ።

« ነይ ግቢ » ብሎ ቢያስገድደኝ « አልገባም ፣ በመኪና መሄድ አለመደብኝም እለዋለሁ ። የሚጠይቀኝ ጥያቄ ካለ እንደዚሁ ያለመኪና ቢጠይቀኝ እንደሚሻል እነግረዋለሁ ። እንቢ ብሎ ለማስገደድ ቢያስብ በድንጋይ መኪናውን አመድ አደርግለታለሁ » እያለች ከራስዋ ጋር እየተማከረች መኪናው አጠገብ ደረሰች ። የተለመደው የመኪናው ጥሩምባ ፓም . . . ፓም . . . የሚል ድምፅ እንዳሰማ ሕሊና ዘወር ብላ ተመለከተች ። ያየችው ባለኮፍያውን ሳይሆን ኮፍያ የሌለው ከራሱ ገባ ያለ ሰው ነበር ። ሕሊና መልኩን ስታይ ወዲያውኑ እስታወሰችው ።

የመኪናው ባለቤት እጁን በመስኮት ወጣ አድርጎ ሕሊናን በምልክት ሲጠራት ካለችበት አልተነቃሳቀሰችም ። ከመኪና ወጥቶ ወደ እሷ ቀስ እያለ ተጠጋት ።

« አረሳሽኝ እንዴ ሕሊና ? እንተዋወቃለን እኮ » አሏት በፈገግታ እያስተዋሏት ።

« መርሳት አልረሳሁም ፤ ሆኖም ለምን ነበር የሚፈልጉኝ ? እቸኩላለሁ » ብላ መንገዷን መቀጠል ጀመረች ።

« አብዬ ጋሻዬ እኮ ነኝ አባይነሽ ቤት አታስታውሽኝም ? » አሏት ከኋላዋ እየተከተሏት ::

« ገብቶኛል ፤ ሆኖም ለምን ይፈልጉኛል ? » በማለት በፍርሀት ዓይነት ከላይ እስከታች ሰውየውን በዓይኗ ፈተሸቻቸው ::

« ልጋብዝሽ ነው የምፈልግሽ ? » በማለት በጥያቄ አመለካከት ዓይን ዓይኗን አስተዋሏት ::

« ግብዣ » የሚለው ቃል የቡና ቤት ትዝታዋ አንደኛው ገፅታ ነው :: ቃሉ እየዘገነናት እርምጃዋን ቀጠለች :: አብዬ ጋሻዬ በግዙፍ ሰውነታቸው መንገዱን ዘግተው ያዙባት :: ሕሊና ቀጥላ ምን ማድረግ እንዳለባት ስታሰላስል ከማታውቀው አቅጣጫ የሆነ ኃይለቃል ተወረወረ ::

« ልቀቃት ትዟድ ! እኩያህ አይደለችም ! ቀላል ! . . . » የሚል ንግግር ተሰማት :: ቀና ስትል ያሬድና አብዬ ጋሻዬ ፊትለፊት ተፋጠዋል :: አብዬ ጋሻዬ የዘጉትን መንገድ ለቀቅ አደረጉ ::

« ለመሆኑ አንተ ማነህ ? » በማለት ያሬድን ጠየቁት ::

« መንገደኛ ነኝ ፤ ከዚህ በላይ ስለእኔ ባታውቅ ይሻልሃል :: ለማንኛውም ከዛሬ ጀምሮ ይህችን ልጅ አነጋግራለሁ ወይም መንገድ ላይ እከተላለሁ ብትል ኋላ በሰው እንዳታዝን :: ይኼ የመጨረሻ ቃሌ ነው :: በተረፈ የሠላም መንገድ ያድርግልህ » አላቸውና ባሉበት ትቶአቸው ፣ ሕሊናን አስከትሎ ወደፊት ገሰገሰ :: ቤት እንደገቡ « ሕሊና ተቀመጭ የምንነጋገረው ነገር አለ » አላት :: በፍርሃት ተውጣ አጠገቡ ተቀመጠች ::

« ይህን ሰው የት ነው የምታውቂው ? »

« የማውቃቸው . . . የማውቃቸው ቀደም ሲል እቴቴ ጋ እያለሁ ነው » አለችው ::

« አነጋግሮሽ ያውቃል ? ማለቴ ከዚህ ቀደም . . . »

« የእቴቴ ወዳጅ ነበሩ :: አንድ ቀን ብቻ ነው ያየኋቸው ::»



« ታዲያ ምን ይልሽ ነበር ያኔ ? »

« ምንም » አለች ::

« ታዲያ እንደዚሁ ከምድር ተነስቶ ይከተልሻል እንዴ ? ለመሆኑ ዛሬ ምን ነበር ያለሽ ? » ሲል ጠየቃት በቅናት ዓይነት ::

« ልጋብዝሽ ነው ያሉኝ »

« ልጋብዝሽ ? እንዲሁ ዝም ብሉ ? ይህ የማይመስል ወሬ ነው » አላት :: ሕሊና የተናገረችው ውሸቷን መሰለው :: አላመናትም :: ጥርጣሬና ቅናት በአንደበቱ ውስጥ ተድበሰበሰ :: ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደመኝታ ቤቱ ገባ :: ያሰልማዱ ልብሱን አወላልቆ ተጠቅልሎ ተኛ :: በአእምሮው ቁርጡ ያለየለት ፣ እንደ ደመና እየተነኑ የሚያስጨንቁ የተለያዩ ሀሳቦች ተፈጠሩ ::

የተፈጠረው ሁኔታ ሕሊናንም አስጨንቋት ቆየ :: በተለይ ፈልጋው ባይሆንም በሷ ምክንያት ያሬድ እንዲከፋ አትፈልግም ነበር:: ብዙ ነገር ስታወጣ ስታወርድ ከቆየች በኋላ ቢያንስ ያሬድን እራት ማብላት እንዳለባት ወሰነችና የመኝታ በሩን አንኳኳች ::

« ጋሼ ያሬድ ራት እንብላ » ስትል በፍርሀት ድምጿን አሰማች ::

« አሞኛል አልበላም አንቺ ብዪ » አላት ፤ በብርድልብሱ ውስጥ እንደተጠቀለለ :: ከዚህ በላይ ልትረብሸው አልፈለገችም :: ደስተኛም አልነበረችም :: እሷም እራቷን ሳትበላ በሯን ዘግታ ልብስዋን አወላልቃ ተኛች ::

ዕንቅልፍ አልነበራትም :: የያሬድ ማኩረፍና በእሷ ላይ ያለው ጥርጣሬ ምስጢር ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረች ::

ያሬድ ለሕሊና ያለው እምነት እየመነመነ መጣ :: ፊቷን ለማየት ያለው ፍላጎት ከድሮው እየቀነሰና ውጪ ማምሸት እያዘወተረ ሄደ :: በቤቱ ውስጥ ቀደም ሲል የነበረው የትብብር መንፈስ ተሰወጠ:: ቁጣና ትዕዛዝ ለያሬድ አዲስ ፀባይ ሆነ :: የዚህ ዓይነቱ

የመከራረፍ ግማሽ ኑሮ በመካከላቸው ለአንድ ሳምንት ያህል ሰፍኖ ቆየ ። ሆኖም ያሬድ በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ የትም እንደማያደርሰው ተገነዘበ ። ራሱን ለመለወጥ ፤ አቀራረቡን ለማሻሻል ወሰነ ።

አንድ ቀን ከስራ መልስ በጊዜ ወደቤቱ ገባ ። ሕሊና እራሷን በሁለት እጆችዋ መሀከል አድርጋ የምታጠና መስላ ጠረጴዛ ላይ ተደፍታ ነበር ። ያሬድ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ተነስታ ወደጓዳ አመራች።

« ሕሊና ተቀመጪ እንጂ ፤ ሰው ሲመጣ ወዴት ሽሽት ነው። ደግሞ ዛሬ ካንቺ ጋር መጫወት እፈልጋለሁ » አላት በፈገግታ።

« ከሥራ አይደለም የምትመጣው ? » ስትል ወደ ኩሽና ሄደች ። የያሬድ መለወጥ ልትገልፀው የማትችለው ልዩ ተዓምር ነበር የሆነባት ። ያሬድ ወደ መኝታ ክፍሉ ገብቶ ፣ የለበሰውን ልብስ አወላልቆ ፣ የቤት ውስጥ የስፖርት ቱታውን ለብሶ ሕሊና የምታዘጋጀውን ጨርሳ ወደ ሳሎን ስትገባ እሱም አብሮ ገባ ።

« ትምህርቱ እንዴት ይዞሻል ? ለፈተና ተዘጋጀሽ ? » አላት የሻዩን ማንኪያ እያወዛወዘ ።

« ደህና ነው ። ለፈተና የቀረን ሁለት ሳምንት ስለሆነ ለዝግጅቱ እደርሳለሁ »

« ትምህርቱን እንኳን እተማመናለሁ በደንብ እንደምታጠኚ ብቻ . . . ብሎ ያሰበውን ሳይጨርስ አቆመ ።

« ለምን ብቻ ብለህ ታቆማለህ ጋሼ ያሬድ ተናገር እንጂ ! ምንድነው ውስጥህ ያለው ነገር ? » ስትል ጭንቅላቷን በቅሬታ አወዛወዘች ።

« ተይው ሕሊና . . . ምን ያደርጋል . . . የኔው ሞኝነት ነው . . . በቃ ፣ በቃ ስለአለፈው አናውራ . . . » አላት ።



« ለምን ጀምረህ ትተወዋለህ ? ሰሞኑን የሆንኩትን እኔና አንድ አምላክ ብቻ ነን የምናውቀው ። . . . » አለችው በመለማመጥ መንፈስ ። ዓይኖችዋ እንባ አግተዋል ። ፊቷ መቅላት ጀምሯል ።

ያሬድ ድንገት ጥንካሬው ከላዩ ላይ እንደጥላ ሲሸሸው ተሰማው ። ከሕሊና ጋር ፍቅር አስቦ የነበረው ስሜቱ ያሳበቀበት መሰለው ። እርግጠኛ ስለመሆኑ ራሱን ተጠራጠረ ።

የቤቱን ጣሪያ በዓይኖቹ እየዳሰሰ « ሕሊና ለሁሉም ነገር መነሻ አለው ። ለእኔም መነሻ አለኝ ። ከዚያ ሰው ጋር ያደረጋችሁት ንግግር ሆዴን አሻክሮታል ።

ሕሊና እኔ ላንቺ የምመኘው ጥሩ ህይወት ነው ። ተምረሽ እራስሽን እንድትችይ ፣ ያለአንዳች ተፅእኖ ሁሉንም ነገር በራስሽ ፈቃድ መስራት እንዳይሳንሽ እፈልጋለሁ ። ለዚህ ደግሞ ባለኝ አቅም የምችለውን ሁሉ አደርግልሻለሁ የሚል እምነት ነበረኝ ። ሆኖም ከሰውዬው ጋር የነበረሽ ግንኙነት ተስፋዬን ሁሉ አጨለመው ። መጥፎ ስሜት አሳደረብኝ ። አየሽ ሕሊና . . . ቡና ቤት ያውቃት ይሆናል ብዬ መጠራጠር ጀመርኩ ። ቢሆንም አትፍረጂብኝ . . . » አለና ዝም አለ ።

ሕሊና ያሬድ ተናግሮ ሳይጨርስ ከት ብላ ከልቧ ሳቀች ። እሱም ግራ በመጋባትና ሀፍረት በተቀላቀለበት ስሜት ወደ ሕሊና እያስተዋለ « ምነው ! ምን ያስቅሻል ? . . . እውነቴን እኮ ነው ፣ ያስቃል እንዴ ? » አለና ፊትለፊቱ ቀዝቅዞ ያበቃለትን ሻይ አነሳ ።

*  *  *

ወ/ሮ አባይነሽ በሥማቸው አንድ አርጌ ቶዮታ ፒክአፕ መኪና በደላላ አስገዝተው በሾፌር እንድትነዳና በፈሩቅ ትዕዛዝ ሥር እንድትውል አደረጉ ። እቅዳቸው ለጥቂት ጊዜያት አይስራ እንጂ ውሎ አድሮ በድርጊት መፈጸሙ አልቀረም ። ፈሩቅ ባጭር ጊዜ የመንጃ ፈቃድ አወጣ ። የመጀመሪያ ዕቅድ መኪናው፣ ራሱ መያዝ ነበር ።

ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር በውሃ ቀጠነ ንትርክ አበዛ ። ቆይቶ መኪናውን እራሱ መያዝ እንዳለበት አፍ አውጥቶ ተናገረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ጥያቄ ሊቀርብላቸው እንደሚችል ያውቁ ነበር ፤ ይፈልጉም ነበር ። መኪናው እንዲገዛ ሲያደርጉም ለዚሁ ብለው ነበር። የፈሩቅን ባህሪ በውል አውቀውታል ። ከስራቸው ለማራቅ ባሰቡ ቁጥር መኪና መግዛት ነበረ የታያቸው ። ግን ያሰቡት ቢሳካም፤ ሊያስጠረጥሩ አልፈለጉም ። ተቃወሙት ። ፈሩቅም ማሸነፉን ያውቅበታል ። ከመኪናውና ከምስጢራቸው የሚበጃቸውን እንዲመርጡ ቀጭን ቃል ተነፈሰላቸው ። ቀስ እያሉ መኪናውን ለቀቁለት ። ፈሩቅ ጊዜ አልፈጀም ። ህይወትን መኖር ጀመረ ። ህይወት ከከተማ ከተማ ጠራችው ። በመኪና ሄደላት ። ልዩልዩ ሰበቦች እየፈጠረ ፤ ወ/ሮ አባይነሽም ያመኑት እየመሰሉ ውጭ ውሎ ማደሩ ተለመደ ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ለወ/ሮ አባይነሽ የሚጠብቁትን መልካም አጋጣሚ ፈጠረላቸው ። እንደልብ ቡና ቤታቸውን ለመቆጣጠር ፣ የቆዩ ወዳጆቻቸውን ለማግኘት ፣ በሰላይነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ተላላኪዎቻቸውን ለማለማራት ዕድል ለጣቸው ። እንደልብ ከቤት



ወጥተው ለመመለስ ፣ ቤተክርስቲያን ለመሳለም አመቻቸው ። አንድ ቀን ወ/ሮ አባይነሽ እንደልማዳቸው ቤተክርስቲያን ደርሰው ሲመለሱ እንደድንገት ከያሬድና ሕሊና ጋር በመንገድ ላይ ተላለፉ ። ወ/ሮ አባይነሽ ባዩት ነገር እርግጠኛ አልነበሩም ። ያሬድና ሕሊና ከዓይናቸው እስኪሰወሩ ባሉበት ቆመው ሸኙዋቸው ።

« እሷ ነች አይደለችም ? » እሉ በህሳብ ከሄዱበት ሲመለሱ። አልተሳሳትኩም እሷው ነች ። » በማለት ለራሳቸው አረጋገጡ ። ቤታቸው እንደገቡ ሰለሞንን ትልቁ ቤት አስጠሩት ። ካለበት ተፈልጎ በጓሮ በር ወደ ሳሎን እንደገባ ፤

« ሰለሞን ስንተኛ ክፍል ደረስክ ? » ሲሉ ጠየቁት ።

ፈገግ ብሎ « አሁን የአስረኛ ክፍል ፈተና ወስጃለሁ ። ለከርሞ ፈተናውን ካለፍኩ አስራአንደኛ ክፍል እገባለሁ » አለ አንገቱን አቀርቅሮ ።

« ጎሽ ! ጎሽ ! ልጄ ጎበዝ » በማለት ጥቂት ከአሰላሰሉ በኋላ « ለመሆኑ ሕሊናን አይተሃት ታውቃለህ ? » አሉት ።

እያቅማማ « እ . . . እ . . . እ . . ሕሊናን ካየኋት . . ብዙ ጊዜ ሆኖኛል » መቼ እንዳያት እያሰላሰለ መለሰ ።

« ዛሬ መንገድ ላይ ያየሁዋት መሰለኝ ። አንድ ወንድ አብሮአት አለ » አሉ ።

« ምን ዓይነት ወንድ ነው ? » አላቸው በጥርጣሬ ዓይነት ።

« መልከ መልካም ወጣት ነው ፤ እረዘም ያለ ፣ ምነው የምታውቀው ነገር አለ እንዴ ? » በማለት ወደ ሰለሞን ተመለከቱ ።

« አዎ አሁን የሚሉት ጋሼ ያሬድን ነው ። ከእሱ ጋር ነው የምትኖረው » አላቸው እንደተራ ነገር ። « እህህ . . . ሀ . . ም . . ም . . » በማለት እየተገረሙ ፣ « ሰው እንደዚህ ይሰወጣል ? » በማለት እራሳቸውን ጠየቁ ።

« በትምህርት ቤቱ የታወቀች ተማሪ ሆናለች ። ባለፈው ጊዜ ለወላጆች ቀን ከጎበዝ ተማሪዎች አንዷ በመሆን ሽልማት ተቀብላለች:: አሁንማ ሕሊና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ እኮ ነች ። » ሲል ስለሞን የጀመረውን ንግግር ቀጠለ ።

« ስለሞን አሁን የጠራኸው ማን አልከው ስሙን ? . . . አዎ ያሬድ . . . ነገ በምሳ ሰዓት ይዘኸው እንድትመጣ » አሉት ትዕዛዝ በመሰለ አቀራረብ ።

« እዬ . . . እህ . . . ሀ . . ሀ . . ጋሼ ያሬድ እንኳን እሺ የሚል አይመስለኝም ። እሱ እኛ ቡና ቤት ገብቶ አያውቅም ። እኔ እንጃ ብቻ እስኪ እነግረዋለሁ » አለ እርግጠኛ ባለመሆን ።

« ምን ማለትህ ነው ? ለምን አይመጣም ? ለማንኛውም አንተ የተባልከውን ፈፅም ። ይምጣ አይምጣ የአንተ ችግር አይደለም» አሉት ተቆጥተው ።

« እሺ እስኪ እንግዲህ መልዕክቱን አደርሳለሁ » አላቸው ።

« ታዲያ መልሱን መቼ ይዘህ ትመጣለህ ? »

« ዛሬ ማታ እሄዳለሁ ። » አለና እጅ ነስቶ ወጣ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድ እቤታቸው መጣ ማለት ከሕሊና ጋር የመታረቅ ዕድላቸው በእጃቸው የጨበጡትን ያህል ሆኖ ተሰማቸው ። ጨለማ ለብሶ የነበረው ተስፋቸው እንደገና እያንሰራራ መጣ ። የያሬድን መልስ በጉጉት ነበር የሚጠብቁት ። ከሕሊና ጋር ታረቁ ማለት በፈሩቅ የተገፈፉትን ነፃነታቸውን በቀላሉ ማስመለስ እንደሚችሉ እርግጠኛ ነበሩ ። እስከዚያው ሁሉም ነገር በምስጢር መከናወን አለበት ። ለእቅዳቸው መሳካት ያመች ዘንድ ካብትሽን ጠሯት ። ሦስት አራት ጊዜ እጅ በመንሳት ወደ ሳሎን የገባችው ካብትሽ ታማኝነቷን በህይወት ዘመናቸው በተደጋጋሚ ያዩት ስለሆነ አልጠረጠሯትም ።



« ካብትሽ ሂጂና አባን ጥሪልኝ ። በጣም እፈልግዎታለሁ ። ሌላም ሥራ ቢኖርዎት ለአንድ አፍታ ብቅ ይበሉ በይልኝ » በማለት አዘዟት ።

« እሺ እሜትዬ » በማለት ካብትሽ እጅ ነስታ ወደተላከችበት ሄደች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ጓዳ ገብተው የቤት ልብሳቸውን ቀይረው ወደ ሳሎን ተመለሱ ። ፈሩቅ ከቤት ከወጣ አራተኛ ቀኑን ይዟል ። ሲወጣ ብርቱካን ለማምጣት ወደ ዲላ እንደሚሄድ ቢነግራቸውም ከወሰደው የገንዘብ መጠን አኳያ በቅርቡ እንደማይመለስ ገምተዋል ። ሳሎን ተቀምጠው ቡና እያስፈሉ ቁርሳቸውን እየበሉ እንዳሉ የነፍስ አባታቸው በጓሮ በር ገቡ ። ያልታጠቡትን እጃቸውን ወደኋላቸው እንደመደበቅ አደረጉና ከመቀመጫቸው ተነስተው « ይግቡ አባ » ከማለታቸው ፣ አባ ከጋቢያቸው ውስጥ በኪሳቸው የያዙትን መስቀል በቀኝ እጃቸው ወጣ አድርገው በሹክሹክታ የማይሰማ አባባላቸውን አነበነቡና አሳልመው « እግዚአብሔር ይፍታ » አሉ ።

« የእጅ ውሃ አምጡ ፤ አባ ወዲህ ይቅረቡ ቁርስ እናድርግ ። ገና አሁን መግባቱ ነው » አሉአቸው ።

አባ ወደገበታው ጠጋ ብለው በተጋበዙበት ወንበር ላይ ተቀምጠው « በስመአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ » በማለት እጃቸውን ታጥበው መብላት ጀመሩ ። ፊት ለፊታቸው የተቀመጡት ወ/ሮ አባይነሽ « ቡናውን ቶሎ ቶሎ በሉ » በማለት ትዕዛዝ ሰጥተው መመገቡን ተያያዙት ። ወደ ዋናው ውይይት ሳይገቡ በአጠቃላይ ሁኔታ ላይ ሲጨዋወቱ ቆይተው ማዕድ ሲነሳ ሲል የነፍስ አባታቸው ተነሱና የገበታ ማሳረጊያ ፀሎታቸውን አሰሙ ። በክፍሉ ውስጥ የሦስተኛ ሰው መኖርን ያልፈለጉት ወ/ሮ አባይነሽ ቡና ተፈልቶ እስካለቀ ድረስ ዋናውን ቁም ነገር አልጀመሩም ነበር ።

« በይ እንግዲህ አንቺ ሂጅና ማዕድቤት ሥራ አግዥ » አሉና አሰናበቷት ምስጢር እንዳይባክን በመስጋት ። ነፃ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ፣ « አባ አሁን የጠራሁዎት ከዚህ ቀደም ስላነሳነው ጉዳይ እንደገና ላማክርዎት ነው » አሉ ።

አባም ዓይናቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ በማተኮር ግራ እንደተጋቡ ሁሉ « የትኛው ጉዳይ ? . . . በይ እንጂ » አሉ ፊታቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ አስጠግተው ።

ወ/ሮ አባይነሽ የነጠላቸውን ጫፍ በእጃቸው ያዝ አድርገው እንደመቋጨት እያፍተለተሉ « አባ መቼም ሰው ሆኖ ኖሮ ኖሮ መሞቱ አይቀርም ። ሞት ቀጠሮ አይሰጥም ። ሰው እኖራለሁ ይላል፤ ሆኖም እግዚአብሄር ሲጠራ አስቀድሞ መልዕክተኛ አይልክም። የእኔ ህይወት እንደምታውቁት መና ሆኖ ቀርቷል ። ይህን የለፋሁበትን ሀብቴን ለማንም በትኜ ብሞት አስከፊ ሞት ሞተች ይባላል ። ከፋም ለማም ያለችኝ የሥጋ ዘመዴ የእህቴ ልጅ ብቻ ነበረች ። ምንም ቢሆን ብሞት ተዝካሬን እንኳ በሚገባ ልታወጣ ትችል ነበር ። ይኸው አብሮኝ ያለውም ሰው የእኔን ሞት ከዛሬ ነገ እየጠበቀ ነው ። ስለዚህ ይቅር ብለውኝ ከእህቴ ልጅ ጋራ እንዲያስታርቁኝ ነው የምፈልገው » አሏቸው ።

« ይኸውልሽ ልጄ ፤ ከሥጋ ኖረው ሞት አይቀርም ። እንዳልሽው የማይሞተው ነፍስ ብቻ ነው ። ይሄን ካሰብሽ መልካም ነው ። እግዚአብሔር መንገዱን መርቶሻል ። ታዲያ እርቁን እውነተኛ እርቅ ለማድረግ ሊያሸንፉ የሚችሉ ሽማግሌዎች ልሰብስብና አብረን ሄደን እንማፀናታለን » ሲሉ የነፍስ አባታቸው የሌላ ሰው መኖር አስፈላጊ መሆኑን ተናገሩ ።

« የለም . . . የለም . . . ሽማግሌማ አያስፈልግም ። ሰው ሳይሰማ ተቀራርበን ሁለታችን ይቅር ለእግዜር መባባሉ ነው



የሚሻለው ። ለዚህ ደግሞ የእርስዎ ሽምግልና ይበቃል ። ወሬ ማባዛት ምን ያደርጋል ? » አሉ እጃቸውን እያወናጨፉ ።

« ይህማ ደንብም አይደል ። ሰው መኖሩ ደግ ነው ። ድንገት አሻፈረኝ ብትል እንኳ ከብዙዎቹ አንድ የሚያሸንፋት ይገኛል ፤ የሰው ብዛት አይከፋም » አሏቸው ።

« አባ ይህማ እንደው አጉል ይሆናል ። ይልቁንስ ነገ ለምሳ አብሮአት ያለውን ሰው እዚህ ድረስ ቀጥሬዋለሁ ። እርስዎም ተገኝተው ከእሱ ጋራ ብንነጋገር የእርቁን ነገር ማዘጋጀት ይቻላል » አሉ ።

« እንግዲህ በይ እንዳልሽ . . . መስሎኝ ነው » አሉ አባ ።

* * *

ሒሊና ማዕድቤት ገብታ እራት ስታዘጋጅ አጠገብዋ ዕቃ እየነካካ የሚያስቸግራት ኩቻን « አንተ መቼም ያለማጥፋት ሥራ የለህ ። አታስቀምጥም አሁን ! መጣሁብህ ! » እያለች ስትናገር ሮጦ ከማዕድቤት ወጥቶ ሜዳ ላይ ቆመ ። ኩቻን ተከትላ በር ላይ ቆማ ፣

« አታመጣም አሁን » ብላ በግሳፄ ዓይን ተመለከተችው ። እሱም እሷን እያየ « አልሰብረውም እኮ » አላት ።

« ምን ልታደርግበት ነው ? እጅህን ትቆርጣለህ ፣ አምጣ ነው የምልህ ! » በማለት ወደ ኩቻ ራመድ ስትል ኩቻ ተፈተለከ ። ሒሊናም እልህ ያዛትና ተከትላው ሮጠች ። መሀል መንገድ ላይ ስትደርስ የሆነ ነገር ባለችበት ገትሮ አስቀራት የምታውቀው የሚመስላት አፍሮ ጠይም ልጅ ተመለከተች ። በእርግጥም ታውቀው ኖሯል ። « ሰለሞን ከየት መጣህ ? » አለችውና ይዛው ወደ ቤት ገባች ።

« ጋሼ ያሬድ የለም እንዴ ? » ሲል ተናገረ ሰለሞን ። ያሬድ ጆሮውን ተከሎ ያዳምጥ ስለነበረ ከመኝታ ቤት « ማነው ? ሕሊና » ሲል ተጣራ ።

« እኔ ሰለሞን ነኝ ጋሼ ያሬድ » ሲል መለሰለት ።

« ሰለሞን ነህ ?ደህና ነህ ? ምነው በምሽት ምን አጋጠመህ?» በማለት በበሩ በኩል ብቅ አለ ።

« ፈልጌህ ነበር ጋሼ ያሬድ » አለ ሰለሞን ። ሕሊና ነፃነት ልትሰጣቸው ስለፈለገች በጓዳ በር በኩል ወጣች ።

« ምን አስቸኳይ ጉዳይ አጋጠመህ ? ደህናም አይደለህ ? » ሲል ያሬድ ሰለሞንን ጠየቀው ።

« ደህናስ ደህና ነኝ . . . እንዲያው » እያለ ነገሩን ለመናገር በማመንታት ትንሽ አቅማማ ። « እማማ አባይነሽ ወደ አንተ ጋ ልከውኝ ነው የመጣሁት » አለ ። ያሬድ የሰማውን ባለማመን ፤

« አባይነሽ ? አባይነሽ የሕሊና አክስት ? » ሲል በማረጋገጥ ዓይነት ጠየቀው ።

« አዎ የሕሊና አክስት ። መቼም አዲስ ነገር ነው ። ይኸውልህ ዛሬ አስጠርተው ነገ ለምሳ እንዲመጣ ንገረው አሉኝ ። እኔ እንኳን ዝም ብዬ አልመጣም አለኝ ልላቸው ነበር ። በኋላ በሌላ ሰው አስጠይቀው ደግሞ ቢታወቅ ብዬ ነው የመጣሁት » አለ ሰለሞን።

« ምን ፍጠር ነው የሚሉኝ ደግሞ ? » ሲል ግራ በተጋባ ሁኔታ ጠየቀው ።

« እኔ እንጃ ግን በጣም ነው የሚፈልጉህ »

« ለሠላም ነው ለፀብ ? እንዲህ አጣዳፊ የሆነ ጥሪ ። በእርግጥ ያሬድ ብለው ነው የነገሩህ ? » በጥርጣሬ ዓይነት ጠየቀ ።

አዎ ያሬድ ብለው ነው ። ጠዋት ከሕሊና ጋራ ስትሄዱ አይተዋችሁ ነበር ። ከቤተክርስቲያን መልስ እንደመጡ አስጠርተው



ሕሊናን አይቻት አውቅ እንደሆን ጠየቁኝ ። እኔም እንደልማዳቸው አሰናቀን ስደባት ብለው እንደሚልኩት ሁሉ እኔንም ሊልኩኝ ነው ብዬ አውቄ ብዙ ጊዜዬ ነው ካየኋት አልኳቸው ። በኋላማ ዕንባ እየተናነቃቸው አንተን እንድጠራሁ የመለመን ያህል ነበር የነገሩኝ » አለ ሰለሞን ።

« ለመሆኑ ጥሪው በስንት ሰዓት ነው ? » ሲል ጠየቀው ።

« የተወሰነ ጊዜ እንኳን አልተናገሩም ። ሆኖም በምሳ ሰዓት ማለታቸውን አውቃለሁ ። » በማለት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ « እየመሸ ነው ፤ ጋሼ ያሬድ ልሂድ » አለ ። ያሬድም እተቀመጠበት ቦታ ሆኖ « ሕሊና . . . ሕሊና . . . » ሲል ተጣራና መልስ ሲያገኝ « ሰለሞን ደህና እደሪ ይልሻል » አላት ። ሕሊና ከማዕድቤት ተጣድፋ ወጣችና « ምነው ሰለሞን አትጫወትም ? ሥራ ይገፍ ነው እኮ ያላጫወትኩህ » አለችው ።

« የለም መሽቷል ፤ ሌላ ጊዜ መጥቼ እጫወታለሁ » ብሎ ያሬድን ጨብጦ ወደ በሩ አመራ ።

« በል እናትህን ሠላም በልልኝ ፤ ሌሎቹንም በሙሉ » ስትል ተሰናበተችው ።

« በል እንግዲህ እንዳትረሳ ! እምክራለሁ ነው ያልኩህ ድንገት ሥራ ሊያጋጥመኝ ይችላል » አለው ያሬድም ።

እራት ቀርቧል ። ሕሊና የመጨረሻ ፈተናዋ ስለነበረው ስለ እጅሥራ ትምህርት ከባድነት ለያሬድ በማስረዳት ላይ ነበረች ። ያሬድም ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ጥሪ በማሰላሰል ላይ ስለነበር ምን እንዳለችው በቅጡ አላዳመጣትም ሕሊና ቀና ብላ ያሬድን ስታየው ሀሳብ ውስጥ መግባቱን ተመልክታ ብቻዋን የምታወራ እብድ የሆነች መሰላትና ደነገጠች ።

« ምነው ያሬድ አትበላም እንዴ ? » አለችው ሳይደነግጥ ከሄደበት እንዲመለስ አስባ ።

« እንደዛሬም ጠግቤ አላውቅ » አላት ፈገግ ብሉ « ባይገርምሽ ሀሳብ ውስጥ ገብቼ ብዙ ሳልበላ አልቀረሁም » ሲል አከለ ::

« ምን እያሰብክ ነው የምትበላው ? ወጡ አልጣፈጠህም እንዴ ? » ብላ ምላስዋን በማጣጣም ዓይነት ድምፅ እያሰማች የወጡን መጣፈጥ ሞከረችው ::

« ያንቺ እጅ የነካው ምን ይወጣለታል :: ወጡስ ይጣፍጣል:: ሀሳቡ ግን ወዲህ ነው » አላት :: « በል ነገሩን ብቻህን አትበላው ባይሆን አካፍለኝ » አለችው ::

« ሕሊና . . . አክስትሽ እኮ ለነገ ምሳ ጋበዙኝ :: » አላት እንደድንገት ::

« አልገባኝም ፤ የምን ምሳ ? ለምን ? » ብላ ጠየቀችው በድንጋጤ ::

« አይዞሽ አትደንግጪ. ሕሊና ለክፉ አሳልፌ አልሰጥሽም :: ለሰሞን የመጣው ይህንኑ ተልኮ ሊነግረኝ ነበር :: ነገር ግን የምሳውን ዓይነትና ለምን ? የሚለውን ጥያቄ ስሄድ አውቀዋለሁ :: » በማለት ፈገግ አለና መለሰላት :: « መሄድስ አትሄድም :: እሳቸው እንደሆኑ ለማንም አይመለሱም ድንገት . . . » በማለት የጀመረችውን ሳትጨርስ ሳግ አነቃት :: እንደምንም እንባዋን ተቆጣጥራ « እባክህ አልሄድም በለኝ ! ጋሼ ያሬድ አልሄድም በለኝ » ስትል የግድ ተነፈሰች ::

« ሕሊና ሕፃን አትሁኚ :: የሚሉትን ማወቁ አይከፋም :: ለማድረግ ያሰቡት ነገር ካለ መቼም ቢሆን ሊሆንላቸው አይችልም :: በዚህ ላይ ብቻዬን አልሄድም :: ከተሾመ ጋር ነው የምሄደው » በማለት የሕሊናን ዓይን በአንክሮ አስተዋለ ::

« እኔ ፈርቻለሁ አትሂድ ነው የምልህ ::አልሄድም በለኝ :: »

« ምን እሆናለሁ ብለሽ ነው ? እንዲያው ቀን በቀን ጠርተው



እያስደበድቡኝ :: ቢሆንም ደግሞ ተሾመ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች እያንዳንዳቸውን ያውቃቸዋል :: » በማለት ለማሳመን ሞከረ ::

« መርዝ ያበሉሃል :: እሳቸው ግድ የላቸውም ፤ ለሰው ነፍስ አይሳሱም :: በሆነ ነገር ነው ለግድያ የሚዘጋጁት » በማለት በዕንባ በታጀበ ቃል እንዳይሄድ ተማፀነችው :: ያሬድ ዱብ ዱብ እያለ የሚወርደው እንባዋ የመንፈስ ጭንቀት ፈጠረበት :: ተነስቶ ፀጉሯን እያሻሸ « አይዞሽ በቃ አልሄድም :: ለምን ታለቅሻለሽ ? አልሄድም አልኩኮ » ሲል ማባበል ጀመረ :: ለያሬድ የሕሊናን ፀጉር መነካካት ከበረዶ የወጣን እጅ የሞቀ ውሃ ውስጥ እንደመከተት ያህል ነበር የተሰማው ::

« እውነትህን ነው » አለች ሕሊና ቀና ብላ እያየችው :: በፈገግታ ደምቃ ታየችው :: ውስጡ ተረበሸ ::

* * *

ትዕግሥታቸው አልቋል :: ሰለሞን የቁራ መላክተኛ ሆኖ ቀርቷል :: የማይፈልጉትን ሁኔታ ላለመቀበል ብቻ « ትዕግስት » ይላሉ ለራሳቸው :: እንዲያም ሆኖ ዓይናቸው ደጋግሞ ወደጓሮ በር ይወረወራል :: ቢያንስ በሰለሞን ላይ ተስፋ አልቆረጠም :: በተዘበራረቀ ስሜት ውስጥ እንዳሉ ከሰለሞን ጋር ተገናኙ ::

« ነገርከው ? » አሉት በጉጉት ::

« አዎን ነግሬዋለሁ :: እሞክራለሁ ግን ከመጣሁ ከሰው ጋር ነው ብሏል » አላቸው ::

« የምን ሰው ነው ደግሞ ? » በማለት ፊታቸውን በማኮማተር ጠየቁት ::

« ለእኔ አልነገረኝም ፤ ብቻ ይህንኑ ንገራቸው ነው ያለኝ :: »

« ሕሊና ነበረች ? » ሲሉ ጠየቁት ::

« መኖሩን ነበረች ። ነገር ግን እሷ አልለማችም ። ሁለታችን ብቻ ስንሆን ነው የነገርኩት » በማለት አስረዳቸው ። ሆኖም የመልዕክቱን ውጤት በጥርጣሬ ነበር የተቀበሉት ። ያሬድ « እሞክራለሁ » ብሎ መመለስ አልመጣም ማለቱ እንደሆነ አድርገው ገመቱት ። ቢሆንም ተስፋ ለመቁረጥ አልደፈሩም ። በመኝታቸው ላይ ሆነው እንደሚሳካ ወስደው ከራሳቸው ጋር መከሩበት ። አጋጣሚው ለህይወታቸው ወሳኝ ነው ። ከሕሊና ጋር መታረቅ ከፈሩቅ የተንኮል ወጥመድ ነፃ መሆን እንደሆነ ካመኑ ቆይተዋል ። ስለዚህ ማንኛውንም መስዋዕትነት በመክፈል የሕሊናን ይቅር ባይነት ለማግኘት መሞከር ምርጫ የሌለው ጉዳይ ነው ። አንድ ጊዜ እርቁ ይስመር እንጂ የዘመድን ጥቅም አውቀው ስለመቀበላቸው ከእንግዲህ ያውቁበታል ።

ነገን በተስፋ ተሞልተው እያሰላሰሉ ጠዋት ማልደው ተነሱ ። የትልቁን ቤት ዝግጅታቸውን ገና በማለዳው ጀመሩት ። ተሠርቶ የማያውቅ ዓይነት ወጥ በልዩ ትዕዛዝ በእሳቸው በራሳቸው ተመልካችነት ተሰራ ። ሳሎን ቤትም ተነጥፈው የማያውቁ ምንጣፎች ፣ የከት ጌጣጌጦች በየጠረጴዛውና በየወለሉ ላይ ተቀመጡ። እሳቸው ራሳቸው ምርጥ የአበሻ ቀሚሳቸውን ፣ በአንገታቸው ላይ ትልቁን የወርቅ ሀብል አጥልቀው ፣ በጣታቸው ልክ ቀለበት አድርገው ላያቸው በሰውነታቸው ሀብታቸውን ለማሳየት የተዘጋጁ ይመስላሉ ። የቤቱንና የራሳቸውን ዝግጅት ከጨረሱ በኋላ የዋናውን ቤት ፊት ለፊት በር ከፍተው ሳሎን ባለው የፎቴ ወንበር ላይ ተቀምጠው እንግዳቸውን መጠባበቅ ጀመሩ ።

« እንደምንዋላችሁ ? » ሲሉ የነፍስ አባታቸው በዋናው በር ሲገቡ ብድግ ብለው የተለመደውን ሥነ-ሥርዓት በመፈፀም ተቀበሏቸው ።



« የምሳ ሠዓት አልፏል ። ግን የሚጠበቀው እንግዳ እስካሁን ብቅ አላለም ። » አሉ በጥርጣሬ መንፈስ ። የነፍስ አባታቸው መምጣታቸው ትንሽ ፋታ ሰጥቷቸዋል ። ሰለሞን ከግቢ ውጪ በበሩ አካባቢ እየተንጎራደደ መንገድ መንገዱን በመቃኘት እንግዳውን ጠበቀ:: ወ/ሮ አባይነሽ አልፎ አልፎ ወደ ትልቁ በር ብቅ እያሉ « አልመጣም ? » ሲሉ እየጠየቁ ይገባሉ ።

ያሬድና ተሾመ ከሩቅ ሲመጡ ታዩ ። ሰለሞን በሮ ሄዶ « እማማ አባይነሽ እየመጡ ነው ! » አለ ።

« በል ፍጠን ሰለሞን ፤ ቶሎ አስገባቸው » አሉ እየተጣደፉ:: ያሬድና ተሾመ ወደ ሳሎን ገብተው ፎቴ ወንበር ላይ ተቀመጡ ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ « ምሳ ይቅረብ ወይንስ ማባያ የሚሆን ምን መጠጥ ይምጣላችሁ ? » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ ደስታ እየተለማቸው ።

ያሬድ ከነሱ ራቅ ወዳሉት ቄስ ዓይኑን ተክሎ « እኔ እንኳን ምሳ ሌላ ሰው ጋብዞኝ አሁን በልቼ ነው የመጣሁት » አለና ወደ ተሾመ ተመለከተ ።

« ምሳማ እስከአሁን ማን ይጠብቃል ? ባይሆን እንኳን ወንድ ልጅና አትክልት ከወደ ውሀው ነው ይባላል » አለ ተሾመ ። ሁሉም ሳቁ ። ቄሱም « ልክ ነው » በሚል ዓይነት ራሳቸውን ነቀነቁ ። ወ/ሮ አባይነሽ ዝግጅታቸው መና እንዳይቀር ምግብ ለማቅረብ ብዙ ታገሉ ። ማንንም ማሳመን አልቻሉም ። ወደ መጠጡ ተመለሱ ። የተሾመንና የያሬድን ምርጫ ጠየቁ ።

« እኔ ቢራ ይሻለኛል » አለ ያሬድ ። ተሾመም ቢራ መረጠ:: ወ/ሮ አባይነሽ ቢራ ከፍሪጅ አውጥተው ከንፁህ ብርጭቆ ጋር አቀረቡላቸው ። ተሾመ ቢራውን አጋባ ። ያሬድ ግን የጠርሙሱን አፍ በግራ እጁ ጠረግ ጠረግ አድርጎ አስቀመጠው ።

« መቼም ለቁስ ቢራ አይታዘዝለትም ፤ በይ ለእኔ ከዚያ ከነጮ ነገር አምጪልኝ» አሉ ቁሉ ። ወ/ሮ አባይነሽ ለነፍስ አባታቸው መጠጥ እያቀረቡ ፤

« ምነው ከሰሞኑ የት ሄደህ ነበር ጠፋህሳ ? » ሲሉ ተሽመን ጠየቁ ።

« አይ እትዬ ሁልጊዜ ይደላል ብለው ነው ? ከሰሞኑ እንኳን በሥራ ብዛት ነው ለመምጣት ያልቻልኩት » በማለት እየተቁነጠነጠ መለሰላቸው ። ያሬድ የቤቱን ሁኔታ ከወ/ሮ አባይነሽ የሰውነት ይዘት ጋር በማነፃፀር በሀሳብ ተጠምዶ ነበር ።

« ይህ ሁሉ ሀብት በስንቱ ላብ የተገነባ ነው ። በከተማ በንግዱ በኩል ወሳን የሌለው ትርፍ በማግበስበስ በሌላ በኩል ደግሞ ከገጠር አርሶ አደሩን የላቡን ውጤት ምርት በመንጠቅ የግል ኑሮአቸውን እንደዚህ አሳምረው ይኖራሉ ። ግን ምን ያህል ስግብግብ ናቸው የአንድ እህታቸውን የሥጋ ቁራጭ የሆነችውን ልጃቸውን አስተምረው ለቁም ነገር ለማድረስ ያልፈለጉት ? ሲሞቱ እኚህ ግዙፍ ሴት የሚኖራቸው ሀብት እንደ የእንጨት ሳጥንና ግፋ ቢል ሁለት ሜትር ስፋት ያለው ጉድጓድ ነው ። ምን አለበት የወደፊቱን ኑሮአቸውን ሲያስቡ ሞትም በመንገዳቸው እንዳለ ቢገነዘቡ ? አይ ስግብግብነት ! ስግብግብነት መሀፀኑ ለፊ ነው ። በቃኝን አያውቅም » እያለ ከራሱ ጋር ይጫዋወት ነበር ።

ወ/ሮ አባይነሽ እየተቁነጠነጡ እጃቸውን ግራና ቀኝ ባለው ፎቴ ወንበር ላይ አሳርፈው ፤ « በሉ እንግዲህ አባ ወደ ቁም ነገሩ ብንግባ አይሻልም ? » በማለት የነፍስ አባታቸውን ለውይይቱ ጋበዟቸው ። አባም ከመቀመጫቸው ብድግ ሲሉ ሌሎቹም አብረው ተነሱ ። አባ ቃለ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ፤

« እግዚአብሄር ይፍታህ » አሉና ተቀመጡ ። በፊታቸው ላይ ብርር ያለውን ጊማቸውን በእጃቸው እየጠመለሉ ዓይኖቻቸውን



ከወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሁለቱ ወንዶች እየወረወሩ ፤ « እንግዲህ ሰው ሆኖ የማይጣላ የለም ፤ ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት እንዳለ ሁሉ ወ/ሮ አባይነሽ ከልጇ ከሕሊና ጋር በስህተት በመጣላትዋ ከቤቷ ወጥታ እንድትኮበልል ሆናለች ። ታዲያ እናትና ልጅ እስከመቼ ተለያይተው ይኖራሉ ? ይህን እግዚአብሔርም አይወደውም። ስለዚህ ዛሬ እነኚህ ሁለት ሰዎች እንዲታረቁ ነው እዚህ እንድንገናኝ የተደረገው ። » አሉና ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ፊታቸውን መልሰው « አይደለ እንዴ ? » ብለው ጠየቁ ።

ስለጉዳዩ ለመናገር የተርበተበቱት ወ/ሮ አባይነሽም ወደ ያሬድ እያዩ « ለአባት ለእናታችን እኔና ወርቂቱ የሕሊና እናት ብቻ ነበርን። የሕሊና እናት ታናሽ ነች ። እናትና አባታችን በተከታታይ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የሕሊናን እናት ከሀገር ቤት ያስወጣኋት እኔ ነኝ። እዚሁ ቤት ከሕሊና አባት ጋር ይተያዩና ይለራረቃሉ ። ይህችው ሕሊና ሆድዋ ትቀራለች ። እናቷ ለኔ ምንም ሳትነግረኝ ከሕሊና አባት ጋር ኮብልላ ጠፋችብኝ ። እህቴን ይዞ ከሀገር ከጠፋ በኋላ በሽማግሌ ሊታረቁ መፈለጋቸውን ብዙ ጊዜ ገልጸውልኝ ነበር ። ሆኖም በጊዜው በጣም በመናደዱ ሽማግሌዎችንም መቀበል አልቻልኩም ። ከዚያም ትንሽ ቆየት እንዳልኩ ሕሊና ተወለደች አሉ። ሁለት ዓመት እንደሞላትም እናትዋ ሞተችባት ። መርዶዬን ተረዳሁት ። ሕሊናን የት እንዳለች ባፈላልግ አባትየው ያለበት ቦታ በመሰወሩ ለማግኘት አልቻልኩም ። ከዚያ እንግዲህ አባትዋ ሲሞት ሕሊና እሱ በነገራት አድራሻ ወደዚህ መጣች ። እናትዋን ሳልድራት ከቤት ኮብልላ ቀረች ። አሁን ደግሞ ልጅቱ . . . » በማለት ወደ ያሬድ ዓይናቸውን በመትከል ፤ « እንደ እናትዋ ከቤት ወጥታ ቀረች ልጆ » ብለው እጃቸውን ወደ ደረታቸው ጨብጠው አስቀሩ ።

« እኔ መሀን ነኝ የእህቴን ልጅ በሠርግ ደግሼ ለመዳር የነበረኝን ፍላጎት መቼም ለእናንተ አላወራውም ። ግን ምን ያደርጋል

እሁንም የልጅነት ፀባይ ይዟት እኔን ለማየት አትፈልግ ይሆናል ። ለዚህ ነው እናንተን በአማላጅነት እንድታስታርቁኝ ዛሬ እዚህ የጠራኋችሁ » ብለው ለተሰበሰቡት ሰዎች ሳይሆን ለራሳቸው ዕንባቸው ዓይናቸው ላይ እያቀረረ « ምነው ከዚህ ሁሉ የራሴ ነው የምለው አንድ ልጅ ቢኖረኝ አይ አንተ አምላክ ፍረደዋ ! » በማለት እጃቸውን ወደ ሠማይ በመዘርጋት ወደ ላይ አንጋጠው ጣሪያውን ተመለከቱ ። የነፍስ አባታቸው « መቼም ኖረው ኖረው ከመሬት፤ ዞረው ዞረው ከቤት እንደሚባለው ሁሉ » ሲሉ ቀኝ እጃቸውን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘርግተው « ከእንግዲህ ይህች ሰው ቆርባ መኖሪያዋ ነው ። የለፋችበት ሀብት ሜዳ ላይ ተበትኖ እዳይቀር ይህችን ልጅ በምክንያት እግዚአብሄር በደግነቱ ሰጥቷታል ። ታዲያ የእነሱ መጣላት ለምኑ ነው ። ግድ የሰም ይሁን ልጅቱ በገዛ ፈቃድዋ ቤቷን መርጣለች . . . ማለፊያ ነው ። መቼም ዘመኑ ያመጣው ስለሆነ ይቅር ብለን መቀበል አለብን ። ይሁንና ለልጅቱም ቢሆን ኑሮዋ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለውና ደስተኛ እንድትሆን የእናትዋ ምርቃት አስፈላጊ ነው ። ታዲያ በወግ በማዕረጉ በሠርግ ከቤትዋ ብትወጣ ምን ይከፋል ?» በማለት ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ያሬድን ለሕሊና እንደ ባል በመቁጠር ነበር ።

ያሬድ ሁለቱ የሚናገሩትን አዳመጠ ። ብዙ ግልፅ ያልሆኑለት ጉዳዮች ስለነበሩ ለመቸኮል አልፈለገም ። ጆሮዎቹን ቀስሮ ለማዳመጥ ቅድሚያ ሰጠ ። ተሾመም በጉዳዩ ላይ ከያሬድ በላይ አልነበረም ።

ወ/ሮ አባይነሽ ይህ ግንኙነት በወደፊት ህይወታቸው ላይ ያለውን ወሳኝነት በመገመት እነያሬድ እንዲያዝኑላቸው ገለፃቸውን በለቅሶ ቀጠሉ ።

« ሕሊና ገና እዚህ ቤት ስትመጣ የእህቴ የወርቂቱ ምስል በመሆንዋ እራስዋ ወርቂቱ በህይወት ተመልሳ የመጣች ነበር የመሰለኝ ። ግን ምን ያደርጋል ከአባትዋ ጋር ስትኖር የወረሰችው



ፀባይ ልግመኛ አድርጓታል ። የምለውን አትሰማም ፤ እንደመጣች እዚህ አብራኝ የምትኖር አንድ ሴት ነበረች ። ከእሷ ጋር ገጠሙ ። ከዚያ በኋላ ነው እኔን ዓይንሽን ላፈር ብላ የጠላችኝ ። ያው ያቺም የነገር ቋት የማትለው የላትም በመጨረሻ በስካር እራስዋን ስታ ተሰቅላ ሞታ ተገኘች ። አይ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ ! » በማለት ወደ ኮርኒስ በዓይናቸው እየተመለከቱ ።

« እሷም የዘመድ ልጅ ነበረች ፤ አይ አስካበች . . . » ብለው ዕንባቸውን ማንባት ሲጀምሩ የነፍስ አባታቸው ተቆጡ ።

« የሙት ስም አታንሺ ! እግዚአብሄር ይቅር ይበልሽ ! ኧረ ነውርም አይደል ። ካለፈ በኋላ ነፍሷን ይማር ይባላል እንጂ » በማለት ወደነያሬድ እየተመለከቱ « በሉ ልጆቼ አይከፋችሁም መቼም ልጆቼ ብላችሁ ይሄን መሳይ ጉድ ነው ይህች ሴት ተሸክማ ያለችው። እግዚአብሄር ይቅር ይበላችሁ ይቅር በሏትና የጠየቀችውን ፈጽሙላት» በማለት ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው እጃቸውን ወደ እነያሬድ ዘረጉ ፤ በልመና ዓይነት ።

ያሬድም ቄሱ በአዛውንትነታቸው መከበር እንዳለባቸው ስላመነ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ « ኧረባክዎ አባባ ተቀመጡና እንነጋገር » አላቸው ፤ ቶሎ ይቅርታ ለማድረግ ባልፈለገ አቀራረብ ።

« ይቅርታ ሳላገኝ እንዴት ልቀመጥ ? ይቅርታህን ስጠኝና ልቀመጥ » በማለት እንደቆሙ ቀሩ ።

« ነገሩ ወዲህ ነው ። ይቅርታ ለማድረግም ላለማድረግም እርሶ ይቀመጡ » በማለት ወደ አባ ቀረብ ብሎ በእጁ እጃቸውን ይዞ እንዲቀመጡ አደረገና እርሱም ተመልሶ ተቀመጠ ።

ያሬድ ወ/ሮ አባይነሽንና የነፍስ አባታቸውን ከአንዱ ወደሌላው በማቀያየር እያየ « ይቅርታ ለማድረግ እኔ ብቻ ብቁ አይደለሁም ። ጉዳዩ እንዲያውም እኔን አይመለከተኝም ። ተበደልኩ ባይ እኔ ባለመሆኔ የእኔ ይቅር ባይነት ያለቦታው ይሆናል። እኔም

ከእርሶ ጋር ትውውቅም ቂምም የለኝም ፡፡ ግን በእናንተ አስተሳሰብ የተሳሳተ አባባል አለ ፡፡

ሕሊና ለእኔ ሚስቴ አይደለችም ፡፡ በቅድሚያ ይህን ልታውቁልኝ ይገባል ፡፡ በመካከላችን ምንም ዓይነት ግንኙነት አልፈጠርንም ፡፡ ስለመመለስና ስለ ሠርጉ ጉዳይ እንግዲህ ወሳኝዋ እራሷ ባለቤቷ ነች፡፡ የእርስዎም የእማማም አባባል ከልብ ገብቶኛል፡፡

ሆኖም በእኔ በኩል ልፈፅመው የምችለው ነገር ቢኖር ይህንኑ መልዕክት ለእሷ ማድረስ ነው ፡፡ አይመስላችሁም ? » በማለት ለወ/ሮ አባይነሽና ለአባ ጥያቄ አቀረበ ፡፡

« ጎሽ እግዚአብሔር ይባርክህ፤ የአዋቂ አነጋገር ነው የተናገርከው ፡፡ መቼም ስለሁሉም ነገር እናንተ ታውቃላችሁ ፡፡ ሰው ግን የሚያወራው አግብታ እየተማረች ነው እያለ ነው ፤ ካልሆነም ማለፊያ . . . » አሉና ወ/ሮ አባይነሽን ተመለከቱ ፡፡

« መቼም መጋባቱ በመንገዱ ቢሆን ነውርም የለው ፡፡ እኔም አባ እንዳሉት ሰው መቼም ወሬኛ ነው ያላየውን በይሆናል ያወራል ፡፡ ግን ካልሆነም በሀሳብ የተዛመዱ ሰዎች ኖረው ኖረው በሥጋ መዋሃዳቸው አይቀርም » በማለት ያሬድን በፈገግታ አስተዋሉት ፡፡

ተሾመ ጣልቃ ገባ ፡፡ « እንዲያው በማታውቀው ነገር ገባህ ባትሉኝ በዚህ ንግግር የሚጎለን ሁለቱን ተበዳይ ነን ባይዎች አቀራርቦ ማነጋገርና የበደሉን መጠን አመዛዝኖ በዳይ ተበዳይን እንዲክስ አድርጎ ማስታረቅ ነው ፡፡ ታዲያ ይህም የመጀመሪያ ግንኙነት ስለሆነ አይከፋም ፡፡ ለዋናው መነሻ ሊሆን ይችላል ፡፡ ስለዚህ የሚቀጥለው ግኑኝነታችሁን የምታደርጉበት ቀን ቀጠሮ ወስኑና ያሬድም ሕሊናን ያነጋግር ፤ እናንተም እንግዲህ ወ/ሮ አባይነሽ ዝርዝር ሁኔታውን አስበውበት መዘጋጀት ይሻላል » በማለት ሀሳብ አቀረበ ፡፡



« ይባርክህ ማለፊያ ፤ ህሳብ ነው ያቀረብከው ፡፡ እንግዲህ ወ/ሮ አባይነሽም የሚመችሽን ቀን እናንተም የሚመቻችሁን ቀን ወስኑልኝና በዚሁ እንለያይ » አሉ የነፍስ አባታቸው ፡፡

ወ/ሮ አባይነሽ በራሳቸው መንገድ ቀጠሮውን ሊያደርጉ ብዙ ቢታገሉም ያሬድ ከሳምንት እሁድ ውጪ አይመቸኝም ስላለ በዚሁ ተስማሙ ፡፡ ቀጠሮው ከተያዘ በኋላ ያሬድ ወደ ቤቱ ለመመለስ ከተቀመጠበት ተነሳ ፡፡ ወ/ሮ አባይነሽ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሲለምኑት ተቀመጠ ፡፡ አንድ ሌላ ቢራ እንዲደግም አስገደዱት ፤ እና ተቀበለ ፡፡ ባልታወቀ ሁኔታ ከመጠጡ ጋር ጨዋታ ተጀመረ ፡፡ አልኮልዋ የሰራች መሰለች ፡፡ ወ/ሮ አባይነሽና ያሬድ አፍ ለአፍ ገጥመው መጨዋወት ጀመሩ ፡፡ በዚህ መሀል ወ/ሮ አባይነሽ ተቆርቋሪነታቸውንና ስለ ሕሊና በቅርብ መከታተላቸውን ለማረጋገጥ አንድ የሚያውቋትን የግዛ ምስጢራቸውን ለያሬድ ተነፈሱ ፡፡

« ባለፈው ጊዜ ማን ነበር እሱ ? ሕሊና አዲስ እንደመጣች ቤታችሁ ተሰብሮ ነበር ብሎ ነገረኝ ፡፡ መቼም በጣም ነበር የደነገጥኩት ፡፡ እንዲያው እዚህ ሀገር እኮ የዚህ የፋብሪካ የቀን ሠራተኞች ሥራ ሲፈቱ ማታ ማታ የሚያደርጋቸውን ነው የሚያሳጣቸው » በማለት እንደተቆረቆረ ሁሉ ጉዳዩን ለመስማት በመጓጓት ያሬድን ተጠጉት ፡፡ « አይ እሱማ ያለ ነው ፡፡ ግን እኮ የሚገርመው ምንም ነገር ሳይወስዱ በሩን ሰብረው ትተው ነው የሄዱት ፡፡ ለእነሱ የሚጠቅም ሳህን ፣ ማንኪያ ፣ ሹካ እያለ አንዱንም ነገር ሳያነሱ መውጣታቸው በጣሙን ነው የገረመኝ » ሲል ተናገረ በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከታቸው ፡፡ የወ/ሮ አባይነሽ የፊት ቀለም ሲቀያየር አስተዋለ ፣ የታችኛው ከንፈራቸው የሚናገሩትን ሳይሆን የደበቁትን ለመናገር ትግል አደረገ ፡፡ ሆኖም እንደምንም ብለው እንደበታቸውን ገቱት ፡፡

« ልክስክስ ሌባ ነው ። እንዲያው አንድም ነገር ሳያነሳ ሄደ በሞቴ ? » አሉ ። « ምንም የተነሳ የለም ። በቤቱ ውስጥ የተቀመጠው ዕቃ እንኳን ቦታውን አለወጠም ። እንዳለ አገኘነው » አሉቸው ።

ለወ/ሮ አባይነሽ ይህ በቂ ነበር ። ቀደም ብሎም ስርቆቱ ምንም ኮሽታና ጩኸት ወይም ጋጋታ ሳይሰማ መፈጸሙ የድርጊቱን ምንነት ምልክት አጠራጣሪ አድርጎባቸው ነበር ። አንድ ነገር የጎደለ መሆኑን ሰውነታቸው ነግሮአቸው ነበር ። ግን ማንን ይጠይቁ ? ምስጢሩ ምስጢር ሆኖባቸው እንዲሁ እንደቀፈፋቸው ነበሩ ። አጋጣሚውን ተጠቀሙበት ። ጥርጣሬአቸው ልክ ነበር ። ግን ጭንቅላታቸው ሊቀበለው የሚፈልገው እውነት አልነበረም ። ሠማይ ምድሩ ዞረባቸው ። ሰውነታቸው የሚፋጅ ላብ መትፋት ጀመረ ። ውስጣቸው ተቃጠለ ። ትንፋሻቸው ፍጥነቱን ጨመረ ። ያሬድ ፊት ለፊት እያያቸው ከተቀመጡበት ሸርተት ብለው ፎቴው ላይ ተዘረጉ። ያሬድ የሚያየው ሁሉ ህልም መሰለው ። የማያውቀው ድንገተኛ ድንጋጤ ወረረው ።

« ምነው እመመዎት እንጄ ? » አለ ።

« ውኃ ፣ እባካችሁ ውኃ አምጡ » ሲሉ ጮኹ የነፍስ አባታቸው ።



* * *

ያሬድና ተሾመ በገጠማቸው ሁኔታ ተደናግጠው ከግቢው አጥር በር እንደወጡ ያመሩት ወደ ወንድማማቾች ቡና ቤት ነበር ። ያሬድ የወ/ሮ አባይነሽ ሁኔታ በጣም አሳዝኖታል ። ሲያስመስሉ እንዳልሆነ ከሁኔታቸው ተረድቷል ። ያ ሁሉ ላብ ያለአንዳች ምክንያት ሲመነጭ እንዳልቻለ ተገንዝቧል ። ያነቡት ዕንባ የዋዛ አልነበረም ። « ሴትየዋን ምን ነካቸው ? በጤና ሲያነጋግሩን ቆይተው ከመቅስፈት የተለዋወጡት ? » ሲል ተሾመን ጠየቀው ።

ተሾመም ከያሬድ የተለየ ህሳብ አልነበረውም ። ለወ/ሮ አባይነሽ ከልብ አዝኖላቸው ነበር ። « በሠሩት ኃጢያት ተፀፅተው ይሆናል ። በሰው ላይ ክፉ ነገር መሥራት መጥፎ ነው ። የመንፈስ ጭንቀት ተገዥ ያደርጋል » ሲል መለሰለት ።

« በህይወት ይኖራሉ ብለህ ነው ? የዚህ ዓይነት በሽታ ያለበት ሰው ዕድሜው አጭር ነው » አለ በምሬት ።

« ምን ይሆናሉ ብለህ ነው ? ለእኛ አዲስ ነገር ሆነ እንጂ የተዋሃዳቸው በሽታ ይመስለኛል » እየተባባሉ ወንድማማቾች ቡና ቤት በራፍ ደረሱ ። ከመግባታቸው በፊት ውጪ ትንሽ ቆም አሉና ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ ። ጥግ ይዘው ቢራ አዘዙ ። ሳያስቡት ጀምረውት ወደነበረው ውይይት ተመለሱ ።

« ምን ነበር የሚዘላብዱት ? ጋብቻ ፣ ሠርግ ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው ? » ሲል ያሬድ ጠየቀ ።

« ያው ነው ፤ ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ። እንግዲህ አንተንና ሒሲናን ሲያጋቧችሁ ይሆናላ » በማለት ፈገግ አለ ።

« ይቀልዳሉ ! አሁን ደርሰው ስለ ጋብቻ ምን አሳሰባቸው ? »

« ምን ግራ ይገባሃል ? አንተን የመሰለ ጥሩ አማች እንዳያመልጣቸው ብለው ነው፡፡ ያሬድ አትቀየመኝና አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ፡፡ አሁን ሕሊና ትምህርቷን ስትጨርስ ሌላ ሰው እንዲያገባት ቢጠይቅህ ትፈቅዳለህ ? » ሲል ያሳሰበውን ጥያቄ አቀረበለት ፡፡ ያሬድ እራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፣

« ምን ማለትህ ነው ? ጥያቄህ አልገባኝም » ሲል በጥሞና ተሾመን አስተዋለው ፡፡

« ስማኝ ጥሩ ምክር ልምክርህ ፡፡ ያልከውን ብትል አንተ ሕሊናን አግብተህ አብራችሁ እንደምትኖሩ አትጠራጠር ፡፡ ግን ወ/ሮ አባይነሽ ይህ የደከመ ህይወታቸው አንድ ቀን ሊሰናበት ያየኸው ሀብት ሁሉ የሕሊና ይሆናል ፡፡ ሌላ ወራሽ የላቸውም ፡፡ አሁን የተቸገሩት የመሞቻ ጊዜያቸው የተቃረበ እየመሰላቸው በህይወት ዘመናቸው ያፈሩትን ሀብት ለማንም አባክነው አሳልፈው እንዳይሰጡ ነው፡፡ አብሮአቸው ያለውም ሰው ሞታቸውን ነው የሚጠባበቅላቸው፡፡ ነገር ግን ሀብታቸው በዚህ ሰው እጅ እንዲወድቅ አይፈልጉም ፡፡ ገባህ? የዕርቁ መሠረት ይህ ነው ፡፡ የቀረውን እንግዲህ አንተ እወቅበት » አለው በተቆርቋሪነት ዓይነት ፡፡

ያሬድ በሀሳብ ማዕበል በመዋጥ በውስጡ እየተጨነቀ ተሾመን ተመለከተውና « ሰለ ጋብቻው ያልከው እንግዲህ ጊዜ ነው የሚወስነው ፡፡ ግን ሕሊና ትምህርቷን እስከምትጨርስ የዚህ ዓይነቱ ሀሳብ በእኔም በእሷም እንዲፀነስ ፍላጎቴ አይደለም ፡፡ ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ሀብት ወሳኝዋ ሕሊና ነች ፡፡ ለመታረቅ ብትፈልግ መልካም፤ ካልፈለገች ግን ይህን አድርጊ ብዬ እኔ አልገፋፋትም » በማለት የቀረበውን ጠርሙስ ቢራ ብድግ አድርጎ ጉሮሮውን እራሰ ፡፡

« ያሬድ ይህን ብታደርግ ሞኝ ነህ ፡፡ ሰው በእግር በፈረስ የሚፈልገውን ዕድል በርህን እንኳኩቶ ሲመጣ አልፈልግህም ብለህ ብትሸኘው ይህን የዋህነት እለዋለሁ እንጂ ሀቀኝነት አይደለም ፡፡



ሕሊና ምን ይወጣላታል ፡፡ በዚህ ላይ ተቀጥላ ሀብት ይዛ የምትመጣ ከሆነ ለማን ብለህ ነው አሳልፈህ ለሌላ የምትሰጣት ? እኔ አንተን ብሆን ኖሮ አሜን አማምዬ ብዬ ሕሊናን በእጅ በእግሯ ገብቼ ነበር እርቁን እንድትቀበል የማደርገው ፡፡ ብቻ . . . ተወው አንዱ ጭልፊት ይቀድምህና ሕሊናን አግብቶ በተደላደለ ኑሮ ሲዝናና ወይኔ እኔ ነበርኩ እኮ የዚህ ዕድል ባለቤት አያልክ በንዴት የሚደርቀውን ከንፈርህን ስትመጥ እንዳላይህና እንዳልስቅ » አለው ፡፡ ያሬድ ለመነሳት እየተዘጋጀ « የምትለውን ጨረስክ ? » ሲል ተሾመን ጠየቀው ፡፡

ያሬድ ወደ ቤት ሲገባ ጊዜው አልመሸም ነበር ፡፡ ሆኖም በሀሳብ እየዋለለ ወደ መኝታው አመራ ፡፡ አልጋው ላይ ልብሱን ሳያወልቅ ጋደም ብሎ ቀን ሲፈጽም የዋለውን እያንዳንዱን ቃላት በመመርመር በሀሳብ ተጓዘ ፡፡

« እውነታው ተሾመ እንዳስቀመጠው ነው ፡፡ ሕሊና ከሀብት ጋር ብትሆንም ፣ ያለሀብት ብትቀርም ለሌላ ሰው አሳልፌ ለመስጠት አልቃጣም » አለ በሀሳቡ ፡፡ « ግን እኮ ጋብቻም ቢሆን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለእኔም ሆነ ለሕሊና ያለምንም መሰናዶ መፈፀም አይቻልም ፡፡ ለሕሊና ይህን ሀሳብ ማቅረቡ ከአስተሳሰብዋ ማለትም የአባትዋ ቅሪት ከሆነው እምነቷ ጋር መቃረን መሆኑን እረዳለሁ ፡፡ እነዚህን ውስብስብ ጥያቄዎች ለመፍታት በመጀመሪያ ደረጃ መፈፀም ያለበት ሕሊና ከአክስቷ ጋር እርቅ እንድታደርግ መገፋፋት ነው ፡፡ ብቻ መታረቅ እንኳን ቀርቶ የአክስቷ ስም ሲነሳ እንደሚያንገፈግፋት አውቃለሁ ፡፡ ታዲያ በምን ዓይነት ዘዴ ነው ሕሊናን ማሳመን ቀርቶ ማነጋገርስ የሚቻለው ? » ሲል አሰበ ፡፡

ባለፈው ጊዜ በውስጣዊ ስሜቱ ተገፋፍቶ ሕሲና ወ/ሮ አባይነሽ ጋር እንዳይሄድ ስትጠይቀው እሺ አልሄድም ብሎ መስማማቱ ታሰበው ፡፡ ለዚህም « ሄጃለሁ » ማለቱ ብቻ ለሕሲና

መቀየም መሠረት ሊሆን እንደሚችል ተገነዘበ ። መቀየሟ ከሕሊና ጋር ሳይነጋገር ውሎ ማደርን እንደሚያመጣበት ገመተ ። ድንገት « አልችልም ! » ሲል ጮኸና ከአልጋው ላይ ተስፈንጥሮ ተነሳ ።

*      *      *

አብዬ ጋሻዬ የሕሊናን አድራሻ አጠያይቀው ሲደርሱበት እንደገመቱት ሕሊናን በእጃቸው ለማድረግ አልተሳካላቸውም ። መንገድ ላይ ጠብቀዋትም ሆነ ከትምህርት ቤት አስጠርተው ሊያነጋግሩዋት ሞክረው አልሆነላቸውም ። ፊት ለፊት ሲያገኟትም ቢሞክሩ ያሬድ ህልማቸውን እውን እንዲሆን አላደረገም ። ይህን ጉዳይ ከቅርብ ጓደኛቸው ከቀኛአዝማች አዲሱ ጋር ለመነጋገር የወሰኑት ብቻቸውን ሊወጡት የማይችሉት መሆኑን ከተገነዘቡት በኋላ ነበር ። ቀኛአዝማች አዲሱ እንደወትሮአቸው በአብዬ ጋሻዬ የእህል መጋዘን በረንዳ ጊዜያቸውን በሚያሳልፉበት ወቅት ነበር ሁኔታውን ከሥር ጀምረው ያወሩላቸው ።

« ጉድ ሆነሃላ ! ምነው ታዲያ እስከአሁን ደበቅከኝ ? » አሉ ቀኛአዝማች አዲሱ ፣ አብዬ ጋሻዬ የገጠማቸው ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን በሚያሳይ ፊት ። ጭንቀትና ችግራቸውን እንዴት ሊወጡት እንደሚገባቸው ሲያውጠነጥኑ ከቆዩ በኋላ አንድ ሀሳብ ድንገት ብልጭ እንዳለላቸው ወደ በረንዳው ዳር እያመሩ ፣ « መንገዱን ሁሉ አጥረህብኝ ምን ዓይነት መፍትሄ እንደማመጣ እኮ ቸገረኝ ። ብቻ አንድ ነገር ማድረግ የሚቻል ይመስለኛል » ብለው አካባቢያቸውን ግራና ቀኙን ከቃኙ በኋላ በአብዬ ጋሻዬ ጆሮ አንድ ነገር ሹክ አሏቸው።

« ይሆናል ብለህ ቀኛአዝማች ? እንዲህ ያለውን ምክር ታዲያ አደራህን በምስጢር መያዝ ይገባሃል »



« ምነውጃል ! ለእኔ ነው የምትነግረኝ ? ወንድምህን አጣኸው? በሦስት ቀን ውስጥ ውጤቱን አሳይሃለሁ » ለእኔ ተወው በሚል አመለካከት ነበር የተናገሩት ። አብዬ ጋሻዬና ቀኛአዝማች የተለመደውን የግል ወሬያቸውን ጨርሰው ተለያዩ ።

ቀኛአዝማች እንደተለዩ ያመሩት ቀጥታ የያሬድ የቅርብ ጓደኛ ተሾመ ዘወትር ወደሚገኝበት ወደ ወንድማማቾች ቡና ቤት ነበር ። ተሾመን ለመቅረብ ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም ። እንደአጋጣሚ ቢራ አዞ ይጠጣ ስለነበር የሦስቱን ቢራ ሂሳብ ከፍለው እንዲጋበዝ አደረጉት ። ሂሳቡን የከፈሉት ቀኛአዝማች መሆናቸውን እንዳወቀ በደንብ ተዋወቃቸውና ስለ ግብዣው አመስግኖ ተለያዩ ።

ማክሰኞ ዕለት ሌላ ቦታ ቆይቶ ቡና ቤቱ የደረሰው ዘግይቶ ነበር ። ቀኛአዝማች ሲጠብቁት ቆይተው ትዕግስታቸው ሊያልቅ ሲል ነበር የደረሰው ። ገና ሲገባ ብድግ ብለው ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀበሉት። አጠገባቸው ያለውን ወንበር ሳብ አድርገው እንዲቀመጥ ጋበዙት ።

« ልጅ ተሾመ እንዲያው ከሩቅ ሆኜ ሁኔታህን ስመለከት እንዲያ ሰውን ሁሉ በሳቅ ስትጨርሰው እኔም የጨዋታህን ለዛ መካፈል ፈለግኩ ። እስኪ ቀርቤው እንጨዋወት ብዬ ነው ። »

« ምናለ ታዲያ ደግ ነው ። እኔ እንኳን ጨዋታ አላውቅም ማለትም እጅግም ነኝ የጎረምሳ ጨዋታ ደግሞ . . . » ብሎ ሽምግልናቸውን ቢጠራ ስሜታቸውን ይነካል ብሎ ፈራና የፈለገውን ሳይናገር በእንጥልጥል ተወው ።

« እይ የእናንተ ነገር ፣ ማነው ሽማግሌ ያለፈ የጉርምስና ታሪኩን እንዳይለማ የከለከለው እኮ የትኛው ህግ ነው ? ይልቁንስ እኛ ከናንተ እናንተ ከእኛ የምንማማረው ብዙ ነገር አይኖርም ብለህ ነው ልጅ ተሾመ ? ይህ እንኳን የማይመስል ነገር ነው » አሉ ቀኛአዝማች አዝማሚያው ከዓላማቸው ጋር እንዳይጋጭ በመፍራት።

« እንደሱ እንኳን ማለቴ አይደለም » አለ ተሾመ ከእሳቸው ጋር በዚህ ጉዳይ መከራከሩ የትም እንደማያደርሰው በመገመት ::

ቀኝአዝማችና ተሾመ ከረጅም የመግባቢያ ንግግር በኋላ ስለ ጓደኛው ያሬድና አብራው ስለምትኖረው ስለ ሕሊና ዳር ዳር ሲሉ ቆይተው ዋናውን ጉዳይ አለስልሰው ነገሩት :: ተሾመ በቀኝአዝማች ትረካ መካከል የአብዬ ጋሻዬን ስም ሲሰማ ከዚህ በፊት በወ/ሮ አባይነሽ ቤት በተደጋጋሚ ለሕሊና ያላቸውን አመለካከት ከአሁኑ ሁኔታ ጋር ሲያገናዝብ የሰማው ነገር ይህን ያህል ባያስደንቀውም ስሜቱ ረግብ ሲልለት አብዬ ጋሻዬ የሕሊናን እጅ እንዲሰጧቸው ጥያቄ አቅርበዋል ብሎ ለያሬድ እንዲነግር የተመረጠበትን ምክንያት በጉዳዩ ጣልቃ እንዴት ሊያስገቡት እንደቻሉ የጠየቃቸው ኮሰተር ብሎና በቁጣ ነበር ::

« አይ ልጅ ተሾመ ፣ እንስማማ እንደሆነ በዚህ እንድንጨርሰው ብዬ እንጂ የማንግባባ ከሆነ እኮ ጉዳዩ ቀላል ነው :: አሁን ማ ይሙት . . ጋሻዬ እንቢ የሚባል ፣ ለዚህ የማይበቃ ሰው ሆኖ ነው ? እንኳን ይህችን መጤ ቀርቶ የፈለገውን መርጦ ማግባት ያቅተዋል ? እንዲያው ጥሉበት እንጂ » አሉ :: ቀኛዝማች እኔ የያዘኩት ነገር እንዴት ተናቀ በሚል የቁጭት አመለካከት ::

« ታግባባው እንደሆ አግባባው :: ጓደኛዬ ነው ብለህ የለ ? የጓደኛህን ጥቃት የማትወድ ከሆነ ልጅቷን ጠልፈን ከምንወስዳትና የማታገኝበት ቦታ ከማስቀመጣችን በፊት እኔም ሆንኩ አንተ በደንብ ብናስብበት ይሻላል :: እስከአሁን ከእኛ ምክር የወጣ በአቃቂ አለመኖሩንም ጠይቀህ ተረዳ » አሉ ኮስተር ብለው ::

ተሾመ ከረጅም ዝምታና ሀሳብ በኋላ « እንዴ ! እኔ እኮ እሺም እምቢም ለማለት ስልጣን የለኝም :: ያሉትን መልዕክት ለመናገሩ ከሆነ ነገሩን እነግረዋለሁ :: »



« ጎሽ ተባረክ ! ገና ወጣት ነህ :: በሥራህም ማደግ ትፈልጋለህ :: ከእኛ ትዕዛዝና ምክር መውጣቱ ደግም አይሆን » አሉት ቀኝአዝማች ዓላማቸው እንደተሳካላቸው ሲያረጋግጡ ::

« በል እንግዲህ እኔን ታገኛለህ በማንኛውም ነገር ስትፈልገኝ ከዚህ አልጠፋም እንዲያው የሆነውን ብቅ ብለህ አጫውተኝ » ብለው ሂሳቡን ከፍለው ከቡና ቤቱ ወጥተው ሄዱ ::

ተሾመ ቀኝአዝማች መራቃቸውን ሲያረጋግጥ የቀድሞውን የደህና እደሩ ሠላምታ ለቡና ቤቱ ሠራተኞች ሳያቀርብ ወጥቶ ሄደ :: እግሩ በተለምዶ ይራመዳል እንጂ ወዴት እንደሚሄድ እንኳን አያውቅም :: ከራሱ ሀሳብ ጋር ይሟገታል :: « አሁን በምን እግሬ እዚህ ቤት መጣሁና ይህን ውስብስብ ጉዳይ ሰማሁት ? አሁን ያሬድ ማ ይሙት ያቺን እንደ ጣኦት የሚያመልክባትን ፣ የሚወዳትንና ከሰው ጋር የተጣመደባትን ልጅ ለአብዬ ጋሻዬ . . . ያውም ለአብዬ ጋሻዬ አሳልፈህ ስጥ ብዬ ልነግረው ? ወይ ጉድ ! ይህን እንኳ አላደርገውም የማልችለውን :: » ብሎ ወደ ውሳኔ ሲቃረብ ቀኝአዝማች በመጨረሻ ስለ ሥራው የተናገሩት ጉዳይ ደግሞ ሀሳቡን እንደገና እንዲመረምረው ፣ እንዲያጤነው ወተወተው ::

« ማን ከነሱ ጋር ይቃቃራል ? እንኳን ሥራዬን እኔነቴን ሊያሳጡኝ ይችላሉ :: ምን ፈተና ፣ ምን ዕዳ ዳረጉብኝ ? » እያለ የሚሆነውንና የማይሆነውን እያሰላሰለ እቤቱ ደረሰ :: ተሾመ ሲያሰጨንቀው ያደረውን ጉዳይ ለያሬድ ለመንገር በቀጥታ እንደተጣደፈ ወደ ቢሮ አመራ :: ያሬድ ግን ያለ ወትሮው ቢሮው አልነበረም :: ሲንቆራጠጥ ቆይቶ ከሥራ ለመውጣት ሩብ ሰዓት እንደቀራቸው አገኘው ::

« ምነው በደህና ? ዛሬስ ዘገየህ :: ጠዋት ቢሮህ ብመጣ አልገባህም ነበር »

« ድሮ ከምገባበት ሠዓት ትንሽ አሳለፍኩ እንጂ ማርፈዴስ ይህን ያህል አይደለም ። ይልቅ ምነው የደከመህ ትመስላለህ ። ዓይንህም ከብዶታል ። »

« ማታ አምሽቼ ነበር የተኛሁት ። እዚህም ስመጣ ማሽን ተበላሽቶ እሱን ፊክስ ለማድረግ ስጨናበስ ዋልኩኝ ። ዕረፍትም አላገኘሁም » አለው ።

ያሬድ እና ሀለን ሳያስቡት ነበር ወንድማማቾች ቡና ቤት የደረሱት ። በረንዳ ላይ ቁጭ እንዳሉ ተሾመ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የተሸከመውን ጉዳይ እንዴት እንደሚተነፍሰው ሲያመነታ « አንድ የምነግርህ ጉዳይ ነበር ። ጠዋትም የፈለግኩህ በምክንያት ነው ። ያውም ያንተ ጉዳይ » አለ ተሾመ በረጅሙ ተንፍሶ ።

« ያውም የእኔ ? ደግሞ ምን ተፈጠረ ? የትርሲት የዘወትር አርቲቡርቲ ወሬ ከሆነ ልሰማው አልፈልግም ፤ እንዳታወራልኝ »

« አንተ ደግሞ ጉዳይህን የያዝኩት እኔ ፣ የምትጨሰው አንተ! ሰው ሁልጊዜ አይቀልድም » አለ ተሾመ በሩ[illegible]ስልቾትና በማማረር አኳኋን ።

ተሾመ ቀኝአዝማችን ከተዋወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ትናንት ድረስ ያለውን ታሪክ ሁሉ ለያሬድ ሲነግረው የያሬድ ፊት ቀስ በቀስ እየተለወጠ ፣ በቁጭትና በንዴት እየተመረዘ ይሄድ ጀመር ። ተሾመ ተርኮ እንደጨረሰ እፎይታ ተሰምቶት አጥፎ የነበረውን እግሩን ዘርግቶ ተዝናንቶ ተቀመጠ ። ያሬድ ለሰማው ነገር ቀንድና ጭራውን ለይቶ ለማወቅ እረጅም ሰዓት ወሰደበት ።

« ይልቅ ለምን ሆነ ብለን ከምንከራከርና ጉዳዩ ሰውየው እንዳሉት ወደ መጥፎ አዝማሚያ ከመድረሱ በፊት ማድረግ የሚገባንን በወቅቱ መፈጸሙ ላይ ብናተኩር የተሻለ ይመስለኛል ። ቀኝአዝማችም ጉዳዩን በቀላሉ ያዩት አይመስለኝም » አለ ተሾመ የመጠቡት አቀጣጫ በሩቁ እየቀፈፈው ።



ያሬድና ተሾመ ለረጅም ሰዓት ቡና ቤት ውስጥ ቆይተው ማምሻውን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተነጋግረው ተለያዩ ። ያሬድ ወደ ቤቱ አቅጣጫ ሲያመራ ተሾመ ወደ ከተማ አቀና ። ያሬድ እንደተለመደው ሳሎን አልተቀመጠም ። ለሕሊና እራሱን እንዳመመውና ሻይ እንድታፈላለት ነግሯት ወደ መኝታ ቤቱ ገብቶ የበኩሉን ሀሳብ እያውጠነጠነ « ይህ ሽማግሌ አልተው አለ አይደል ? አሁን ምን ልሁን ብሎ ነው በዚህ ዕድሜው እንዲህ የሚቀለው ? የሞቀ ትዳሩን ትቶ ልጁን ለማግባት የሚጥረው ? ከእሷ የማይተናነሱ ልጆች አድርሷል ። ምን በሀብት ላይ ሀብት ቢኖረው ፣ የተከበረም ቢሆን ለዚህች ለቀረችው አጭር ዕድሜ ሥሙን ባያጠፋና የልጅቷንም ዕድል ባያበላሽ ምን አለበት ። » እያለ ያሬድ የሰው ልጅ ክፋትና ስግብግብነት እያሳዘነው ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕሊና ወ/ሮ አባይነሽ ቤት በነበረችበት ወቅት ምናልባት ከኔ የደበቀችው ከሽማግሌው ጋር የሆነ ግንኙነት ይኖራት ይሆን ? ሲል እየተጠራጠረ ሳለ ሕሊና ሻይውን በማቅረቢያ አምጥታ ከመዲና ላይ አስቀመጠችለት ።

« ምነው አልተሻለህም ? ጋሼ ያሬድ ካፌኖል ለምን አትውጥም ? » አለችው ።

« ይሻለኛል ፤ ግድ የለም ሻይው ያሽለኛል » አላት ያሬድ ቶሎ እንድትወጣለት በአጭሩ በመመለስ ።

« የለም ሕሊና ይህን አታደርግም ። በፍጹም በዚህ አትጠረጠርም ። የምትደብቀኝ ነገር የለም » ሲል ወደ ጀመረው ሀሳብ ተመለሰ ።

ከሁለት ቀን በኋላ ያሬድና ተሾመ ከሥራ መልስ በረንዳ ላይ ወንበር አስመጥተው ቁጭ ብለዋል ። ተሾመ በቀደም ከያሬድ ተለይቶ እንደሄደ አንድ የትምህርት ቤት ጓደኛውን አግኝቶ ከቀኝአዝማች ጋር እንደተገናኙና ጉዳዩ ምን ደረጃ እንደደረሰ

ተነጋግረው ለአርብ በ12 ሠዓት ያሬድ ቤት መጥተው ፊት ለፊት በጉዳዩ ላይ ውይይት ለማድረግ እንደሚሹ አስረዳው ። ጉዳዩም በሰላም እንደሚያልቅ መምሩ ገዝሙ የሚባል እዚያው የነበረ የተሾመ ጓደኛና ሌሎች ሁለት ሽማግሌዎች አብረውት እንደሚመጡ በዝርዝር አጫወተው ።

« ወይ ጉድ እኔ ምን መሆኔ ነው ወደ እኔ የሚመጡት አክስቷ እሉ አይደለም ? እሳቸው ዘንድ አይሄዱም እንዴ ? እኔ እኮ የትናንት ሰው ነኝ ። እንደምታውቀው ከእኔ ጋር እንድትኖር ያደረግሁት . . . . » ብሎ የታወቀ ነገር መድገሙ እንደማያስፈልግ በመገንዘብ በእንጥልጥል ተወው ።

« ያሬድ አሁን እንደ አዲስ አትሁን ። በቀደም ስለ ሰዎቹ ማንነትና በከተማው ስላላቸው ተሰሚነት ተነጋግረንበት አልፈናል ። በውድ ካልሆነ በግድ ብለዋል ። እሱ ደግሞ መሆን እንደሌለበት ሁለታችንም ተስማምተናል ። ስለዚህ ውይይቱ አንድ መፍትሄ ሳይሰጠን አይቀርም ። ምናልባትም ማን ያውቃል ነገሩን ይተውት ይሆናል » አለ ተሾመ ያሬድን ለማግባባት በእጁም በጭንቅላቱም ንቅናቄ እያሳየ ።

« እንዳልከው የማይጋፉትን ባለጋራ መጋፋቱ አያዋጣም ። ግን . . . » ብሎ አቆመ ያሬድ ፣ ሊናገር ያሰበው እንደጠፋበት አፉን ከፍቶ ቀረ ። « የሽማግሌዎቹ መገኘት ነው ያልገባኝ እነሱ ደግሞ ምን ሊፈጥሩ ነው ? »

« ሽማግሌዎቹማ » አለ ተሾመ ቀለል በማድረግና በፈገግታ « አንተ ዘንድ ነው የሚመጡት ፣ ሊያግባቡህ ። ሰዎቹን እንኳን እኔ እንድመርጥ ዕድል ተሰጥቶኛል ። ድንገት የአንተና የሕሊና ምክንያት አይሎ ዕርዳታ ቢያስፈልጋችሁ ብዬ የሚያስማሙን ሰዎች እንዲመረጡ አድርጌአለሁ ። » ያሬድ የአገሩ ሰው ባለመሆኑ ለጥቃት እንደተዳረገ በመገመት በጣም አዘነ ። ዓይኑ እያየ ሕሊናን



ሊያስነጥቅ፣ ይህችን ውብና ለግላጋ አስተዋይና እሩህሩህ ልጅ ለማይገባ ሽማግሌ አሳልፎ ሊሰጥ ነው ። አማራጭ አልነበረውም ። የነገው ውይይት የመጨረሻ ዕድሉን የሚሞክርበት ይሆናል ። የሕሊና የወደፊት ዕድል የሚወሰንበት እንደሚሆን በመቁጠር ተሾመ የራሱን ሀሳብ አውጠነጠነ ። ተሾመ ከቀኝአዝማች ጋር የተስማማበትን ቀጠሮ በእሽታ ነበር የተቀበለው ። አርብ በ12 ሰዓት ያሬድ ቤት ተባብለው ነገሩን ጨርሰዋል ።

ሰሞኑን ያለማቋረጥ የአቃቂን ከተማ ሲያዳርስ የነበረው ዝናብ ጭው ባለ ፀሐይ ተተክቷል ። ጭቃው ደርቆ መንገዱም እንደልብ ያስኬዳል ። የያሬድ ቤት መግቢያ ያለ ችግር ያራምዳል ። ያሬድ ቀደም ብሎ ከሥራው ተመልሶ እቤት ነበር ። ከጎረቤት ሁለት ወንበሮች አስመጥቶ በእንግዶቹ ልክ መቀመጫ አዘጋጅቷል ። ሳሎኑ በሰንደል ሽታ እንዲታወድ ተደርጓል ። ሕሊና ቤቱን ስትጠራርግና ስታሰማምር ዋለች ።

« ጋሼ ያሬድ እንግዳው የሚመጣው ከአዲስ አበባ ነው ወይስ ከዚሁ ? » አለችው ።

« ከአዲስ አበባ እንኳን አይደለም ሌሎች እንግዶች ናቸው ከመ/ቤት የሚመጡት » አላት በደፈናው ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንግዶቹ ቤቱን ሞሉት ። ተሾመ ያሬድን ከቀኝአዝማችና ከሌሎችም ሽማግሌዎች ጋር አስተዋወቀው ። አብዬ ጋሻዬ ከእንግዶች ጋር እኩል አልገቡም ነበር ። ከያሬድ ቤት ትንሽ ራቅ ብሎ ከሚገኘው ቡና ቤት አረፍ ብለው ሽማግሌዎቹን መጠበቁን መርጡ ። ከሽማግሌዎቹ አንዱ አብዬ ጋሻዬ መምጣት እንደሚገባቸው ሲናገሩ ሰው ተልኮባቸው ካሉበት ተጠርተው ከሽማግሌዎቹ ጋር ተቀላቀሉ ። ነገሩ ግራ የገባቸው ሽማግሌዎች በዝምታ እርስ በእርሳቸው መተያየት ጀመሩ ። ቀኝአዝማች ረዥም ቁመናቸውን አግዝፈው ተነስተው ድምፃቸውን ለንግግር ሳሉና ፣

« እንግዲህ ወንድሞቼም ልበላችሁ እህቶቼ የተሰበሰብንበትን ዝርዝር ምክንያት በመግለጽ ጊዜ ላጠፋ አልፈልግም ። ሁላችሁም ነገሩን በጭምጭምታ የሰማችሁት መሰለኝ ። አባቶቻችን የመከረ ጊደር ምክር ያጣ ወይፈን ገዛ ይላሉ ። መምከር ማስመስከር አግባብ ነው ። ውጤቱም ጥሩ ነው ብለን ነው ዛሬ መገናኘታችን ። እንደምታውቁት . . . » ቀኛአዝማች ዞር ብለው በእገጫቸው አብዬ ጋሻዬን እያመላከቱ « እዚህ አቃቂ ሰረጅም ጊዜ ነዋሪ የሆነና በርስቱ፣ በፀባዩና በዘሩ የተከበረ የሰው ልጅ መካሪና አስታራቂ በመሆንም በቀደምትነት የሚጠራ ሰው ነው ። ታዲያ ይህ ሁሉ ሞልቶ ተርፎለት ዘሩን የሚቀጥሉለት ሴት ልጆች ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ሞልተውት ሳለ እንዲያው ቤቱን የሚያከብርለትና ወራሽም ሆኖ ታሪኩን የሚያስጠራ ወንድ ልጅ ሞክሮ ሞክሮ አልተሳካለትም » በማለት የተሰበሰቡበትን ምክንያት ሲተርኩ ከውጭ « የአቶ ያሬድ ቤት ነው ? » የሚል የሴት ድምጽ ተሰማ ።

ቀኛአዝማች የሰሙት ድምጽ የማን መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ በሩ አንገታቸውን አቅንተው ሲመለከቱ ወደ ቤት በመግባት ላይ የሚገኙትን የአብዬ ጋሻዬን ባለቤት ወ/ሮ ይትባረክን አዩ ። ተከትላም አንጋፋዋ የአብዬ ጋሻዬ ልጅ ትዕግሥት ገባች ።

የቀኛዝማች ዓይን ፊጦ የሚመለከቱት እውነት ነው ወይስ ህልም ነው የሚል ይመስላል ። ረጅም ሰውነታቸው ወደ አንድ ጎን አዘንብሎ ሊወድቅ ተዳርሷል ። ብዓይናቸው የአብዬን ዓይን ፈለጉ ። አብዬ ጋሻዬ ዓይኖቻቸው ፈጠው ፣ ላባቸው በግንባራቸው ቸፍ ብሎ፣ ከንፈራቸው ደርቆ ፣ የተከሰተውን ትርዒት ይመለከታሉ ።

« ቀጥል እንጂ ቀኛአዝማች ! ወይስ ያበቀልከው የእንጨት ሽበት ነው ። መች አጣሁት ? ከ25 ዓመት ባለቤቴ ጋር ልታሰያየኝ ከዚህ በፊትም ስትዶልት ነበር ። ያ ባይሳካልህ አሁን ደግሞ አሥር ልጆች እቤት ውስጥ አፍስሶ ሌላ የልጆቹን እኩያ እንዲያገባ ላይ እታች ስትል ትንሽ አታፍርም በማለት ቀኛአዝማች ላይ አፈጠጡባቸው » ።

ወ/ሮ ይትባረክ የአብዬ ጋሻዬን የአሰፈ ታሪክ በየቦታው መወሸማቸውንና በዚህ ዕድሜያቸው የሚያደርጉትን ዝሙት ለተሰበሰበው ሲናገሩ አንድም ሰው ለመመለስ አልሞከረም ። ወ/ሮ ይትባረክ የዛሬውን ሁኔታ እንዴት እንደተጠነሰሰና ማን እደጠነሰሰው መናገር ሲጀምሩ ዕንባቸውን ሊያግዱት አልቻሉም ። ሳግ ወረሳቸው። ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። ትዕግስትም ከነበረችበት ተንደርድራ አባትዋ ጉልበት ላይ ተንበርክካ መሪር ለቅሶ አሰማች ።

ያሬድ የመኝታ ቤቱን በር ተደግፎ ትርዒቱን ሲመለከት ከቆየ በኋላ በመጨረሻ የሰዎቹን ሁኔታ በውስጡ ለመሸከም ትዕግሥቱን ጨረሰ ። ብሶቱ ገነፈለበት ።

« አባቶች ከእናንተ የበለጠ ባላውቅም ከነገሩ ፊር ማጣት ከጓደኛዬ ከተሾመ ጋር ስንከራከርበት ነበር የከረምነው ። ይህችን ገና እንቡጥ የሆነች ልጅ የህይወት ታሪክ በከተማው እንደሰማችሁት ወይም እናንተ እንደምታውቁት አይደለም ።

ሕሊና . . . » ብሎ ስለ ሕሊና ትውልድ ዕድገት ፣ ስለ ቤተሰቦችዋ ሁኔታ የሚያውቀውን ሁሉ በዝርዝር አስረዳ ። አብዬ ጋሻዬን ሊደግፉ የመጡት ሽማግሌዎች አንገታቸውን በመነቅነቅና በሀዘኔታ ነበር ያዳመጡት ።

« እና ይህች ልጅ ለእሷም ሆነ ለወገኗ የምትጠቅመው እኩያዋ ያልሆኑ ሰው ፣ ያሰዕድሜዋ አግብታ ሳይሆን ከራስዋ አንደበት ለመስማት እንደምትችሉት ተምራና እራስዋን ችላ ፣ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ በውስጧ ስትረዳ ብቻ ነው ። የአባቷን አደራ ለመወጣት የቆረጠች ወጣት ናት ። ስለዚህ አባቶች ድፍረት አይሁንብኝና የእናንተን ልመና አልፈልግም ። ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ

እንዛር እንድትፈርዱልኝ ወይም እንድትፈርዱብኝ ነው ልመናዬ » አለ ያሬድ ግንባሩ ላይ የወጣውን ላብ በመሀረቡ እየጠረገ ።

« ይህን አሳዛኝ የህይወት ታሪክ ሰምተው ምንስ ተጨማሪ ማብራሪያ ፣ ምንስ ጥያቄ ይኖረዋል ? እንዲህ ባለ ቅሌት ውስጥ እራሴን አግብቼ አላውቅም ነበር ። ዛሬ ግን ተሳሳትኩ » ብለው ማንንም ሳይመለከቱ በመጀመሪያ የወጡት ለተሾመ ቤት ያከራዩት አቶ ድንበሩ ነበሩ ። ሌሎቹም እንገታቸውን እንደደፉ ተከታትለው ወጡ ። ትዕግስትና ወ/ሮ ይትባረክ በስተመጨረሻ ያሬድን ተሰናብተው ሄዱ ።

ያሬድ በዚያን ቀን የተቀዳጀው ድል በሰፈሩ ተነዛ ። አብዬ ጋሻዬ ግን ከዕለቱ ጀምሮ የሞተው ልባቸው አላገገመላቸውም። በከተማውም አዘውትረው ከመታየት ታቀቡ ።



# ምዕራፍ ሦስት

ወ/ሮ አባይነሽ ስለ መጥረቢያው ምስጢር በተዘዋዋሪ ከያሬድ አነጋገር ከተረዱ ወዲህ አንድም እሳቸውን ያህል ሰው በአንድ አልባሌ ዘበኛ መታለሉ ፣ ይበጀኛል ብለው የሰሩት ደባ በሥሩ እንዲተዳደሩ ስለአደረጋቸው በጣም ፀፀታቸው ። አዋቂ ነኝ ባዩ ጠንቋይ የማነብርሃን አረክሳለሁ፣ አወግዛለሁ በማለት የወሰደው ገንዘብ እንደ እግርእሳት አቃጠላቸው ። ምስጢሩ ይፋ ከሆነላቸው በኋላ ደግሞ ለፀፀትም ለመቃጠልም ቦታ አጡ ። መበቀል አሰባቸው ። ሁሉም የእጁን ማግኘት አለበት ። እቅድ አወጡ ። በመጀመሪያ ፈሩቅ የገዛቸውን ጓደኞቹን ማሸነፍና በቁጥጥር ሥር ማዋል ። ከዚያ በኋላ እሳቸው ያውቁበታል ። ፈሩቅን ማጅራቱን መቶ መጣል ነው በቃ-ግልግል ! እስከዚያ ፈሩቅን ማባረር እንደሌለባቸው አምነዋል። ለዚያውም ቢሆን ጠባቂ ያስፈልጋቸዋል ። ፈሩቅን የሚያሸንፍ ሰው አለቡ ። ግን ማን ይታመናል ? ከፈሩቅ ወዲህ ሰውን ማመን አይቻልም ። ሌላ አማራጭ አገኙ ። ሽጉጥ ገዝተው ተለማምደው ራሳቸውን ለመጠበቅ ወሰኑ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ስዝግጅታቸው ጊዜ አላባከኑም ። በደላሎች አማካኝነት አንድ ኮልት ሽጉጥ በሺህ ሁለት መቶ ብር ገዙ ። አንድ ጡረተኛ ወታደር በምስጢር ቀጠሩና ልምምዱን ጀመሩ ። ቃታ አሳሳቡን ፣ የሽጉጥ ጥይት አጎራረሱንና ፣ ማነጣጠሩን ሲያጠኑ ቆይተው ፤ በመጨረሻም በድብቅ ከከተማ ወጥተው የተግባር ልምምድ አደረጉ ። ቀጥለው ከፈሩቅ ጋር የሚያያይዟቸውን ገመዶች መበጣጠስ ያዙ ። አዲስ አበባ ሄደው ስድስት አስተናጋጆች ይዘው ተመለሱ ። የቡና ቤቱን በር ዘጉ ። ከቀድሞዎቹ የቡና ቤት

አስተናጋጆች መካከል ከሁለት ሰዎች በስተቀር ሌሎቹ ሂሳባቸውን እንዲያስረክቡ አደረጉ ። ሰራተኞቹም እየተደረገ ባለው ሁኔታ እየተደናገጡ ያለባቸውን ሂሳብ አስረከቡ ። « በሉ በጣም ነው የማመሰግናችሁ ። በጉልበታችሁ ረድታችሁኛል ። ከዛሬ ጀምሮ ግን እንድትሰሩልኝ አልፈልግም ። አሰናብቻችኋለሁ » ሲሉ ትዕዛዝ ሰጡ።

« መሄድስ እንሄዳለን ሾፌሮች ብቻ አይደለም ቡና ቤት ዕድሜ ሰጉልበታችን ወጣቶች ነን ደሞዛችንን ይስጡን ። » በማለት አንዷ አስተናጋጅ አፈጠጠችባቸው ።

« ቦጌ የናንተን ደመወዝ የማስቀር ሰው አይደለሁም ። ነገ ኑና ውሰዱ ። አልጠፋም ቤት ንብረት ያለኝ ሰው ነኝ ። » ብለው እያጣደፉ ሸኟቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ በዚህ ስልታቸው የፈሩቅ ቅምጦች ናቸው ብለው የጠረጠሯቸውን ሴቶች ከቡና ቤት አሰናበቱ ። ፈሩቅ በቤት ውስጥ የሚደረገውን ድርጊት በቅርቡ እንዳይከታተል የሩቅ መነጽሩን እንደቀሙት አድርገው ቆጠሩ ። አዲስ ቀጥረው ያመጧቸውን ሴቶች በተባረሩት ምትክ አሰማሩ ።

« ከእኔ በስተቀር ለዚህ ቡና ቤት ኃላፊ የለም ። የሚያስፈልገውን ነገር እኔን መጠየቅ ትችላላችሁ ። ማንም ሰው መጥቶ እኔ ነኝ ኃላፊ ብሎ ቢያጭበረብራችሁ በኃላፊነት ትጠየቃላችሁ » በማለት ግልጽ ትዕዛዝ አስተላለፉ ። አስተናጋጆቹም ለአዲሱ ሥራቸው ያመቻል ያሉትን ጌጣ ጌጥና ልብስ ለብሰው ወደ ሥራ ገበታቸው ተሰማሩ ።

ወ/ሮ አባይነሽ ሳሎን ሄደው ጥቂት ቆይታ አድርገው ፣ አንድ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር ይዘው ቡና ቤታቸው ገቡና በገንዘብ ተቀባይ ባንኮኒ ተሰየሙ ። ቡና ቤቱ በአዲሶቹ ሠራተኞች ተወሯል ። አመሻሹ ላይ አዲሶቹ አስተናጋጆች በወ/ሮ አባይነሽ ፊት ምን ያህል ተወዳጅ እንደሆኑና ቅልጥፍናቸውን ለማሳየት በቤቱ ውስጥ



እንደዕንዝርት በመሽከርከር ደንበኞቻቸውን ማስተናገዱን ተያያዙት ። በወረት አዲስ ፊት ለማየት የተኮለኮለው ደንበኛም የቡና ቤቱን ገበያ አደራው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከቀድሞው በበለጠ ፈገግታ ደምቀው ገቢውን በመቀበል ወጪውን በመሰናበት ቤቱን ከዳር እስከዳር ይቃኛሉ ። ለአንድ አፍታም ቢሆን ከተቀመጡበት ወንበር አልተነሱም ። ሳይሰለቹ በዚሁ ሁኔታ ቡና ቤታቸውን ሲመሩ አመሹ ። ጊዜው መሽቶ ደንበኞች በሙሉ ከወጡና ቤቱ ባዶ ከሆነ በኋላ ወደመኝታ ክፍላቸው ሲያመሩ በጨርቅ የጠቀለሉትን ነገር ጠበቅ አድርገው ይዘው ነበር ።

* * *

ለያሬድ ይህ ሳምንት የፈተና ጊዜው ሆኖበታል ። ከአብዬ ጋሻዬ ጋር ቁርጥ ያለ ውይይት አድርጓል ። በዚህ ጉዳይ ከሕሊና ጋር ተግባብተዋል ። የቀረው ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ስለሚያደርገው ድርድር ከሕሊና ጋር ለመወያየት መቻል ነበር ። ያሬድ ለሕሊና ደፍሮ ለመንገር አልቻለም ። ቢሆንም አንድ ምሽት ደፈረ ። ጊዜው መሽቶ ሕሊና ኩሽና ውስጥ ለእራት የሚሆን ምግብ በማበሳሰል ላይ ነበረች ። ወደ ቤት ስትገባ ያሬድ ከከረጢቷ ውስጥ የአባቷን መጥረቢያ አውጥቶ ፣ አልጋዋ ላይ አስቀምጦ ፣ ወንበሩን ወደ አልጋዋ አዙሮ ፣ ዓይኖቹን መጥረቢያው ላይ ተክሎ ሲመለከት አገኘችው ። በሁኔታው በመደናገጥ መለ ሰውነቷን ወደ ሳሎን ሳታስገባ በሩ ላይ ቆማ አስተዋለችው ። ያሬድ ፊቱን ሳያዞር ወደ መጥረቢያው እየተመለከተ « ሕሊና ግቢና ተቀመጭ » አላት ። ምንም ድምጽ ሳታሰማ ወንበር ስባ ከያሬድ በስተጀርባ ተቀመጠች ።

« ሕሊና አባትሽን በጣም ትወጃቸው ነበር ? » ሲል ጠየቃት።

« እንዴት ማለት ትወጂያቸው ነበር ስትል ? አሁንም እወደዋለሁ » አለችው አጠያየቁ ግራ ገብቷት ::

ያሬድ ፊቱን ወደ ሕሊና መልሶ ፣ « አይዞሽ አትፍሪ » በማለት ፈገግ አለና ፣ « አባትሽ በጣም ጥሩ ሰው ነበሩ :: የዚያ የሰይጣን ሀሳብ ባይረብሽን ኖሮ ዛሬ ላነጋግርሽ ያሰብኩት ስለ አንድ ጉዳይ ነበር :: ሆኖም አሁንም ዝም አልልሽም :: ልንወያይ እንችላለን » በማለት አልጋው ላይ የተቀመጠውን መጥረቢያ አነሳና ለሕሊና ሰጣት ::

መጥረቢያውን እንደ ቀድሞዋ በደስታ ወዲያውኑ አልተቀበለችውም :: ፍርሃት በተሞላበት አመለካከት እያየች ሁለት እጆችዋን ቀስ ብላ ዘረጋችና የመጥረቢያውን እጀታ በዓይኖችዋ ከላይ እስከታች ዳሰሰች :: ያሬድ የሕሊናን ድርጊት በማስተዋል ከመጥረቢያው ላይ ዓይኑን ሳያነሳ ፣ « ሕሊና በጠረጴዛው ላይ አስቀምጪው » አላት :: በጥንቃቄ የተባለችውን አደረገች ::

« ጋሼ ያሬድ ያለፈው አለፈ :: ጉዳዩን ሁሉ ሳትረዳ አልቀረህም :: አሁን ደግሞ ምን አደረግሽ ልትለኝ ነው ? » ዓይኖችዋን በልመና መልክ ዕንባ ሞልታ በያሬድ ዓይኖች ላይ አሳረፈች ::

ያሬድ በሀሳቡ « አይ ሕሊና እነኚህ ውብ ዓይኖችሽ ሲያለቅሱ የኔ ልብ ይደማል እባክሽ አታልቅሺ :: ፈገግታሽ ለሰውነቴ ሙቀት ለማንኛውም በሽታዬ መድኃኒት ነው :: እባክሽ ሕሊና ካንቺ ዓይን ጠብ ጠብ የሚሉት ዘለላ እንባዎች ከኔ ልብ እንደሚፈስ ደም ነው የምቆጥረው :: » በማለት ሳያስበው ብድግ ብሎ ወደ ሕሊና ጀርባ ዞረ:: ከበስተጀርባዋ ሆኖ በእጆቹ የሕሊናን አንገት ዳሰስ አድርጎ አቀፋት እሷም እጆቹን ከእጆችዋ ጋር በማጣመር ወደ ደረቷ አስጠግታ ያዘቻቸው :: ለሕሊና የመንፈስ ጭንቀት የያሬድ አጠገቧ መኖር ወሳኝ ነበር :: ዓይኗ ላይ ያቀረረው እንባ ተመልሶ ተዋጠ ::



ፍም መስሎ ደም ሊተፋ የደረሰው ጉንጭዋ እየፈካ መጣ :: አንገቷን ወደኋላ መለስ አድርጋ ከላይዋ ላይ የቆመውን ያሬድን ፈገግ በማለት አስተዋለች ::

« ምንድነው ተናገር እንጂ ለምን ዝም ትላለህ ? » በማለት እጆቹን በእጆችዋ ዳሰሰቻቸው ::

« ሕሊና አትቀየሚኝ ዋሽቼሻለሁ :: ዛሬ ከአዲስ አበባ የሚመጡ እንግዶች ብዬ የነገርኩሽ እነማን እንደነበሩ አይተሻል :: ይህ አንደኛው ውሸት ነው » ብሎ እንደገና አንገቱን ዝቅ አድርጎ የሕሊናን ዓይን በመፈለግ ዓይነት ተመለከተ ::

« አልቀየምህም ተናገር :: ለዚህ ነው አባቴን ያስታወስከው?» ስትል ፈገግ አለች:: ያሬድ እጆቹን ከሕሊና እጆች ላይ የግዱን አላቆ ፊት ለፊቷ ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ::

« ሁለተኛው ውሸት ደግሞ ሕሊና በቀደም እሁድ አትሂድ ያልሽኝ ቦታ ሄጃለሁ :: » በማለት ቀና ብሎ ተመለከታት ፣ እራሱን በቀኝ እጁ እያሻሸ ::

« እህ . . . እናስ ? » ስትል በድንጋጤ ጠየቀችው :: ፊቱ ከመቅጽበት ጨለመ ::

« ሕሊና ጉዳዩ ፈፅሞ አንቺ እንዳሰብሽው አይደለም :: አክስትሽ የጋበዙኝ ምሳ ለመብላት ሳይሆን ከአንቺ ጋር እርቅ ለመደራደር ነው » አላት ፍርጥም ብሎ ::

« እርቅ ? ይህ ዘዴ ደግሞ መቼ ተከሰተላቸው ? መቼም ከዚህ ሀሳባቸው በኋላ ሌላ ዕቅድ ይኖራቸዋል :: ታዲያ አንተ ምን ብለህ መለስክላቸው ? » ስትል ጠየቀችው ::

« መቼም ያልደረደሩት ምክንያት አልነበረም :: የለቅሶውን ነገር ተይው :: በመጨረሻም እራሳቸውን ሰተው ታመሙና ለሌላ ጊዜ ተቃጥረን ተለያየን » ሲል አስረዳት :: የሰማችውን በጥሞና

የምታዳምጥ መስላ ዓይኗን ፊት ለፊት የተጋደመው መጥረቢያ ላይ ተክላ ተመለከተች ::

« እ . . እ . . . ምን አልከኝ ? ጋሼ ያሬድ » በማለት አስተዋለችው :: የሒሊና ሀሳብ በምን ላይ እንዳተኮረ ለማወቅ አላዳገተውም :: መጥረቢያው ! ሒሊና እንኳን በግልፅ ፊት ለፊቷ ተቀምጦ ቀርቶ በከረጢትም ውስጥ ሆኖ ጫፉ ከታየ ሀሳቧ ከሱ ጋር እንደሚሆን ካወቀው ቆይቷል ::

« ወ/ሮ አባይነሽ በእውነትም ባደረጉት ጥፋት ተፀፅተው ከልባቸው ይቅርታ የሚጠይቁ ከሆነ ከአባትሽ የወረስሽው ደግነት እንዲታሰብሽ ስል ነው መጥረቢያውን ያወጣሁት :: ሒሊና ፣ ከይቅርታ በስተቀር ወ/ሮ አባይነሽ ከአንቺ የሚፈልጉት ነገር አይኖርም :: ሒሊና ወ/ሮ አባይነሽ በበሽታ የታጠሩ ይመስለኛል :: ምናለ በጥፋታቸው ይቅር ብትያቸው ? » አላት በልመና ዓይነት ከአንገቱ ጋደል ብሎ አትኩሮ እያስተዋላት ::

« ጋሼ ያሬድ ከዕለታት አንድ ቀን አባቴ ፣ ደግነት ፣ ሀቀኝነት ሁሉም በቦታቸው ሲደረጉ ብቻ ነው ትርጉም የሚኖራቸው፤ ያለቦታቸው ከተጠቀምንባቸው ትርጉማቸው ሞኝነት ይሆናል ብሎ ነግሮኝ ነበር :: » አለችና ከተቀመጠችበት ተነስታ መጥረቢያውን በእጇ እየዳሰሰች « የእኔ አክስት ላደረሱብኝ ጥፋት ከእኔ ይቅርታ ቢያገኙም የሞቱትን ግን ይቅርታ ሊጠይቋቸው አይችሉም :: የእኔ ይቅርታ ብቻውን ሠላም ሊሰጣቸው መቻሉን እጠራጠራለሁ :: ከእኔ በበለጠ ግፍ የተዋለባቸው አሉ :: በእርግጥ እሁን በህይወት የሉም :: ለዚህም ነው የሞቱትን ይቅርታ ለመጠየቅ ባለመቻላቸው ቋሚውን በራሳቸው ጭንቀት ግፍ ሊውሉባቸው እንዳች ነገር የሚያስገድዳቸው:: ጋሼ ያሬድ ባንተ ስም ስለመጡብኝ እኔ እራሴ ብቻ ይቅርታ ላደርግላቸው ዝግጁ ነኝ :: ሆኖም የእኔና የእሳቸው ግንኙነት እንደ ቀድሞው ሊሆን አይችልም :: የቀድሞውን ከሞቱት ሰዎች ጋር አንድ ላይ ቀብረውታል » በማለት እራስዋን ቀና አድርጋ እጆችዋን ከመጥረቢያው ሳትለይ ያሬድን እያየች ፈገግ ብላ ቀረች ::



ያሬድ የሒሊናን አነጋገር በተመስጦ ነበር ያዳመጠው :: በሰጠችው ቃል ፍላጎቱ በመርካቱ ፊቱ ፈካ :: « ሒሊና በጣም ደግ ሰው ነሽ :: ለእኔ ብለሽ ለወ/ሮ አባይነሽ ይቅርታ ማድረግሽ በእኔ ዘንድ እንደ ትልቅ ውለታ ነው የምቆጥረው :: አመሰግናለሁ ! » ብሏት ከመቀመጫው ብድግ ሲል ፣

« ጋሼ ያሬድ » በማለት ጠራችው :: ዓይን ዓይኑን እያየች « እንግዲህ ሁሉንም ባንተ በኩል ፈፅመው :: እኔ ከእሳቸው ጋር ዓይን ለዓይን መተያየት አልፈልግም :: » አለችው ::

እራሱን ቀስ ብሎ በመነቅነቅ መልስ ሰጣት :: ሒሊና ተመልሳ የአባቷን መጥረቢያ በፍቅር ተመለከተች :: ዓይኗ እንባ አቀረረ :: በማይሰማ ድምፅ ከንፈሯን አንቀሳቀሰች :: ከከባድ ሥራ እንደተመለሰ ሰው « እፎይ » ብላ በረጅሙ ተነፈሰች :: ያሬድ የቀን ሸክሙን ካራገፈ በኋላ ቀለል ስለአለው ወደ መኝታው ገብቶ አልጋው ላይ ጋደም አለ :: ፊቱ እንደፈካ እንቅልፍ ሸለብ አደረገው ::

ሒሊና ሥራዋን እንደጨረሰች ከነልብሷ መኝታዋ ላይ ጋደም ብላ ክንዷን ተንተርሳ ሳለ የያሬድን ንግግር ማሰላሰል ጀመረች :: ወሰን የለሽ ደግነቱን በማድነቅ በአባቷ ምትክ ይሁን ሰው በማግኘቷ በጣም ደስ ተሰኘች :: ያሬድ ተቀምጦበት የነበረውን ወንበር ፈገግ ብላ መልከት አደረገችና ቀስ ብላ ልብሷን አወላልቃ የእንቅልፍ ጉዞዋን ጀመረች ::